# ነገረ-ኢትዮጵያ

ስለ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን እንናገራለን!

ቅፅ 1 ቁጥር 5 | አርብ መጋቢት 12 2006 ዓ.ም. | ዋጋ 8.00 ብር

መዘመሩ ኢህአዴግ! 3

ሰላማዊ ትግሉ መሪዎቹን ይሻል 12

የኢትዮጵያ ፖለቲካና የሴቶች ተሳትፎ 11



## የሰማያዊ ፓርቲ ሊቀመንበር በአሜሪካ መንግስት የአፍሪካ ስኬታማ ወጣት መሪ ተብለው ተመረጡ

## ‹‹ለውጡ እንደቀረበ ጥርጥር የለኝም››

ኢ/ር ይልቃል ጌትነት፣ የሰማያዊ ፓርቲ ሊቀመንበር

4

አዲስ አበባ፡- የሰማያዊ ፓርቲ ሊቀመንበር ኢንጅነር ይልቃል ጌትነት በአሜሪካ መንግስት ስቴት ዲፓርትመንት የአፍሪካ ስኬታማና በቀጣይነትም ሀገራቸውን መምራት የሚችሉ ወጣት መሪ ተብለው ተመረጡ፡፡

ከፓርቲው የህዝብ ግንኙነት የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው ኢንጅነር ይልቃል ለአሸናፊነት የበቁት ‹‹የአሁኑ ወጣት የአፍሪካ መሪና ወደፊትም ለአገራቸው መሪ ሊሆኑ የሚችሉ፣ በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ጥሩ ስራ የሰሩ መሪዎች መካከል በተደረገ ውድድር በአሜሪካ መንግስት ስቴት ዲፓርትመንት›› መስፈርቱን አሟልተው በመገኘታቸው ነው፡፡

ሊቀመንበሩ ለአሸናፊነት መብቃታቸው ይፋ ከመሆኑ በፊት የአሜሪካ መንግስት የኢንጅነር ይልቃልን መሰረታዊ የሚባሉትን የፖለቲካ ቆይታ፣ የትምህርት ዝግጅት፣ በፖለቲካው ውስጥ የነበራቸውን ተሳትፎ እና የመሳሰሉትን መረጃዎች ወስዶ እንደነበር ለማወቅ ተችሏል፡፡

ኢንጅነር ይልቃል በዚህ ውድድር በመመዘኛዎች መሰረት በማሸነፋቸው በአሜሪካ መንግስት ስቴት ዲፓርትመንት የጉብኝት ግብዣ ተደርጎላቸዋል፡፡ በመሆኑም የአሜሪካ መንግስት ሙሉውን ወጭ ሸፍኖ ለሶስት ሳምንት በአሜሪካ የመንግስት አወቃቀርና ዴሞክራሲን ጨምሮ በተግባር የሚሰጡ ስልጠናዎችን የማግኘትና የአሜሪካ መንግስት ባለስልጣናትም ባሉበት ከተለያዩ ተቋማት ጋርም ለመገናኘት እድል እንደሚኖራቸው ያገኘነው መረጃ ያመለክታል፡፡

‹‹የሊቀመንበሩ ለዚህ ሽልማት መብቃት አዲሱን ትውልድ ወደ ፖለቲካው ለማምጣት በሚያደርገው ጥረት እንደ አንድ ማበረታቻ ተደርጎ ሊወሰድ እንደሚችልና ሰማያዊ ፓርቲ እያደረገው ላለው ሰላማዊ ትግል ትልቅ እውቅና እንደሆነ ያሳያል›› በማለት የህዝብ ግንኙነቱ ያደረሰን መረጃ ይጠቅሳል፡፡ ኢንጅነር ይልቃል ጌትነት ዛሬ ወደ አሜሪካ እንደሚያመሩም መረጃው ጨምሮ ገልጾዋል፡፡

( በጉዳዩ ዙሪያ ነገረ-ኢትዮጵያ ኢንጅነር ይልቃል ጋር ሰፋ ያለ ቆይታ አድርጋለች፡፡ ሙሉ ቃለ-መጠይቁን ገጽ-4 ይመልከቱ፡፡)







## ባለ ቀለሙን አብዮት ማን ይመራዋል?

5



ነጻነት የዋጋ ተመን የለውም! 15

ለለውጡ ዝግጅት ያስፈልጋል! 2

# ርዕሰ አንቀጽ

## ለለውጡ ዝግጅት ያስፈልጋል !

ለውጥን ማዘግየት ይቻል እንደሆን እንጂ ገድቦ ማስቀረት እንደማይቻል ከትርክት አልፎ በተግባር የታየ ሀቅ ነው፡፡ በተለይ ህዝባዊ የለውጥ እንቅስቃሴን አፍኖ መዝለቅ የማያዛልቅ ሙከራ እንደሆነ በተለያየ ጊዜ በተለያዩ ሀገራት ታይቷል፡፡ በዓለም ላይ የማይለወጥ ነገር አለ ከተባለ ራሱ ለውጥ ነው የሚባለውም ለዚህ ነው፡፡ የአሜሪካ ፕሬዝዳንት የነበሩት ጆን ኦፍ ኬኔዲ ‹‹እነዚያ ሰላማዊ ለውጥን የማይቻል ለማድረግ የሚሞክሩ ሁሉ ሀይል ያመዘነበት አብዮትን የማይቀር ያደርጉታል›› እንዲሉ ለውጥን ለመገደብ መሞከር በራሱ ከዚያም በላይ የሆነ ታላቅ አብዮትን ይጠራል፡፡

በሀገራችን ለበርካታ ጊዜያት ይህ ሀቅ በእውን ተከስቷል፡፡ 40 አመታትን ወደኋላ ብንጓዝ እንኳ የ1966ቱ አብዮት ያለበቂ ዝግጁነት የተካሄደ እንደነበር እናስታውሳለን፡፡ በወቅቱ የኑሮ ውድነት፣ ብዝበዛ እንዲሁም ቅጥ ያጣ በስልጣን መባለግ የነበረ ቢሆንም፣ የአጼው ስርዓት የህዝብን ሰቆቃና ቅያሜ፤ የዓለምንና የኢትዮጵያን ወቅታዊ ሁኔታ ከምንም ባለመቁጠሩ የተቀጣጠለውን ህዝባዊ አብዮት፣ በአግባቡ መርቶ ፍሬያማ ለማድረግ የሚያስችል ስራ ባለመሰራቱ አሁን ድረስ ለዘለቀው የፖለቲካችን ብልሹነትም ሆነ ለስርዓቱ አሳዛኝ መጨረሻ ጉልህ አሉታዊ አስተዋጽኦ አበርክቷል፡፡

ህዝባዊ አብዮት መቼ ሊቀሰቀስ እንደሚችል በእርግጠኝነት ለማወቅ ቢከብድም በአንዲት ሀገር ያለው ነባራዊ ሁኔታን በመመልከት ግን የለውጡን ነጋሪት ማዳመጥ ይቻላል፡፡ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ በተለያዩ ሀገራት የተነሱትን አብዮቶች ስናይ፣ ማናቸውም በአምባገነን የአገዛዝ ስርዓት ስር የሚገኝ ህዝብ ነጻነቱን በህዝባዊ የለውጥ እንቅስቃሴ ለማወጅ ወደ ኋላ እንደማይል ነው፡፡ በቱኒዝያ፣ ግብጽ፣ ሊቢያና በሌሎችም ሀገራት የተስተናገደውን ህዝባዊ አብዮት ለአብነት ማንሳት ይቻላል፡፡

ሰሞኑን ደግሞ መሰል አብዮት ከወደ ዩክሬን ተስተናግዷል፡፡ የዚህ ሁሉ አብዮት መንስኤ በየሀገራቱ ሰፍኖ የቆየው አምባገንነት ነው፡፡ ወደ ሐገራችን ሁኔታ ስንመለስም ከ1966ቱ ጊዜ በባሰ የኑሮ ውድነት፣ የሐይማኖት ጣልቃገብነት፣ ኢ-ፍትሐዊነት፣ የመሰረታዊ አገልግሎት መጓደልና ሌሎችም ችግሮች ተደራርበው የህዝብን ጫንቃ አጉብጠውት ይገኛሉ፡፡

ይህን በሀገራችን የተንሰራፋውን ጭቆናና የኑሮ ውድነት ስናይ የህዝባዊ አብዮትን መምጣት እንድንገምት ያደርገናል፡፡ እንዲህ አይነቱ ሲጠራቀም በቆየ የህዝብ ብሶት ምክንያት ሊነሳ የሚችልን የህዝብ የለውጥ እንቅስቃሴ ደግሞ ማስቀረት አይቻልም፡፡ ትንታጉ ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ ደጋግሞ ይለው እንደነበረው ዳግም አብዮቱ በኢትዮጵያ መከሰቱ አይቀርም፡፡ ይህን ለውጥም የሚያስቀረው ኃይል አይኖርም፤ ያለው ብቸኛ አማራጭ (በተለይ በመንግስት በኩል) የሚመጣውን ለውጥ በአግባቡ ማስተናገድ ወይም ‹ማኔጅ› ማድረግ ነው፡፡

በእርግጥም ለውጡ ካለው የሀገሪቱ ሁኔታ አኳያ ሲታይ መከሰቱ የማይቀር ነው፡፡ ስለሆነም አሁን ላይ ለሚመጣው ህዝባዊ እንቅስቃሴና ለሚከተለው ለውጥ መዘጋጀት ያስፈልጋል፡፡ የተከሰተውን ህዝባዊ አብዮት በአግባቡ አለመምራትና አለማስተናገዳችን ያስከተለብንን አሉታዊ ተጽዕኖ የዛሬ 40 ዓመት አይተናል፡፡ አሁን ከዚያ ድክመታችን ትምህርት ቀስመን የቀረበ የሚመስለውን የለውጥ ትግል መምራትና ማስተናገድ እንዳለብን እሙን ነው፡፡

በህዝባዊ የለውጥ እንቅስቃሴ ሁለት ዋና ዋና አካላት ይበልጡን ከፊት የሚገኙ ይሆናል፡፡ አንደኛው መንግስት ሲሆን ሌላኛው በተቃውሞ ጎራ ያለውና የትግል አቀጣጣዩን ክንፍ (ነጻ ማህበራት ሊሆኑ ይችላሉ) የሚያካትተው አካል ነው፡፡ መንግስት ቢችል ለውጡን የማደናቀፍ ስራን ለመስራት መሞከሩ አይቀርም፡፡ ከዚህም አልፎ ጭራሹን የህዝብን እንቅስቃሴ ለመጨፍለቅ ሊሞክር ይችላል፡፡ ይህም እርምጃ እጅጉን አደገኛና ክቡር ህይወትን ሊቀጥፍ የሚችል እስከመሆን ይደርስ ይሆናል፡፡ እንዲህ አይነቱ እርምጃ የሚመጣው ለለውጡ ካለመዘጋጀት ስለሚሆን በመንግስት በኩል ከአሁኑ ዝግጅት ማድረግ እንዳለበት ነገረ-ኢትዮጵያ ማሳሰብ ትወዳለች፡፡ ይህን በማድረግም መንግስት ቢያንስ ለውጡን ‹ማኔጅ› በማድረግ ኃላፊነቱን መወጣት ይቻለዋል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ የለውጡን እንቅስቃሴ በአግባቡ መርቶ ተፈላጊውን ውጤት ማምጣት ለማስቻል በተቃዋሚ ፓርቲዎች ዘንድና በነጻ ማህበራት በኩል በቂ ዝግጅት ማድረግን እንደሚጠይቃቸው ማስገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

ምንም ያህል ከስርዓቱ ወገን ለውጥን ለማስተናገድ ያለመፈለግና ያለመዘጋጀት ቢታይም እንኳ ህዝብ የተነሳለትን ዓላማ ማስቀረት እንደማይቻል ተገንዝበው፣ ለውጡን በተደራጀና በአንድነት መንፈስ ለመምራት የፓርቲዎችና የማህበራት ሚና የጎላ መሆኑ ለአፍታም መዘንጋት የለበትም፡፡ ስለሆነም እነዚህ አካላት ጥቃቅን ልዩነቶች ሊኖራቸው ቢችል እንኳ በእንዲህ አይነት ወቅት ትብብራቸውን ማጠናከርና ለጋራ የህዝብ ጥቅም መቆም ይኖርባቸዋል፡፡ ከምንም በላይ ደግሞ ሊመጣ የሚችለው ለውጥ እውን ከሆነ ማግስት ሌላ ችግር እንዳይከሰት ህዝብ አመኔታ የሚጥልበትና በቀጣይ የመሪነት ሚናን ለመወጣት ጠንካራ ፓርቲ ሆኖ መውጣት ግድ ይላል! ለዚህም ዝግጅት ማድረግ ያስፈልጋል!

## እንዲህም ተብሏል

‹‹ሌላ ሰው አልያም ሌላ ጊዜ የምንጠብቅ ከሆነ ለውጥ አይመጣም፤ ለለውጡ ስንጠበቅ የነበርነው እኛው ራሳችን ነን፡፡ የምንሻውን ለውጥ የምናመጣውም እኛ ነን››

ባራክ ኦባማ፣ የአሜሪካ ፕሬዝዳንት

‹‹በህይወት ዘመንህ ሙሉ እስረኛ ከመሆን፣ ለነጻነትህ እየተዋጋህ ብትሞት ይሻላል››

ቦብ ማርሌይ፣ የሬጌ ሙዚቃ ንጉስና ራስ ተፈሪያን እንቅስቀቃሴን አራማጅ የነበረ

‹‹ዓለምን መለወጥ ከፈለክ ብዕርህን አንሳና ጻፍ!››

እውቁ የነጻነት ታጋይ ማርቲን ሉተር ኪንግ


አንደኛ ዓመት ቅጽ 1. ቁጥር 5

ነገረ-ኢትዮጵያ ጋዜጣ ጥር 2006 ዓ.ም ተመሰረተች፡፡ ነገረ-ኢትዮጵያ በሰማያዊ ፓርቲ አሳታሚነት የምትታተም ፖለቲካዊ፣ ወቅታዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮችን የምትዳስስ በየሳምንቱ አርብ የምትወጣ ጋዜጣ ናት፡፡

ጋዜጣዋ ሚዛናዊና ነጻ ሆና የማገልገል መርህ አላት፤ ማንኛውም ሀሳብ በነጻነት የሚስተናገድባትና የሚንሸራሸርባት እንድትሆን እንፈልጋለን፡፡ ገዥው ፓርቲም ቢሆን አቋሙንና ፖሊሲውን ለመግለጽ ቢፈልግ የሰፊ ሚዲያ ባለቤት ነው ብለን ዕድሉን አንነፍገውም፤ በራችን ለሁሉም ክፍት ነው፡፡



የአሳታሚ አድራሻ:- የካ ክ/ከተማ ቀበሌ 09/10

ቤት ቁ.460

E-mail:- info@semayawiparty.org

P.O.Box: 180298

ዋና አዘጋጅ

ጌታቸው ሺፈራው

የካ ክ/ከተማ ቀበሌ 01/02

ቤት ቁ. 07/859/14

E-mail:-gecholink@gmail.com

ስልክ ቁጥር:- 09-10-45-99-32

ምክትል ዋና አዘጋጅ

በላይ ማናዬ

የካ ክ/ከተማ ቀበሌ 01/02

ቤት ቁ.099

E-mail:- belaymb@gmail.com

ስልክ ቁጥር:-09-20-19-09-72

አምደኞች

ፐ/ር አለማየሁ ገ/ማርያም

ታዴዎስ ታንቱ

ታምራት ታረቀኝ

አፈወርቅ በደዊ

እያስፔድ ተስፋዬ

ሕትመትና ክትትል

ሳሙኤል አበበ

0913 98 46 40



አታሚ፡ ኪሃራኢ ህትመትና ማስታወቂያ

0921881755



በዚህ ጋዜጣ ላይ የሚወጡ ማንኛውም ፅሁፎች ማተሚያ ቤቱን አይመለከቱም

# መዝሙረ ኢህአዴግ !



በላይ ማናዬ

ፊር መያዣ...

በዚህ ጽሑፍ መዝሙር የሚለውን የቃሉ ፍቺ በተለመደው መልኩ አንዘምርበትም፡፡ የመዝሙር ይዘትንም አናነሳም፡፡ እንደ ልከኛ ፍቺውና ባህሪውም መዝሙሩ መንፈሳችንንና አካላችንን ዘና እንዲያደርገን አይጠበቅም፡፡ የዚህኛው መዝሙር በተደጋጋሚ ሳንፈቅድ እንድንሰማው፣ ሰምተንም በግድ እንድንቀበለው ከመደረጉ የተነሳ አሰልቺ የሆነው ‹‹መዝሙር›› ነው፡፡ ይህን ፊር ይዘን እንዲህ እንቀጥል፡-

በተለያየ ጊዜ በሀገራችን ላይ የተለያዩ ስርዓታት በገዥነት ሲፈራረቁ አንዳቸውን ከአንዳቸው መለየት የሚያስችል ባህርያት አይተንባቸዋል፤ እያየንባቸውም ነው፡፡ እንዳለመታደል ሆኖ ግን የሁሉም ስርዓታት ተመሳሳይነት አምባገነንነታቸው ላይ ያረፈ ነው፡፡ ስርዓታቱ በየዘመናቸው ከብዙዎቹ የስርዓቱ ሰዎች አፍ የማይጠፉ የመወነጃጀያ ወይም የመወዳደሻ፣ የይሄን ሰራሁ፣ ያንኛውን ግን አደናቀፉብኝ አይነት ገለጻዎችን ሰምተናል፡፡ እነዚህን ገለጻዎች የስርዓታቱ መለያ መዝሙሮች ልንላቸው እንችላለን፡፡ አንዳንዶቹ በግለሰቦች (በመሪዎች) ሌሎቹ ደግሞ ግለሰቦችንም ቡድኖችንም ነጥለው አልያም አጣምረው ‹ለዝማሬ› ተጠቅመውባቸዋል፡፡

በንጉሰ ነገስቱ ዘመን አጼውንና የአጼውን ቤተሰቦች የሚያወድሱ ንግግሮች (ዝማሬዎች) የበዙ ነበሩ፡፡ በተቃራኒውም ንጉሱን የሚቃወሙ አካላትን ለማጥላላትና ለማጥቃት ጥቅም ላይ የዋሉ አገላለጾች እንደነበሩ ይታወሳል፡፡ በወታደራዊው ደርግ ጊዜ ደግሞ የራሱ የሆነ ከፍ ያለ ዝማሬ ሊመጣ ችሏል፡፡ በተለይ ደርግ ከኢህአፓ እና ከታጣቂ ቡድኖች ጋር በነበረው ትንቅንቅ የተለያዩ መዝሙረ ደርግ መቀመር ችሎ ነበር፡፡ በእርግጥ ደርግ ሁለት ዋና ዋና መዝሙሮች ይበልጥ መዝሙረ ደርግ ‹‹ያለምንም ደም፣ ኢትዮጵያ ትቅደም!›› የሚለው እንደነበር ይታወቃል፡፡ ዳሩ ግን ስርዓቱ የሚዘምርለትን አብይ ጉዳይ ረስቶ ኢትዮጵያን ደም በደም አድርጎ፣ ሐገሪቱን ከማስቀደም ይልቅ ጭራሹን ወደ ኋላ ሊጎትታት ቻለ፡፡

## መዝሙረ ኢህአዴግ!

ኢህአዴግ በየጊዜው እንደ ሁኔታውና እንደ ተቀናቃኞቹ መልክ እየቀያየረ የተጠቀመባቸው መዝሙሮች በርካታ ናቸው፡፡ መዝሙረ ኢህአዴግ ከሌሎችም የቀደሙ ስርዓታት መገለጫ መዝሙሮች በበለጠ አሰልቺ ሳይሆን አይቀርም፡፡ ከደርግ ውድቀት አንስቶ እስከ አሁን ድረስ የከባቢውን ሙቀት እየለካ አዳዲስ መዝሙሮች መልቀቁንም ገፍቶበታል፡፡ ኢህአዴግ ሲዘምር ስለሌሎች በዙሪያው ስላሉ አካላት ግድ የሚሰጥ አይደለም፡፡ የመዝሙሩ ቃና እንዴት እንደሆነም ሰሚዎችን (የሚያዳምጡትን አላልኩም) መለስ ብሎ አይጠይቅም፡፡

ኢህአዴግ ደስ ካለው የያዘውን መዝሙር ይገፋበታል፤ አዲስ ድርሰት እስኪደርስ ድረስ! ደስ ካላለው ደግሞ ከመቅጽበት በአንድ ጀምበር ዝማሬውን ከግዛቱ ዓመታት ‹በጽናት› ሲያዘምሩ የነበሩት መለስ ዜናዊ ሲያልፉ ለራሳቸው ተዘመረላቸው፡፡ በዚህም ከመለስ ህልፈት በኋላ ያለው መዝሙረ ኢህአዴግ መለስን በማወደስ ላይ ያተኮረ ሊሆን ቻለ፡፡ በአጭሩ መዝሙረ መለስ ተፈበረከ፡፡ በዚህም የሁሉም ነገር አድራጊ፣ ፈጣሪ ‹‹ባለራዕይ፣ መሐንዲስ፣ የዘመኑ ታላቅ መሪ...) መለስ እንደነበሩ የሚያቀነቅን መዝሙረ ኢህአዴግ የኢትዮጵያን ጆሮ አደነቆረ፡፡)

በመጀመሪያዎቹ የኢህአዴግ የስልጣን ዓመታት ወቅት በስፋት ይዘመር የነበረው መዝሙረ ኢህአዴግ ከበረሃ ጀምሮ እንደ ጠላት ሲቆጥረው የነበረውን ብሄር ነጥሎ ከማዳከም ጋር የተያያዘ ነበር፡፡ በዚህም ጠላት ብሎ የፈረጀውን አካል ከድሮው ስርዓት ናፋቂነት እያገናኘ ማጥቃቱ አልቀረም፡፡ ባለጊዜዎቹ ‹ትምክህተኛ›፣ ‹ጠባብ›፣ ‹ርዝራዥ› ወዘተ. የሚሉትን መዝሙሮች ከላይ በተቀመጠው ሰው አውራጅነት እየተቀባበሉ በመዘመር ዕኩይ አላማቸውን ለማሳካት ደፋ ቀና ብለዋል፡፡ የዚህ መዝሙረ ኢህአዴግ የከፋው ክፋት ህዝብን እርስ በዕራሱ በማወነጃጀል ጠላትና ወዳጅ ተባብሎ በጥርጣሬ እንደሚገልጹት መረዳት ይቻላል፡፡ አንደኛው ካለፈው የንጉሱ ስርዓት የተረፉ አካላትን ለመምታት የተጠቀመበት መዝሙር ሲሆን፣ ሌላኛው ደግሞ ቀደም ብሎ የተጠቀሱት ኢህአፓና የወቅቱ ታጣቂ ቡድኖችን ለማጥፋት የተጠቀመበት ናቸው፡፡

ከ‹‹አቆርቋዥ›› እስከ ‹‹ወንበዴ››፣ ከ‹‹ገንጣይ፣ አስገንጣይ›› እስከ ‹‹የእናቱን ጡት ነካሽ››፣ ከ‹‹ጨቋኝ›› እስከ ‹‹መሐል ሰፋሪ››...በደርግ ዘመን ጥቅም ላይ መዋል የቻሉ የመምቻ መዝሙሮች ነበሩ፡፡ (‹የፍየል ወጠጤ›ን እዚህ ጋር ማንሳት የፈለጋችሁ ከራሳችሁ አውድ ጋር አንሱት፡፡) በሌላ በኩል ደግሞ ደርጉ ራሱን ያወድስበት የነበረው አድማስ እስከ አድማስ ያቆመዋል፡፡ የኢህአዴግ ድምጽ አንድ ነው፡፡ ከላይ የሚገኙት ሰውዬ የዘመሩት ያላንዳች ከሁኔታውና ከአካባቢው ነባራዊ ሁኔታ ጋር መዛመድ (አሁን በህይወት ስለሌሉ አዲስ ዝማሬ መውጣቱን አቁሟል) እንዳለ እስከ ታችኛው ተቀባይ ድረስ ይዘመራል፡፡ ዝማሬው ገብቶት መዘመር የሚባል ነገር ኢህአዴግ ውስጥ ብርቅ ነው፡፡ ሰውዬው ያሉትን ተከትሎ መዘመር ብቻ በቂ ይመስላል፡፡ በዚህም ምክንያት መዝሙሩ እጅጉን ፈጥኖ እጅ እጅ የማለት ዕጣ ፈንታ ይገጥመዋል፡፡

(የአብዛኞዎቹ መዝሙረ ኢህአዴግ ደራሲ የነበሩትና ሁሉንም ኢህአዴጎች ለበርካታ እንዲተያይ የሚያደርግ መርዝ በውስጡ መያዙ ነው፡፡

በዚህ መዝሙሩ ኢህዴግ ያተረፈው ነገር ነበር ከተባለ ታሪክንና የሰው ልጆችን የባህልና የቋንቋ ልዩነቶች በማራገብ የከፋፍለህ ግዛ ዘመኑን ማራዘም ነው፡፡ ከዚህም ባለፈ ኢህአዴግ የኢትዮጵያዊነትን ስሜት በማኮሰስ ኢትዮጵያዊያን አንድ የሚያደርጓቸውን የጋራ እሴቶች በመተው ወደ ብሄርና ሐይማኖት ቡድን እንዲወርዱ ለማድረግ መዝሙሩ ጥቂት ፍሬ ሳያፈራለት አልቀረም፡፡ ይህ መዝሙረ ኢህአዴግ ዜጎችን ከመከፋፈሉም በተጨማሪ ለስርዓቱ አስጊ ይሆናሉ የተባሉ በኢትዮጵያዊ አንድነት የሚያምኑ ኃይላትን ለመምታት አገልግሎታል፡፡ ኢትዮጵያዊነትን በኩራት ይዞ ስለአጠቃላይ የሐገር ጥቅም ማሰብ እንደ የድሮው ስርዓት ናፋቂነት ተወስዶ ለጥቃት እንደሚያጋልጥ ለማስጠንቀቅ ውሏል፣ ብሄር ተኮር መዝሙረ ኢህአዴግ፡፡

ይህ ቀጥታ ከሩሲያው አምባገነን መሪ ሌኒን የተቀዳው የብሔር ተኮር መዝሙረ ኢህአዴግ በጋራ ሊያስማማ የማይችል ትርጓሜን በመውለድ ብዙዎቹን ግራ ማጋባትም ችሏል፡፡ ብሄር፣ ብሄረሰብና ህዝብ የሚለው ትርጓሜ ግልጽነት የጎደለውና ግራ አጋቢ ሆኖ ዛሬም ድረስ እንደቀጠለ ይገኛል፡፡ በእርግጥ በኢፌዲሪ ህገ-መንግስት አንቀጽ 39 (5) ላይ እንዲህ የሚል ተጽፎ ይገኛል፤ ‹‹ብሄር፣ ብሄረሰብ፣ ህዝብ› ማለት ሰፋ ያለ የጋራ ጠባይ የሚያንጸባርቅ ባህል ወይም ተመሳሳይ ልምዶች ያላቸው፣ ሊግባቡበት የሚችሉበት የጋራ ቋንቋ ያላቸው፣ የጋራ ወይም የተዛመደ ህልውና አለን ብለው የሚያምኑ፣ የስነ-ልቦና አንድነት ያላቸውና በአብዛኛው በተያያዘ መልክዓ ምድር የሚኖሩ ናቸው፡፡››

**ለመሆኑ <<. . . የጋራ ወይም የተዛመደ ህልውና አለን ብለው የሚያምኑ . . . >> ማለት ምን ማለት ነው? ኢትዮጵያዊያን ሁሉ የጋራ ወይም የተዛመደ ህልውና የለንም ማለት ነው እንዴ? በዚህ ትርጓሜ መሰረትስ <ብሄር> ማን ነው? <ብሄረሰብስ> የትኛው ነው?**

እዚህ ጋ አንድ ጥያቄ ብቻ እናንሳ፡፡ ለመሆኑ ‹‹...የጋራ ወይም የተዛመደ ህልውና አለን ብለው የሚያምኑ...›› ማለት ምን ማለት ነው? ኢትዮጵያዊያን ሁሉ የጋራ ወይም የተዛመደ ህልውና የለንም ማለት ነው እንዴ? በዚህ ትርጓሜ መሰረትስ ‹ብሄር› ማን ነው? (ብሄር ማለት ሐገር ማለት እንደሆነ ከግዕዝ ቋንቋ የወረስነው ትርጓሜ ይነግረናል፡፡) ‹ብሄረሰብስ› የትኛው ነው? ‹ህዝብስ›? ለእነዚህ ጥያቄዎች መልስ መስጠት የሚችል ዘማሪ ኢህአዴግ ያለ አይመስለኝም፡፡ እናም አውራጆቹ ራሳቸው በትክክል ሳይገባቸው ተቀብለው ሌላውም ሳይገባው እንዲቀበለው በማድረግ ረጅም ጊዜ ዝማሬ ላይ ያለው መዝሙረ ኢህአዴግ ይሄኛው ሳይሆን አይቀርም፡፡

ሌላው መዝሙረ ኢህአዴግ የምርጫ ወቅትን እየቆጠረ የሚፈበረከው ጫጫታና ፍረጃ ላይ ያተኮረው ነው፡፡ ከዚያ በፊት ያሉትን ትተን እንኳ በምርጫ 97 ጊዜ ብቻ የነበሩትን መዝሙረ ኢህአዴጎች ለማስታወስ እንሞክር፡፡ ምርጫ 97 ሲነሳ ወጣቱና ኢህአዴግ ክፉኛ የተፋጠጡበትን አጋጣሚ ማስታወስ ግድ ይለናል፡፡ ይኸውም የሆነው በወጣቶች ላይ ያነጣጠረው መዝሙረ ኢህአዴግ ከተደረሰ በኋላ ነበር፡፡ ስራ አጥተው በችግር ላይ የነበሩትን ወጣቶች ኢህአዴግ ‹‹አደገኛ ቦዘኔዎች›› የምትል መዝሙር ሲያቀነቅንባቸው የወጣቶች ቁጣ ገነፈለ፡፡ ይህ የተቆጣ ወጣት በጊዜው አይነተኛ ተቃዋሚ ፓርቲ ወደነበረው ቅንጅት ተመመ፡፡ ወጣቶቹ ፈጣኖች ነበሩ፤ እነሱን አስመልክቶ መቀንቀን ለጀመረው መዝሙረ ኢህአዴግ አጸፋ ሰጡ፤ ‹‹ስራ አጥ በመሆኔ፣ ተባልኩኝ ቦዘኔ›› እያሉ ኢህአዴግን ፊት

ወደ ገፅ 6 ይዞራል

የሰማያዊ ፓርቲ ሊቀመንበር የሆኑት ኢንጅነር ይልቃል ጌትነት ከአሜሪካ መንግስት ስቴት ዲፓርትመንት በተደረገላቸው ግብዣ ወደ አሜሪካ ያመራሉ፡ ፡ በጉዞው ዓላማና በተለያዩ የአገራችን ፖለቲካዊ ጉዳዮች ዙሪያ ከጋዜጠኛ ጌታቸው ሺፈራው ጋር ቆይታ አድርገዋል፡፡

# ‹‹ለውጡ እንደቀረበ ጥርጥር የለኝም››

## ኢ/ር ይልቃል ጌትነት፣ የሰማያዊ ፓርቲ ሊቀመንበር



ነገረ-ኢትዮጵያ፡- ከሁለት ወር በፊት ወደ አሜሪካና የአውሮፓ አገራት ለስራ ጉብኝት ሄደው ነበር፡፡ አሁንም ወደ አሜሪካ ጉዞ ሊያደርጉ እንደሆነ ሰምቻለሁ፡፡ የአሁኑ ጉዞ አላማ ምንድን ነው?

ኢንጅነር ይልቃል፡- መጀመሪያ ያደረኩት ጉዞ የሰማያዊ ፓርቲ አባላትና ደጋፊዎች የፓርቲውን አላማና ፕሮግራም፣ የሰራናቸውን እንዲሁም ወደፊት ልንሰራቸው ያሰብናቸውን ስራዎች፤ ሰማያዊ እንደ አዲስ ኃይል ሲመጣ የቆመላቸው ሀሳቦችና እምነቶች ምን እንደሆኑ ለማስተዋወቅ ታስቦ የተደረገ ነበር፡፡ የአሁኑ ግን ከበፊቱ የተለየና ለሰማያዊ ሊቀመንበር በሚል በቀጥታ በአሜሪካ መንግስት ስቴት ዲፓርትመንት የተደረገ ግብዣ ነው፡ ፡ የአሁኑ ወጣት የአፍሪካ መሪና ወደፊትም ለአገራቸው መሪ ሊሆኑ የሚችሉ፣ በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ጥሩ ስራ የሰሩ፣ በውድድር ከተመረጡ በኋላ በአሜሪካ መንግስት ስቴት ዲፓርትመንት በሚደረግ ምርጫ መመዘኛዎቹን ለሚያሟሉ ሰዎች የሚሰጥ እድል ነው፡፡ በመመዘኛዎቹ መሰረት በማሸነፌ የአሜሪካ መንግስት ሙሉውን ወጭ ሸፍኖ ለሶስት ሳምንት በአሜሪካ የመንግስት አወቃቀርና ዴሞክራሲን ጨምሮ በተግባር የሚሰጡ ስልጠናዎችን የማግኘትና፣ የአሜሪካ መንግስት ባለስልጣናትም ባሉበት ከተለያዩ ተቋማት ጋርም ለመገናኘት እድል ይኖረኛል፡፡

ነገረ-ኢትዮጵያ፡- ከሌሎች የአፍሪካ አገራት የፖለቲካ መሪዎች ጋር ተወዳድረው ነው ያሸነፉት ማለት ነው?

ኢንጅነር ይልቃል፡- አዎ! ግን ሌሎች ያሸነፉ ተጨማሪ ሰዎች ይኑሩ አይኑሩ አላውቅም፡፡ ይህ የፕሬዝዳንቱም ‹ኢኒሸቲቭ› ይመስለኛል፡፡ ለእኔ ግን የተሰጠኝ አዲስ ትውልድ አመራሮች፣ ወደፊትም በአገራቸው መሪ መሆን የሚችሉ፣ ስትራቴጅካሊ የሚያስቡ፣ በአስቸጋሪ ሁኔታ ላይም ሆነው መልካም ስራ ለሰሩ ሰዎች የሚሰጥ ልዩ የጉብኝት እድል ነው፡፡ በአጠቃላይ ውድድርም ተደርጎ የሚወሰድ ነው ማለት ይቻላል፡፡

ነገረ-ኢትዮጵያ፡- የአሜሪካ መንግስት ይህንን እድል ሲሰጥ እርስዎ እንደ መሪም ሆነ ሰማያዊ እንደ ፓርቲ ያሸነፋችሁበትን ዋና ዋና መመዘኛዎች ነግረዋችኋል?

ኢንጅነር ይልቃል፡- ሲመርጡኝ ዝርዝር መረጃዎችን ወስደዋል፡ ፡ መሰረታዊ የሚባሉትን ለምሳሌ ያህል የፖለቲካ ቆይታዬ፣ የትምህርት ዝግጅቴን፣ በፖለቲካው ውስጥ የነበረኝን ተሳትፎ የመሳሰሉትን መረጃዎች ለእጩነት በቀረብኩበት ወቅት ከእኔ ወስደዋል፡፡ ከዛ በኋላ ያስመረጠኝን ዝርዝር መስፈርት አላውቅም፡፡ ነገር ግን ወጣት (እስከ 45 አመት ባለው ውስጥ)፣ በአስቸጋሪ ሁኔታ መልካም ስራ የሰራ፣ ወደፊትም የአገሩ መሪ ሊሆን የሚችል የሚሉት ዋና ዋና መመዘኛዎች እንደሆኑ አውቃለሁ፡ ፡ ይህም በተለይ ከሰማያዊ አንጻር ከሁለት ነገሮች አኳያ እንድናየው ያደርጋል፡፡ አንደኛው በምስራቅ አፍሪካ ያለውን ፖለቲካና እስካሁን ጠቅልሎ የያዘው ኢህአዴግ ነበር፡፡ ሌላ አማራጭ እንደሌለ አድርጎ ነበር የሚያየው፡፡ ሆኖም እንደዚህ አይነት እድል እንደ አሜሪካ ባለ ትልቅ መንግስት የተቃዋሚ መሪ የተለየ ስራ ሰርቷል ተብሎ ሲጋበዝ ሰማያዊ ፓርቲ አዲሱንና ወደ ፖለቲካ ያልመጣውን ትውልድ ወደ ፖለቲካው ለማምጣት በሚያደርገው ጥረት እንደ አንድ ማበረታቻ ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል፡፡ ይህ በሌሎች መስኮች ከምናደርጋቸው የዲፕሎማሲ ስራዎች በተጨማሪ ለሰማያዊ ፓርቲ ከሌሎች ፓርቲዎች በተለየ ይህኛው ግብዣ ሲደረግለት ለሁለተኛ ጊዜ ነው፡፡

ከአሁን በፊት ለሰማያዊ ፓርቲ ሊቀመንበር በአሜሪካ ኤምባሲ ውስጥ የ35 አገራት ኤምባሲዎች የ‹ኢትዮጵያ ፓርትነርስ ግሩፕ› የሚባለው ሲደረግ በአመታዊ ስብሰባቸው ላይ ዋና ተናጋሪ ሆኜ ስለ ኢትዮጵያ ፖለቲካና ስለ ሰማያዊ ፓርቲ ዋና የትግል እንቅስቃሴና የወደፊት አላማችን እንዳስረዳ የተለየ እድል ተሰጥቶኛል፡፡ ይህም ለፓርቲው ሌት ተቀን ለሚሰሩ ወጣቶች፣ እንዲሁም ሁል ጊዜም ቢሆን ወጣቱ ተከታይና ጀሌ እግረኛ ከመሆን አልፎ ራሱ ኃላፊነት የሚወስድ፣ መምራትና የራሱን መሪዎች ማውጣት የሚችል ትውልድ መምጣቱን የሚያሳይ መልካም ጅምር ነው፡፡

ነገረ-ኢትዮጵያ፡- የአሜሪካ መንግስት ከ9/11 እንዲሁም ከ1997 ዓ.ም ምርጫ በኋላ ሶማሊያ ውስጥ ባለው ጥቅም ኢህአዴግ ላይ እስከመጨረሻ ግፊት ማድረግ አልቻለም ነበር፡፡ አሁን ለእርስዎና ለፓርቲዎ ይህን እድል ሲሰጥ ለኢህአዴግ የሚያስተላልፈው መልዕክት ምንድን ነው? የተቃውሞ ጎራውም ቢሆን እስካሁን የሚመራው በ1960ዎቹ ፖለቲከኞች ነው፡፡ አሁን የአሜሪካ መንግስት ይህን እድል ለእርስዎ እንደ መሪና ለሰማያዊ እንደ ወጣት ፓርቲ ሲሰጥ ለኢትዮጵያ ፖለቲካ የሚኖረው አንድምታ ምንድን ነው?

ኢንጅነር ይልቃል፡- እንግዲህ ይህን ጉዳይ ህዝቡም ሆነ የዓለም አቀፍ የፖለቲካ ማህበረሰቡ እየተረዳው የመጣ ይመስለኛል፡፡ ባለፈው አርባ አመት በገዥውም ሆነ በተቃዋሚው ያለው በአንድ አይነት እድሜና የግራ ርዕዮት የሚሽከረከር ነበር፡፡ ይህም የኢትዮጵያን ፖለቲካም ሆነ ኢትዮጵያን በሁሉም መመዘኛዎች ወደ ፊት ሊያራምድ አልቻለም፡፡ እንዲያውም ጥላቻ፣ ቂምና ቁርሾ፣ የእስር በእርስ መጠላፍና የዜሮ ድምር ፖለቲካ ሆኖ ቆይቷል፡ ፡ ያ ትውልድ ያላመጣውን ውጤትም ወጣቱ ያመጣዋል የሚል ነው፡ ፡ ኢትዮጵያ የወጣት አገር ነች፡፡ 70 ከመቶ የሚሆነው ከ35 አመት በታች ነው፡፡ ይህ የህብረተሰብ ክፍል በውክልና ደረጃም ሆነ አዲስ አስተሳሰብና ከበድ ያለ ነገር ይፈልጋል፣ ከዓለም ከተለያየ አቅጣጫ መረጃ ያገኛል፣ በአስተዳደጉም አንጻራዊ ነጻነት አለው፣ በአመለካከትም ቢሆን ይህ የህብረተሰብ ክፍል ወደ ፊት እየመጣ ነው፡፡ ከዚህም አንጻር በታክቲክም ሆነ በአመለካከት ይህን የህብረተሰብ ክፍል መደገፍ የሚያዋጣና አይቀሬነቱን የሚያሳይ ይመስለኛል፡፡

ዋናው የኢህአዴግ የፖሊሲ መሰረት ማታለል ነው፡፡ ‹‹እኔ ከሌለሁ ኢትዮጵያ ትበታተናለች፡፡›› በሚል የምስራቅ አፍሪካንም ሆነ የሶማሊያን የሽብር ሁኔታ እንደ ማታለያ እየተጠቀመ፤ እነሱ የስጋት ፖለቲካ ውስጥ መግባታቸውን ስለሚያውቅ እሳት የማጥፋት ስራ ነበር የሚሰራው፡ ፡ ይህ ግን መሰረታዊ መፍትሄ የሚያመጣ ሳይሆን ነገሮችን እያዳፈነ፣ ችግሩን እያባባሰ በመሆኑ እንዲሁም የጠቅላይነት ፖለቲካን ለቀጠናውም ሆነ ለኢትዮጵያ እየጠቀመ አለመሆኑ የዓለም አቀፍ የፖለቲካ ኃይሎች ተረድተውታል፡፡ አማራጭ የፖለቲካ ኃይልና መሰረታዊ የሆኑ የዴሞክራሲ መመዘኛዎችን ማምጣት፣ መሰረታዊ የሆኑ የዜጎች ልማትና ዴሞክራሲ ማፋጠን፣ በአቻነት የተመሰረተ ግንኙነትን ካልሆነ በስተቀር በጉልበትና በጠብመንጃ የሚደረገው አገዛዝ እንደማያዋጣ የተረዱበት ጊዜ ነው፡፡ አሜሪካኖች አባቶቻቸው የሞቱበት ነገር (the ideals of ower founding fathers) የሚሉት የሰውን ልጅ መብትና የሰብአዊ መብት ማክበር ለሁሉም አገራት መድሃኒት መሆኑን ራሳቸው አፍጋኒስታንና ኢራቅ ውስጥ በነበሩበት ወቅት አይተውታል፡፡ በየመን፣ በምስራቅ አፍሪካዋ ሶማሊያም ቢሆን ተመሳሳይ የእሳት ማጥፋት ፖለቲካ ለውጥ እንዳላመጣ ተገንዝበውታል፡፡ በየ ደረጃው በህዝብ ተሳትፎ የሚያድግ ዴሞክራሲና በዜጎችም ይሁን በአገራት መካከል በእኩልነት ላይ የተመሰረተ ግንኙነት መምጣት ካልቻለ አፋኝነት እንዳልጠቀመ የተረዱበት ጊዜም ይመስለኛል፡፡

ነገረ-ኢትዮጵያ፡- እስካሁን ድረስ ዲያስፖራውም ሆነ አገር ውስጥ ያው የተቃውሞ ኃይል ድምጹን ለማሰማት ሲሞክርም የዓለም አቀፍ ማህበረሰቡ ትኩረት አናሳ እንደነበር ይታወቃል፡፡ እናንተ ይህንን አጋጣሚ ስታገኙ ዓለም አቀፍ ማህበረሰቡ በስርዓቱ ላይ ትኩረት እንዲሰጥ በአጽንኦት የምታስረዱት ምንድን ነው?

ኢንጅነር ይልቃል፡- አንደኛ ከመንግስት ጋር መስራት በሚሉት መርህ ላይ ኢህአዴግ ስልጣን ስላለው ብቻ በአጭር ጊዜ የጮሌነት ግንኙነት፣ ከዛም በኋላ ለአሸነፊውና የኃይል ሚዛኑ ካደላው ጋር ግንኙነት የማድረግ ዋናው የዘመኑ መገለጫ፣ ስግብግብነትን መሰረት ያደረገ የካፒታሊዝም መርህ ስለሆነ በየትኛውም መንገድ ተሂዶ የአገርን ጥቅም ማስጠበቅ የሚባለው እንደማይጠቅም ማስረዳት እንፈልጋለን፡፡ መንግስት ቢያልፍም በህዝብ ላይ የሚደርሰው በደልና ግፍን እያዩ እንዳላዩ ማለፍ ለዘላቂ የአገራቸው ጥቅም እንደማይበጅ፣ ሁል ጊዜም ቢሆን ግንኙነት መመስረት ካለበት ከአገሪቱና ከአገሪቱ ህዝብ ጋር እንደሆነ፣ ግንኙነቱ ታሪካዊና የህዝብን መሰረታዊ መብቶች ጠብቆ የሚደረግ እንጅ ከአንድ ቡድን ጋር የሚደረግ ግንኙነት ኢትዮጵያን ለመሰለ ታሪክና ክብሩን ለሚወድ ህዝብ ውሎ አድሮ የማይጠቅም መሆኑን፣ በአጠቃላይም የኢትዮጵያ የዴሞክራሲ፣ መሰረታዊ መብቶችና ሀሳቦች በሚከበርባቸው መልኩ የሚያራምድ አይነት አስተሳሰብን መሰረት ያደረገ ግንኙነት እንዲያደርጉ ነው በዋነኛነት ማሳሰብ የምንፈልገው፡ ፡ ከአንድ ቡድን ጋር የሚደረግ የአጭር ጊዜ ግንኙነት ራሳቸውንም እንደሚጎዳቸው፣ በቀጠናው ይገኛል የሚባለውን መረጋጋትና ሰላምም ሊያመጣ እንደማይችል እንዲረዱት እንፈልጋለን፡፡

ነገረ-ኢትዮጵያ፡- ይህን አጋጣሚ በመጠቀም ከዲያስፖራው ጋር በመገናኘት የምትሰሩት ሌላ ድርጅታዊ ስራስ ይኖር ይሆን?

ወደ ገፅ 13 ይዞራል

**እንደ ኢትዮጵያ አይነት በዓለም የመጨረሻ ድሃ ለሆነ፣ ብዙ የጎሳና የእምነት መቃቃር በተፈጠረበት አገር፣ በሩቅም በቅርብም የኢትዮጵያን መረጋጋት የማይወዱ አካላት ባሉት ቀጠና ላይ ሆነን፣ እርስ በራሳችንም በተለያዩ የታሪክ ግጭቶች ውስጥ እያለን እንዲህ አይነቱ ለውጥ ባይኖር ደስ ይለናል፡፡ ነገር ግን አልፈለግነውም ማለት አይከሰትም ማለት አይደለም፡፡ ሰማያዊ ፓርቲ እንዲህ አይነት ጉዳይ እንዳይከሰት የተጠና፣ አስቀድሞ በድርጅቱ የተመራ፣ ኃላፊነት በተሞላበት መልኩ የሚካሄድ የስልጣን ሽግግር እንዲኖር ሌት ተቀን ይሰራል**

# ኢትዮጵያና የዩክሬኑ ግጥምጥሞሽ

## • ባለ ቀለሙን አብዮት ማን ይመራዋል?



ጌታቸው ሺፈራው

እ.ኤ.አ ከ1991 ዓ.ም በኋላ ያለው ጊዜ ለአያሌ ህዝቦች የዴሞክራሲ ጭላንጭል የታየበት ነው፡፡ የዓለምን ኃያልነት ለመያዝ ከአሜሪካ ጋር ስትወዳደር የነበረችውና የአምባገነኖች መከታ የነበረችው ሶቬት ህብረት ለራሷም ሳትሆን ስትፈረካከስ ስልጣን ላይ የቀሩት ዴሞክራሲያዊ ስርዓትን መላመድ የግድ ሆኖባቸዋል፡፡ ሆኖም ብዙዎቹ ለይስሙላህ እንጂ ዴሞክራሲያዊ ስርዓትን ባለመመስረታቸው ለስም ህጋዊ ስርዓት መሰረትን ብለው በተግባር አምባገነንነታቸውን መተው አልቻሉም፡፡ በተለይ ምርጫ ማጭበርበር፣ ሰብአዊ መብት ጥሰት፣ ሙስና እና ሌሎቹ ተግባሮች ቀጥለዋል፡፡

በተቃራኒው ህዝብ ከድሮው በተሻለ ህጋዊ መሰረት ማግኘቱ፣ ከምዕራቡ ዓለም ጋር የነበረው ግንኙነት፣ የምዕራባውያን አገራትና ድርጅቶች ግፊት እና እንደ ኢንተርኔት ያሉ አዳዲስ አጋዥ ጉዳዮችን ተጠቅሚ መሆናቸው በስርዓቶቻቸው ላይ ጠንካራ ተቃውሞ እንዲያነሱ አስችሏቸዋል፡፡ በተለይ እ.ኤ.አ ከ2000 ዓ.ም ጀምሮ በርካታ አብዮታዊ እንቅስቃሴዎች ተደርገዋል፡፡ እነዚህ እንቅስቃሴዎች በሲቪሎች የተደረጉ ሲሆኑ የንቅናቄው አባላት አንድነት ለመፍጠር የራሳቸው የሆነ ቀለምን ተጠቅመዋል፡፡ አንዳንዶቹ ደግሞ የፓርቲዎች መለያና ባለ ቀለም ስሞች በመውሰድ ተጠቅመውበታል፡፡ ይህንንም የቀለም አብዮት ይሉታል፡፡ በእርግጥ ሚዲያው ሰፊ ሽፋን የሰጠው ከ2000 በኋላ ያለውን ቢሆንም እንቅስቃሴው የተጀመረው ከ1991 ዓ.ም በፊት መሆኑ ይነገርለታል፡፡

ለአብነት ያህል እ.ኤ.አ በ1986 ፊሊፒንሳውያን ተደጋጋሚ የሰላማዊ ትግል ካደረጉ በኋላ ያሳኩት አብዮት ብጫው አብዮት ብለው ጠርተዋል፡፡ ቡልጋሪያ እ.ኤ.አ በ1997፣ ስሎቫኪያ በ1998፣ ክሮሺያ በ2000ና ሌሎች የይጎዝላቪያ ክፍሎች በ2000 ህዝብን አንድ የሚያደርግ ምልክት በመጠቀም የይጎዝላቪያውን አምባገነኑን አስወግደው ዴሞክራሲያዊ ስርዓትን ለመመስረት ጥረዋል፡፡ ሆኖም በሚዲያዎች ትልቅ ትኩረት ማግኘት የጀመረው እ.ኤ.አ ከ2000 በኋላ ነው፡፡ በተለይ እ.ኤ.አ በ2003 በጆርጅያ የተደረገው የሮዝ አብዮት የሚዲያን ትኩረት የሳበ ሲሆን ከአንድ አመት በኋላ ዩክሬናውያን ያደረጉት ብርቱካናማው አብዮት በበርካታ አገራት እስካሁንም ድረስ በምሳሌነት ይወሰዳል፡፡ ለአብነት ያህል አብዛኛዎቹ የአረብ አገራት ላይ በተሞክሮነት ቀርቧል፡፡ አንዳንዶች በቅርቡ የተደረገውን የአረብ አብዮትም ሎቱስ የተባለ በአረቡ ዓለም የሚዘወተር አበባ ስምና ቀለም ሰይመውታል፡፡

### የቀለም አብዮት የትኛው ነው?

የቀለም አብዮት በአሁኑ ወቅት በፖለቲካ መድረኩ እየተለመደ መምጣቱን ተከትሎ አብዛኛዎቹ እንቅስቃሴዎቹ በዚሁ አብዮት ስም እየተጠሩ ነው፡፡ የቀለም አብዮት እንቅስቃሴው ጉልህ የሆነ ቀለም ኖረውም አልኖረውም ፓርቲዎች ወይንም የአንድ እንቅስቃሴ መሪዎች ህዝብ በቀላሉ በሚግባባበት መንገድ ለማንቀሳቀስ የሚጠቀሙበት የሰላማዊ ትግል ስልት ነው፡፡ ስሙን በቀለም ስም የጠራ፣ የዘመቻውን ስም በአንዳች ቀለም የሰየመም ሆነ ከአሁን በፊት ይህን እንቅስቃሴ ያከናወኑትን አካላት የተጠቀሙበትን የሰላማዊ ትግል ስልት የተጠቀመ ‹‹በቀለም አብዮተኛነት›› ሲሰየም መስማት የተለመደ ሆኗል፡፡ ሉካን ዋይ የተባሉ ምሁሩ ‹‹the real Causes Uses of the Color revolutions›› በሚል ጥናታቸው የቀለም አብዮት ተቃዋሚዎች ኮሚኒስታዊ ባህሪያት ያላቸውን መንግስታትን በሰላማዊ መንገድ የሚዋጉበት ስልት እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡ አጥኚው እንደሚሉት አብዛኛዎቹ የእነዚህ መንግስታት ተቃዋሚዎች በስርዓቱ ላይ ጠንካራ ጫና የሚያደርሱት በምርጫ ወቅት ነው፡፡ ስልቱም ሰላማዊ፣ ስርዓቱን የሚያሳጡ ቀልድና ፌዞችን የሚጠቀምበት፣ የራሳቸውን ምልክት የሚፈጥሩበት፣ በእየ ጎዳናው ድንኳን በመጣል የሚቀመጡበት ስልት ነው፡፡ ይህ ስልት አምባገነኖችን ከስልጣን ለማባረር ፍቱን መሆኑን የሚገልጹት ምሁሩ አሁንም ድረስ ከኮሚኒስት አመለካከታቸው ያልተላቀቁ ስርዓቶች ስልጣን ላይ መኖራቸው የቀለም አብዮትን ውጤታማ አለመሆን አያሳይም ባይ ናቸው፡፡ ይልቁንስ በቅርብ አመታት ጊዜያቸውን እየጠበቁ እንደሆነ ባለሙያው ይጠቅሳሉ፡፡

ቦህዳን ሃራሰይሚው የተባሉ ሌላ አጥኚ ‹‹Ukraine's "Orange Revolution" and Why It Fizzled›› በሚል ስራቸው የቀለም አብዮት ተዋጊና የተለየ ምሁር አያስፈልገውም፡፡ ለዚህም በምሳሌነት የሚጠቅሱት ዩክሬንን ሲሆን በእ.ኤ.አ በ2004 የተደረገው ዩክሬን ብርቱካናማው አብዮት አራማጆች ሙስናን፣ አምባገነንነትን፣ ኢ-ሰብአዊ ድርጊትን፣ የሚቃወሙና ህገ መንግስታዊነት፣ ዴሞክራሲን፣ ሰብአዊ መብትን የሚደግፉ ፖለቲከኞች የመሩት መሆኑን ነው፡፡ ከተዋጊዎች ወይንም በአንድ የርዕዮተ-ዓለም ጽንፍ ላይ ከተቀመጡ ፖለቲከኞች ይልቅ ለአገራቸው ህዝብና ጥቅም የሚቆሙ ጸረ አምባገነን ፖለቲከኞች የመሩት መሆኑም ከንቅናቄው በኋላ በአገሪቱ ሰላም እንዲሰፍን አድርጓል፡፡ እንደ ጥናቱም ዴሞክራሲያዊ ስርዓትን ለመገንባት የተነሱት የብርቱካማው አብዮት አራማጆች በአገሪቱ ዴሞክራሲያዊ ስርዓትን መስርተዋል፡፡

### ኢንተርኔትና የቀለም አብዮት

ማይሮስላው ኪይጂ ‹‹Internet use in Ukraine's Orange Revolution›› በሚል መጣጥፍ ኢንተርኔት ለቀለም አብዮት ዋነኛው መሳሪያ መሆኑን ያሰምሩበታል፡፡፡ እንደ አጥኚው በወቅቱ የዩክሬን ገዥ ፓርቲ ሚዲያውን በሀይልና በሙስና በመቆጣጠር የራሱ ድምጽ በስፋት ከማስተላለፉም በላይ የተቃዋሚዎች ድምጽ እንዳይሰማ አድርጎ ነበር፡፡ ይሁንና በወቅቱ በተለይ የኮሌጅና የዩንቨርሲቲ ተማሪዎች፣ ሌሎች የተማሩ ወጣቶችና ምሁራን ኢንተርኔትን መጠቀም የጀመሩበት ወቅት ስለነበር ለተቃዋሚዎች መልካም አጋጣሚን ፈጥሯል፡፡ በወቅቱ ዓለም አቀፍ ማህበረሰቡና ሚዲያው ለዩክሬን ተቃዋሚዎችና ወጣቶች ያገዘ እንደነበር ምሁሩ ይጠቅሳሉ፡፡ ምንም እንኳ ገዥው ፓርቲ የሚዲያን ፈቃድ በመከልከል፣ ጫና በመፍጠር፣ በኃይል፣ በሙስና በመቆጣጠሩና አላሰራ በማለቱ የተቃዋሚዎች ድምጽ መተላለፍ ባይችልም ኢንተርኔት ግን ገዥ ፓርቲ የነበረበትን ድክመት ለማጋለጥ አዲስ ፋሽን ለመሆን በቅቷል፡፡ በተለይ በሰላማዊ መንገድ ስርዓቱን ሲዋጉ የነበሩትን ወጣቶች ስርዓቱ በአንዱ ጫና ሲፈጥርባቸውና ኢንተርኔትን ላይ ያላቸውን ሚናም ለመቀነስ ሲጥር በሌላኛው በመምጣት የጉሬላ ታጣቂ ኃይል ያህል እንደተዋጉት ይገልጻሉ፡፡ ለስኬቱ አንድ ምክንያት አድርገው የሚወስዱትም ወጣቶቹ በስርዓቱ ላይ ያላቸውን ተቃወውሞ ለመግለጽ ኢንተርኔትን በስፋትና በሚገባው መልኩ መጠቀማቸውን ነው፡፡ ኢራንና አረቦቹም ይህን ስፋት በስፋት ተጠቅመውበታል፡፡

### ዩክሬንና ኢትዮጵያ

ከእኛው 1997 ዓ.ም ምርጫ አንድ አመት ቀደም ብሎ ዩክሬን ውስጥ ምርጫ ተካሂዶ ነበር፡፡ ምርጫውን ብርቱካናማ ቀለምን መለያው አድርጎ የነበረው የተቃዋሚው መሪ ቪክቶር ዩሽቼንኮ አሸንፎ የነበር ቢሆንም ስልጣን ላይ የነበረው ቪክቶር ኑኮቪች የደህንነትና ሎሎች ኃይሎችን በመጠቀም ምርጫውን ያጭበረብራል፡፡ ይህ የዩክሬናውያን ንቅናቄ የተደረገው በአገሪቱ የተደረገውን ምርጫ ተከትሎ ገዥው መንግስት ምርጫውን ማጭበርበሩን ተከትሎ ነው፡፡ ሰላማዊ ንቅናቄው ከታህሳስ አጋማሽ ጀመሮ የዋና ከተማዋን ኬይቭን አደባባይ በመያዝ ለአንድ ወር ቀጥሏል፡፡ ይህ የሆነው የኢትዮጵያው 97 ከመደረጉ አንድ አመት ቀደም ብሎ ነው፡፡ አንድ ወር ከአንድ ቀን የወሰደው የሰላማዊ ሰልፍኞቹ ግፊት ዳግም ምርጫ አስደርጓል፡፡ በስተመጨረሻም የተቃዋሚው ደጋፊዎችም ብርቱካናመውን በቀለምነት በመጠቀም በርካታ ሰላማዊ ተቃውሞዎችን በማድረጋቸው ከአንድ አመት በኋላ ዳግመኛ ምርጫ እንዲደረግ አስገድደውታል፡፡ በምርጫውም ብርቱካማ ቀለምን ተጠቅመው ሰላማዊ ተቃውሟቸውን ሲያደርጉ የነበሩትን ዩክሬናውያን ድጋፍ ያገኘው የተቃዋሚው ፓርቲ ስልጣኑን ከአጭበርባሪው ፕሬዝደንት ተቀብሎታል፡፡

ምንም እንኳ በዩክሬን የነበረው መንግስት የምዕራባዊያንን ተጽዕኖ ለመቀነስ የሩሲያ አሽከር ቢሆንም ከህወሓት/ኢህአዴግ በእጅጉ የተሻለ አገር ወዳድ ነው ለማለት ይቻላል፡፡ አጭበርባሪው ፕሬዝደንት ያለ ግድ በውድ ስልጣኑን ሲለቅ ግን ኃይል አጥቶ አልነበረም፡፡ ይልቁንም ለአገርና ለህዝብ ያዘነ ይመስላል ስልጣኑን ለአሸናፊው ማስረከብ የግድ መሆኑን ሲያስረዳ እንዲህ ነበር ያለው፡፡ ‹‹እኔ እናቶች ልጆቻቸውን፣ ሚስቶች ባሎቻቸውን እንሲያጡ አልፈልግም፡፡ ከኬቭ ወደ ደኒፐሮ አስከሬኖች ሲጎርፉ ማየት አልፈልግም፡፡ ደም አፋስሼ ስልጣን መያዝ አልፈልግም፡፡›› ይህ ለአገሩ የሚያስብ ፖለቲከኛ የሚለው ነው፡፡ ከዩክሬን አንድ አመት በኋላ የእኛው 97 ደም አፋስሷል፡፡ ያሸነፉት ታስረው የተሸነፈ ስልጣን ይዘዋል፡፡ የእኛዎቹ ገዥዎች ‹‹አይደለም 200 ሰው 200 ሺህ ህዝብ ይለቅ፤ ስልጣን ለነፍጠኛ ተላልፎ ከሚሰጥ ኢትዮጵያ ብትንትኗ ይውጣ!›› ነው ያሉት፡፡

እንደ አጋጣሚ ሆኖ ዩክሬንና ኢትዮጵያ ምርጫ የሚያደርጉት በአንድ አመት ልዩነት ነው፡፡ በዩክሬን ምርጫውን ተከትሎ አመጽ ሲቀጣጠል የእኛ 1997 ትልቅ ለውጥ የታየበት ወቅት ነው፡፡1997 ላይ ዳግም ምርጫ አድርጋ 2002 ዓ.ም ላይ ዋናውን ምርጫ ያደረገችው ዩክሬን የተባረረው ፕሬዝዳንት እንደገና ስልጣን ያዘ

ወደ ገፅ 7 ይዞራል

**የቀለም አብዮት እንቅስቃሴው ጉልህ የሆነ ቀለም ኖረውም አልኖረውም ፓርቲዎች ወይንም የአንድ እንቅስቃሴ መሪዎች ህዝብ በቀላሉ በሚግባባበት መንገድ ለማንቀሳቀስ የሚጠቀሙበት የሰላማዊ ትግል ስልት ነው፡፡ ስሙን በቀለም ስም የጠራ፣ የዘመቻውን ስም በአንዳች ቀለም የሰየመም ሆነ ከአሁን በፊት ይህን እንቅስቃሴ ያከናወኑትን አካላት የተጠቀሙበትን የሰላማዊ ትግል ስልት የተጠቀመ < <በቀለም አብዮተኛነት> > ሲሰየም መስማት የተለመደ ሆኗል፡፡**

# መዝሙረ ኢህአዴግ . . .

ከ ገፅ 3 የዞረ

ነሱት፡፡

በዚህ የወጣቶች ምላሽ ኢህአዴግ በኃይል ደንግጦ እንደነበር ይታወቃል፡፡ ይህም ድንጋጤው የወጣቶች ማረፊያ እየሆነ የነበረውን የቅንጅት ፓርቲ በጠላትነት ፈርጆ እንዲዘምር አደረገው፡፡ እናም ሌላ መዝሙረ ኢህአዴግ ተፈበረከ፡፡ ‹‹የቅንጅቱ አመራሮች ኢንተርሃሞይ ናቸው›› የሚል መዝሙረ ኢህአዴግ በማዘጋጀት የቅንጅቱን መሪዎች ከሩዋንዳው የእርስ በእርስ እልቂት ጋር ለማገናኘት የፈጠራ ድር አደራ፡፡

ኢህአዴግ በባህሪው ድንጉጥ ድርጅት ይመስለኛል፡፡ አንድ ጠንከር ያለ ተቃውሞ ሲገጥመው ድንብርብሩ ሲወጣ ይታያል፡፡ በዚህም የተነሳበትን ተቃውሞ በትክክለኛ አካሄድ በሐሳብ ሞግቶ ፋርሽ ለማድረግ ከመሞከር ይልቅ የተነሳበትን የተቃውሞ አካል በጠላትነት ፈርጆ የማጥፋት መዝሙረ ኢህአዴግ ማቀንቀን ይቀነዋል፡፡

ምርጫ 97 ከሁሉም ወገኖች በሚውጣጣ ጣጣ አይሆኑ ሆኖ የኢትዮጵያን ህዝብ ልብ ክፉኛ አሳዝኖ አልፏል፡፡ ጠባሳው ግን አሁንም ድረስ አልጠፋም፡፡ ከዚያ የመነቃቃት ጊዜ በኋላ ያለው መዝሙረ ኢህአዴግም ድርጅቱ ለተቃውሞ የሚነሱበት አካላትን አመጽና ግጭት ቀስቃሽ አድርጎ የመሳል ጋጋታ ላይ ያተኮረ እንዲሆን አድርጎታል፡፡ በዚህም ተቃዋሚዎችን ‹‹ፀረ-ልማት፣ ፀረ-ሰላም፣ ፀረ-ዴሞክራሲ…›› አድርጎ በህዝቡ ዘንድ ለማቅረብ የሚታትሩ መዝሙረ ኢህአዴጎች ረዘም ላለ ጊዜ ሳይቀየሩ ለመቀንቀን ችለዋል፡፡

ኢህአዴግ ተቃውሞን ብቻ ሳይሆን ጸጥታንም የሚፈራ ስብስብ ያለበት ፓርቲ ነው፡፡ ሞቅ ሲል እንደሚደነግጠው ሁሉ ጭር ሲልም አይወድም፡፡ ስለዚህም በህዝብ ዘንድ ዝምታ ሲበዛ አንድ የማደነባበሪያ መዝሙር መልቀቅ እንዳለበት ያምናል፡፡ በሙስሊም ኢትዮጵያውያን ዘንድ ለረጅም ጊዜ እየተካሄደ ያለው ትግል መነሻ የዚህ የኢህአዴግ ዝምታን የመስበሪያ ዘዴ እንደሆነ አድርጎ መውሰድ ይቻላል፡፡ ኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች መንግስት በሐይማኖታችን ጣልቃ እየገባ ነው በማለት እያደረጉት ባለው ትግል ውስጥ ግንባር ቀደም ታጋዮችን የመምቻ ቀዳዳ መፈለግ ነበረበት፡፡ ስለሆነም ‹‹አሸባሪዎች፣ አክራሪዎች…›› የሚሉ መዝሙረ ኢህአዴግ በሙስሊም እህት ወንድሞቻችን ላይ አቀነቀነባቸው፡፡ በዚህም የሙስሊም መፍትሄ አፈላላጊ ኮሚቴ አባላትን ለማሰር ቻለ፡፡

በእርግጥ ይህ ከሽብር ድርጊት ጋር እያገናኘ ለማጥቃት የፈበረከው መዝሙር ከሐይማኖት መሪዎችና ኮሚቴዎች ጥቃት ያለፈና ማንኛውንም ለስልጣኑ አደገኛ ነው ብሎ የገመተውን አካል የማረ አይደለም፡፡ በዚህ ሽብር ተኮር አሸባሪ መዝሙረ ኢህአዴግ በርካቶች ለጥቃት ተዳርገውበታል፡፡ ጋዜጠኞች፣ የፖለቲካ ፓርቲ መሪዎችና አባላት እንዲሁም የነጻነት ተሟጋቾች ወደ ወህኒ እንዲወርዱ ተደርገውበታል፡፡

## መጪው መዝሙረ ኢህአዴግ

በሚቀጥለው ዓመት ሀገራዊ ምርጫ ይካሄዳል ተብሎ ይጠበቃል፡፡ ለዚህ ምርጫ ራሳቸውን ከወዲሁ እያዘጋጁ ያሉ የፖለቲካ ፓርቲዎች እንዳሉም መታዘብ ይቻላል፡፡ ገዥው ፓርቲ ኢህአዴግም ከወዲሁ ለምርጫ ካርድ መግዣ ይሆኑኛል ያላቸውን እንቅስቃሴዎች እያደረገ ለመሆኑ አመላካች ድርጊቶች አሉ፡፡

ከጤነኛው የአንድ ገዥ ፓርቲ የምርጫ ወቅት የምርጫ ካርድ ማግኛ ነጥቦች መካከል የተሰሩ የልማትና መልካም አስተዳደር ውጤቶችን እያነሱ ማስገንዘብ ይገኙበታል፡፡ በዚህም በምርጫ 2007 ጥቅም ላይ ሊውሉ የሚችሉ መዝሙረ ኢህአዴግ የትኞቹ ሊሆኑ እንደሚችሉ ከወዲሁ መገመት ይቻላል፡፡ ለአብነትም በአባይ ወንዝ ላይ እየተገነባ ያለው የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫ ግድብ እና የባቡር ፕሮጀክቶች በዋነኛነት ጥቅም ላይ ሊውሉ የሚችሉ ይሆናሉ ተብሎ ይገመታል፡፡ በተለይ አሁን በይድረስ ይድረስ እየተገነባ ያለው ቀላል የከተማ ባቡር ፕሮጀክት መቼም ቢሆን ከኢህአዴግ ጋር ሊጣጣም ያልቻለውን የአዲስ አበባ ህዝብ ቀልብ ለመሳብ የሚደረግ ይመስላል፡፡

ዳሩ ግን አዲስ አበቤዎች በዚህ የሚሸወዱ አይደሉም፡፡ በውሃ፣ በመብራት፣ በኔትወርክ፣ ከአቅም በላይ በሆነ ግብር ወዘተ. ምን ያህል ችግር እንዳለ ያውቃሉ፡፡ እናም አሁንም እየተገነባ ባለው ባቡር ብቻ (ለዚያውም በተያዘለት ጊዜ የሚያልቅ ከሆነ!) የአዲስ አበባን ህዝብ ቀልብ መሳብ የሚታሰብ አይመስልም፡፡ በዚያ ላይ በአምስት አመት ጊዜ ውስጥ እንደሐገር ይገነባል የተባለው የባቡር መስመር ተረስቶ ከተማ ላይ ብቻ ማተኮሩን ሳንረሳ ማለት ነው፡፡ ስለሆነም ከዚህ ጋር ተያይዞ ጥቅም ላይ ይውላል ተብሎ የሚታሰበው መዝሙረ ኢህአዴግ ከአሁኑ ጆሮ የተነፈገው መሆኑ አይቀሬ እንደሆነ ልብ ማለት ይቻላል፡፡

መጪው ምርጫን ተከትሎ ዋና ዋና የመምቻ መዝሙረ ኢህአዴጎች አሁንም ጥቅም ላይ ያሉትን ጨምሮ አዳዲስ ፈጠራዎችም ሊጨመሩበት እንደሚችሉ መተንበይ ከባድ አይደለም፡፡ ከሐይማኖት ጣልቃ-ገብነት ጋር በተያያዘ ከሙስሊሙም ሆነ ከክርስቲያኑ አብዛኛው ህዝብ ጋር ሆድና ጀርባ ሆኖ የሚገኘው ኢህአዴግ ‹‹አሸባሪ፣ አክራሪ…›› የሚሉትን መዝሙረ ኢህአዴግ በቀጣይ ጊዜያትም አጠናክሮ የሚያቀነቅን ይመስለኛል፡፡ በዚህ መዝሙረ ኢህአዴግ ተቃዋሚዎችና ጋዜጠኞች ዋነኞቹ የጥቃት ማረፊያ ሆነው መቀጠላቸውም አይቀሬ ነው፡፡

ምናልባት በመጪው የምርጫ ወቅት አዳዲስ መዝሙረ ኢህአዴግ ሊፈበረኩም ይችላሉ፡፡ በተለይ በአዲስ የትግል ወኔ ከሰማያዊ እና አንድነት ፓርቲዎች ዘንድ ብቅ ያሉትን ወጣት ታጋዮች ለመምታት እስካሁን ከሚጠቀምባቸው በተጨማሪ አዲስ መዝሙረ ኢህአዴግ ሊኖር እንደሚችል ይገመታል፡፡ ሆኖም ግን እንዲህ አይነት ወጣቶችን መነካካት (ለዚያውም ምርጡ መዝሙረ ኢህአዴግ ደራሲው መለስ ዜናዊ በሌለበት) ልክ እንደ 97ቱ ለኢህአዴግ ያልተጠበቀ ውጤት ሊያስከትልበት ይችላል፡፡ በመሆኑም ወጣቶቹ ታጋዮች ቀጣይ የኢህአዴግ መዝሙር ደራሲዎችን የሚፈትኑ ይሆናሉ፡፡

# በአዲስ ጠብመንጃ . . .

ከ ገፅ 8 የዞረ

አርበኞች የጦር ሜዳ ትግልና ድል ቀጥታ ድምፅ ነው! በሸዋ ጠቅላይ ግዛት ከጀግናው አርበኛ ከጅማ ሰንበቴ የውጊያ መስመር! የካቲት 6 ቀን 1929 ዓ.ም!

አንበሣው አርበኛ ጅማ ሰንበቴ ዘወትር በተጠንቀቅ ላይ እንደ ነበረ አንዘንጋ! በተጓዳኝም በሰው ኃይልና በጦር መሣሪያ ራሱን የማደራጀቱን ሥራ ቀጥሏል! በየወቅቱ በተሠውት ምትክ ሌላ መመልመል ደግሞ የግድ ነበር! በዚህ ሂደት የፋሽሽት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ጀግናውን አርበኛ ጅማ ሰንበቴን ለመግደል ቆርጦ ተነሥቷል! ነገር ግን እንዴት አድርጎ ሊገድል ይችላል?ወራሪው ኃይል ከመስክ ተዋጊዎቹ መካከል በጭካኔ የታወቀውን ክንፍ አዘዘበት! ይህ አርበኛውን ጅማ ሰንበቴን ለመግደል የታዘዘው ተዋጊ ክንፍ እርጉዝ ሴቶችን ሆዳቸውን በመቅደድ እንዲሁም ሕፃናትን በማረድና በመስለብ ይታወቃል! ይህ ተዋጊ ክንፍ ጀግናውን አርበኛ ጅማ ሰንበቴን ከነተከታዮቹ ለመደምሰስ አስቦ በግዳጅ ተልዕኮ ተንቀሳቀሰ፡፡ ጉዞውን ቀጠለ፡፡ አሁን ከጀግናው አርበኛ ጅማ ሰንበቴ ጋር ጦርነት ሊገጥም ተቃርቧል! ምኞት ሁል ጊዜ ወደ ተግባር ባይመጣም ሊሞክር ወስኗል! ሀሳቡን እውን ለማድረግ የድርጊት ተነሳሽነትን ወስዷል! ጦርነት ከፍቷል! ፍልሚያው ቀጥሏል! ቀጥሏል! ቀጥሏል! ለሰዓታት ተካሂዷል! ቆራጦቹ የኢትዮጵያ አርበኞች በተግባር የበላይነትን ጨብጠዋል! ድል አድርገዋል! ታሪክ ይናገራል! ጀግናው አርበኛ ጅማ ሰንበቴ ታሪክ ሠርቷል! ይህ ነው ሰው ማለት! እርጉዞችንና ሕፃናትን በመጨፍጨፍ ከአዛዦቹ አድናቆትን የተቸረው የፋሽሽት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ተዋጊ ክንፍ አይቀጡ ቅጣት ተቀጣ! ይህ በታሪካችን የጥንታዊት ኢትዮጵያ የጀግኖች አርበኞች የትግልና ድል ድምፅ ነው፡፡ ከሸሞ ጠቅላይ ግዛት ከጀግናው አርበኛ ከጅማ ሰንበቴ የውጊያ መስመር! 1930 ዓ.ም!

ቆራጡ የጦር ባለሙያ ጅማ ሰንበቴ በየውጊያ መስመሩ ግንባር ለግንባር ገጥሞ የፋሽሽት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይልን ከትቢያ ጋር ሲያዋህድ ከመኖሩም በላይ ከአዲስ አበባ ወደ አስመራ እንዲሁም ከዚያ ወደዚህ የሚጣውን የወራሪ ኃይል ተዋጊ በመንገድ ላይ እየጠበቀ ብዙ ጊዜ ድባቅ መትቶታል፡፡ ልበ ሙሉ የጦር ሰው ጅማ ሰንበቴ አሁን ከስም ገብቷል! በተወሳሰቡ ድንገተኛ ሁኔታዎች መካከል በወራሪው ኃይል ተከቧል፡፡ ሆኖም ከበባውን በጥሶ ለመውጣት በጀግነት ሲዋጋ ይስተዋላል! ውጊያው ተጋግሏል! በአርበኝነት ታሪካችን አሁን የምንገኘው በሸዋ ጠቅላይ ግዛት በከሰም ውስጥ መሆኑን አንዘንጋ! ጦርነት ነው! ሞት ነው! ዕልቂት ነው! ጀግናው አርበኛ ጅማ ሰንበቴ ቆርጧል! ትግል ነው ሙትሔው! የባንዳ መንጋ እንደ ቅጠል ረግፏል! እርግጥ ነው! ቆራጦች የኢትዮጵያ ጀግኖችም ተሠውተዋል! ጦርነቱ ቀጥሏል! በጣም ያሳዝናል! አሁን በጣም መጥፎ ወታደራዊ ወሬ በተዋጊ አርበኞች መካከል ይናፈሳል! ቆራጡ አርበኛ ጅማ ሰንበቴ በጀግንነት ሲዋጋ በፋሽሽት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ተዋጊዎች ጥይት ተመትቶ መውደቁ ይነገራል! ትክክል ነው! ጀግናው አርበኛ ጅማ ሰንበቴ በክብር ተሰውቷል! ሳያወላውል ዘልቋል! የፋሽሽት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ተዋጊዎች አሁን የጀግናውን አርበኛ የጅማ ሰንበቴን አንገት ለመቁረጥ ሣንጃ ሲቀባበሉ ይስተዋላል! ወደ አስክሬኑ ተጠግተዋል! አንድ ባንዳ በራስጌ በኩል የአስከሬኑን ጎፈሬ ሰብስቦ ይዞታል! ሁለተኛው ባንዳ ጎንበስ በማለት አንገቱን ሲቆርጥ ይታያል! የተቀሩት ከብበው ይመለከቱታል! ጣሊያኖች ወገባቸውን ይዘው ቆመዋል! ወራሪው ኃይል የጀግናውን አርበኛ የጅማ ሰንበቴን አንገት ቆርጦ ራሱን ልዝብ ድንጋይ ወደ ተባለ ቦታ ወሰደው! ካሁን ወዲያ ጀግናው አርበኛ ጅማ ሰንበቴ ሕልውናው በታሪክ ላይ ብቻ ይሆናል! ይህ በታሪካችን የጥንታዊት ኢትዮጵያ የጀግኖች አርበኞች የትግልና የመሥዋዕትነት ቀጥታ ድምፅ ነው! ከሸዋ ጠቅላይ ግዛት ከከሰም ጦር ሜዳ ከጀግናው አርበኛ ከጅማ ሰንበቴ የውጊያ መስመር! ሰኔ 25 ቀን 1932 ዓ.ም

ቆራጡ አርበኛ ጅማ ሰንበቴ በሸዋ ጠቅላ ግዛት በመናገሻ አውራጃ በበረህ ወረዳ አሌልቱ ኤጀርሣ ጊዮርጊስ በተባለ ቦታ በ1868 ዓ.ም ተወለደ፡፡ በወላጆቹ ቤት ካደገ በኋላ አዲስ አበባ መጥቶ ጥብቅና ሥራ ተሰማርቷል! ወራሪው ኃይል አዲስ አበባ ሲገባ ወደ አሌልቱ ተመልሶ ሕዝቡን ለአርበኝነት አስተባብሯል! ጀግናው አርበኛ ጅማ ሰንበቴ ሕምሌ 27 ቀን 1928 ዓ.ም በፍቼ ጦር ሜዳ ተዋግቶ በፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ላይ ከፍተኛ ጉዳት አድርሷል! ቆራጡ አርበኛ ጅማ ሰንበቴ ሲሰዋ ወታደራዊ ባህላዊ ማዕረጉ ፊታውራሪ እንደነበረ ታውቋል! በጀግናው አርበኛ ጅማ ሰንበቴ ስም አንድ ትምህርት ቤት በመናገሻ አውራጃ ውስጥ ተሰይሞ ነበር፡፡ ዛሬ የጎሣ አምበሎች የትምህርት ቤቱን ስም ቀይረውት ሊሆን ይችላል! ያም ሆነ ይህ የኢትዮጵያ ወጣቶች በማንም ከንቱ ስብከት ሳይወናበዱ ለቀደምት የኢትዮጵያ ጀግኖች ተገቢውን ክብር ሁሉ ሊሠጡ ይገባል! ዛሬ በኢትዮጵያ ውስጥ ብሄርተኛ ቦታ እንደሌለው ታውቋል! በተቃራኒው ግን ዘረኝነት ሥር ሰድዶ ጎሰኝነት የአገዛዝ መርህ ሆኗል! ናቡቴዎች ነግሰዋል! የኢትዮጵያ የዛሬው ገጽታ ይህን ይመስላል!

ክብር ለጀግናው አርበኛ ጅማ ሰንበቴ!ክብር ኢትዮጵያን ለማዳን በዱር በገደሉ ለወደቁ ጀግኖች ሁሉ! ክብር ዛሬም ዕለታዊ ጥቅምንና ጊዜዓዊ ምቾትን ንቀው ለኢትጵያ ነፃነት ሲታገሉ በችግር ላይ ለወደቁ ጥቂት ቆራጥ ኢትዮጵያውያን! ኢትዮጵያዊ ብሔርተኝነት ያሸንፋል!!!

# ሰላማዊ ትግሉ መሪዎቹን . . .

ከ ገፅ 12 የዞረ

ሳይሆን ቀርቶ ተቀዋሚው በእምነትና በጽናት በተገቢው መንገድ ሰላማዊ ትግሉን ማስኬድ ካልቻለ፣ ሥልጣን ላይ ያለውም ሥልጣን ወይም ሞት በሚል አስተሳሰቡ ተቀዋሚውን እያዳከመና ለጠንካራ ተቀዋሚ አልታደልንም በሚለው ምጸቱ ከቀጠለ ሕዝቡ በሰላማዊ ትግሉ በአጠቃላይም በፖለቲካው ተስፋ ይቆርጣል፡፡

ያኔ ብሶተኛውና ሌላ አማራጭ ፈላጊው ይበዛል፤ የሚፈራው የሀይል ትግልም ሆነ አሸባሪነት ቦታም ተባባሪም ያገኛሉ፡፡ ከጦርነትና ከአሸባሪ ተግባር የሚገኘው የሰው እልቂት የንብረት ውድመት ፍርስራሽ ብቻ ነውና ከዚህ ድርጊት ሀገርም ሕዝብም ተጠቃሚ አይሆኑም፡፡

በዚህ መንገድ በለስ ቀንቷቸው የምኒልክ ቤተ መንግሥት ወር ተረኛ ለመሆን የሚበቁ ቢኖሩ እነዚህ ጊዜያዊ ተጠቃሚ ሊሆኑ ይችሉ ይሆናል፡፡ ነገር ግን የመጡበትን መንገድ እያሰቡ፣ ሌላ ብሶተኛ እያነፈነፉ፣ ሌላ ጦርነት እየሰጉ፣ አገዛዛቸው የጉልበት፣ ሥርዓታቸው የአፈና ይሆናል፡፡ ስለሆነም ነው ሰላማዊ ትግሉ መሪዎቹን አግኝቶ መጎልበት አለበት የምንለው፡፡

ለጽሁፌ ማሳረጊያ ሥልጣን ባህልና አገዛዝ፣ ፖለቲካና ምርጫ ከሚለው የፕ/ር መስፍን ወልደማሪያም መጽሀፍ አንድ አንቀጽ ልዋስ፡፡ «እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ወደ ፖለቲካ ሲገባ ከልጅነት እስከ እውቀት በውስጡ የተመረገውን የጌትነትና የሎሌነት ባህል ፍቆ ፈቅፍቆ ማርገፍ አለበት፡፡ በግድ የአስተሳሰብ የጽዳት ዘመቻ ያስፈልገናል፡፡ ዓላማን የማጥራት ዘመቻ ያስፈልግናል፡፡ በግድ የነጻነትና የእኩልነት አራማጆች በቁርጠኝነት መነሳትና ማሳየት ያስፈልገናል፡፡ ብዙዎቹ የተቀናቃኝ መሪዎች ላይ የሚታየው የድሮው መኳንንትና መሳፍንት ለመምሰል የመሞከር ጠባይና ከዚህም ጋር ተያይዞ ሎሌዎችን በገንዘብ ሆነ በወደፊት እየገዙ የአገዛዝን ባህል ለማራማድ የሚደረገው ሙከራ የፖለቲካቸውን ሥርዓት አያራምድም፡፡ ጥረቱ ሁሉ በሥልጣን ላይ ያሉትን ሰዎች ለመለወጥ እንጂ ሥርዓትን ለመለወጥ አይመስልም (ገጽ 32)

# ኢትዮጵያና የዩክሬኑ . . .

ከ ገፅ 5 የዞረ

በወቅቱ ከቀደሙ ጋር ሲነጻጸር ይህ ነው የሚባል የህዝብ እንቅስቃሴ አልነበረም፡፡ ይህ በኢትዮጵያም ተመሳሳይነት ነበረው፡፡ 1997 ላይ የተሸነፈው ኢህአዴግ ወደ ምርጫ የገባውን ብቻውን ነው ማለት ይቻላል፡፡ ይህን ያህል የህዝብ እንቅስቃሴ ባልነበረበት ኢህአዴግ 99.6 አሸንፌያለሁ ብሎ ያወጀበት ነበር፡፡

በ2002 ‹‹አሸነፍኩ!›› ያለው የዩክሬን ፕሬዝዳንት ህዝብ የሚጠብቀውን ለውጥ ሊያመጣ አልቻለም፡፡ ከዚህ ይልቅ ግራ ዘመምነቱንና አፋኝነቱን እያጠናከረ ወደ ሩሲያ መጠጋቱን ያኔ የአምባገነኖች መከታ ሆና ከቆየች በኋላ ራሷን ማዳን ያልቻለችው የሶቬት ዋነኛዋ አካል ሩሲያ ስር መወሸቅን መረጠ፡፡ ይህ ግራ ዘመምነቱ ያሳሰባቸው የዩክሬን ወጣቶችም ስርዓቱን በተደጋጋሚ ተቃውመዋል፡፡ ለአብነት ያህል ባለፈው አመት በነበረው እንቅስቃሴ ሰልፈኞቹ ዋና ዋና ከተማዋ ውስጥ የሚገኘውን የሌኒን መታሰቢያ ሀውልት አፈራርሰዋል፡፡ ይህም ከሩሲያ ጋር ያለውን የስርዓቱ ግንኙነት ለመስበር ታስቦ ነው፡፡ መንግስት እንቅስቃሴውን ለማቆም በጥር አጋማሽ ‹‹ጸረ አመጽ ህግ›› ቢያወጣም ጭራሹን አመጹን አባብሶታል፡፡

ሰልፈኞቹ ይህን ህግ ‹‹የአምባገነን ህግ›› ብለው ጠርተውታል፡፡ እውን እንደማይሆን ለማሳየትም ጎዳናዎቹን አጣብበው ታይተዋል፡፡ ከአንድ አመት በኋላ ባለፈው ጥር ወር የዩክሬኗ ኬቭ እንደገና በወጣቶች ተሞላች፡፡ በየእኛው ምርጫ 97 አንድ አመት ሲቀረው አጭበርብሮ በህዝብ ኃይል የተሸነፈው ፕሬዝዳንት በ2002 ምርጫ እንደገና አሸናፊ ሆኗል፡፡ ይህ ፕሬዝዳንት ላይ ነው የኢትዮጵያው የ2007 ምርጫ አንድ አመት ሲቀረው ዩክሬናውያን እንደገና ሰልፍ ወጥተው ወደ ሩሲያ አባረውታል፡፡ ምንም ይሁን ምን ይህ የዩክሬንን ወጣቶች ጥንካሬ የሚያሳይ ነው፡፡ የማይፈለጉትን ፕሬዝዳንት አባረው ለሚፈልጓቸው በር ከፍተዋል፡፡ እነሱም አልመቻቸው ሲሉ ጎዳና ላይ ለመውጣት ማንም ከልካይ ያላቸው አይመስሉም፡፡ ኬይቭ በሰልፍ ተናውጣው ልማደኛውን ፕዝደንት ከስልጣን ስታባርር ከ10 አመት በኋላ ነው፡፡ ኢትዮጵያውያን ደግሞ ከ1997 ምርጫ በኋላ እንደገና ራሳቸውን ቀና እያደረጉ ነው፡፡ ምን አልባት ይህን ስናይ አዲስ አበባና ኬቭ መካከል ጭቆናን ለማስወገድ የሚደረግ የሁለት ዓለም ሰዎች ተመሳሳይ ዓላማና ራዕይ እንዳለ እንገነዘባለን፡፡ ይህን ከማንም ቀድሞ ህወሓት/ኢህአዴግ የተረዳው ይመስላል፡፡ የዩክሬን ወጣቶች የኬቭን አደባባዮች ሲያጥለቀልቁ ኢቲቪ አልዘገበም፡፡ ፕሬዝደንቱ ከተባረረ በኋላ ግን ለውጡን የዩክሬን የገዥ ፓርቲ ሚዲያ አድርጎ ለውጡን ማጥላላት ጀመረ፡፡ ከዚህ ለውጥ በኋላ የአልበርት አንስታይን ተቋም፣ የምዕራባውያን የደህንነት ተቋማት እንደሆኑ በመግለጽ ሰላማዊ ትግልን አጥላልተዋል፡፡ እዲያውም በአሁኑ ወቅት ያለው ከ10 አመት በፊት ከነበረው የበለጠ ጠንካራ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ዩክሬናውያን ከ10 አመት በፊት ፕሬዝደንቱን ከስልጣኑ ሲያወርዱ ኢንተርኔትና ሌሎች አጋጣሚዎች ነበራቸው፡፡ ኢትዮጵያውያን ግል አልነበራቸውም፡፡ በአሁኑ ወቅት የሰላማዊ ትግል አፍሪካ ውስጥ ምን አልባትም በ1960ዎቹ ከነበረው የጸረ ቅኝ ግዛት ትግል በኋላ እንደገና ፋሽን ሆኗል፡፡ ቱኒዚያውያን፣ ግብጻዊያን፣ ሊቢያውያን አምባገነኖቻቸውን አንበርክከዋል፡፡ ይህም ለኢትዮጵያውያን ሌላ ተጨማሪ ልምድ ነው፡፡ ዋና ከተማዋ አዲስ አበባን ጨምሮ በሁሉም የአገሪቱ ክፍሎች መንግስት የሚሰጣቸው አገልግሎቶቹ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተቆራረጡ ነው፡፡ የኑሮ ውድነት ተባብሶ ቀጥሏል፡፡ መንግስት አንዱን የእምነቱ ክፍል ደግፎ ሌላውን እየተቃወመ ነው፡፡ ይህ ዝምታ ውስጥ ቆይቶ 1966 ላይ ከፈነዳው ንቅናቄ ጋርም ልናመሳስለው እንችላለን፡፡

ኢትዮጵያና ‹‹ባለ ቀለሙ አብዮት››

የቀለም አብዮት የሚያስበረግጋቸው አምባገነኖች የመጀመሪያውን የዩክሬን አብዮት ኢንተርኔት ያሰባሰበው አመጽ በሚል ተችተውታል፡፡ በተቃኒው ከአንድ አመት በኋላ በተካሄደው የኢትዮጵያ ምርጫና ማጭበርበሩን ተከትሎ በተፈጠረው ግርግር ኢንተርኔት ይህን ያህል ሚና አልነበረውም፡፡ ይህም የሁለቱን የተለያየ ነባራዊ ሁኔታ ላይ የነበሩ ህዝቦች አንድ የሚያደርግ ነገር እንዳለ እንረዳለን፡፡ ኢንተርኔት ኖረም አልኖረም፣ ጉልህ ቀለም ተጠቀሙ አልተጠቀሙ፣ ሁለቱ ህዝቦች ለመብትና ነጻነት የማይጨነቅ አምባገነን ስርዓትን ለማስወገድ ተንቀሳቅሰዋል፡፡ በእርግጥ የዩክሬን ለውጥ የሰዎች መቀያየር ብቻ ሳይሆን ህገ መንግስቱ፣ የፕሬዝዳንቱና የፓርላማው ስልጣን ላይም አብይ ለውጥ ማድረግ የቻለ ነበር ማለት ይቻላል፡፡ በተቃራኒው የእኛው የታሰበውን የስርዓት ለውጥም ማድረግ አልቻለም፡፡

በ2002 ዓ.ም ምርጫ ላይ የቀለም አብዮትን ከሰላማዊ ትግል ያፈነገጠ ለማስመሰል የማይታክተው ገዥው ፓርቲ ተቃዋሚዎችን ‹‹የቀለም አብዮተኛ›› በሚል በትችት መልክ ማቅረቡ የሚታወስ ነው፡፡ ምንም እንኳ ተቃዋሚዎች ህዝብን ለማንቀሳቀስ መጠነኛ ጥረት አድርገው የነበር ቢሆንም ለቀለም አብዮት የሚመጥን እንቅስቃሴ አልነበረም፡፡ ቀለምን በተለየ መልኩ በስምም ሆነ በሌላ ምልክትነት የተጠቀመ ፓርቲም አልታየም፡፡ የእነ አቶ ልደቱን ኢዴፓ ምልክቱን አበባ አድርጎ የነበር ቢሆንም ለንቅናቄ የሚያበቃውና ከህዝብ ጋር የሚያገናኘው እንቅስቃሴ አልነበረውም፡፡ የአበባውን ቀለምም ለዚህ አላማ ብሎ የመረጠው አይመስልም፡፡ የኢህአዴግ ወቀሳም ከእሱ ጋር የተያያዘ አልነበረም፡፡ ነገር ግን ከ2002 አንድ አመት ቀደም ብሎ በምስራቅ አውሮፓ፣ በኢራንና በመካከለኛው ምስራቅ የዩክሬኑ የቀለም አብዮት ተጠናክሮ የቀጠለበት ወቅት ነበርና ኢህአዴግንም እንቅልፍ ነስቶ እንደነበር አይዘነጋም፡፡ በመሆኑም እያንዳንዱን የተቃዋሚዎች እንቅስቃሴ በተለይም የመድረክን መጠነኛ እንቅስቃሴዎች ከቀለም አብዮት ጋር አገናኝቶ ሲወቅስ ተስተውሏል፡፡

## ቀጣዩንስ ማን ይመራዋል?

ኢትዮጵያ ውስጥ ሰላማዊ ትግል እንደገና በተነቃቃባቸው ባለፉት ሁለት አመታት ሰማያዊና አንድነት ፓርቲዎች እነዚህን የሰላማዊ ትግል ስልቶች በመጠኑም ቢሆን በመጠቀም እንቅስቃሴ እያደረጉ ይገኛሉ፡፡ ሰማያዊ በግራዚያኒ ላይ የተደረገውን ተቃውሞ ከመሩት አካላት መካከል አንዱ ነው፡፡ ለ8 አመት ያህል ተከልክሎ የቆየውን የሰላማዊ ሰልፍ መብት እንደገና በህዝብ እንዲለመድ የራሱን አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡ አሁንም ድረስ በስርዓቱ አደባባዮችን እየተከለከሉም ቢሆን ሰላማዊ ሰልፍን እያደረጉ የቀጠሉት ሁለቱ ፓርቲዎች ብቻ ናቸው፡፡ አንድ ሶስተኛው ያህል የግብጽ ህዝብ ጥቁር ለብሶ ቤት ውስጥ እንዲውል አድርገዋል፡፡ ምንም እንኳ በተወሰኑ ሰዎች ብቻ የተወሰነ ቢሆንም ይህን የጥቁር መልበስ፣ ሻማ ማብራት ሰልትም በሰማያዊ ፓርቲና የአንድነት ፓርቲዎች በመጠኑም ቢሆን ተጠቅመውበታል፡፡ በተለይ ሰማያዊ ፓርቲ ጥቁር መልበስ፣ ጥቁር ሪቫን ማድረግን ጨምሮ የፓርቲውን ሰንደቅ አላማ ጭምር በተለያዩ መድረኮች ለህዝብ ማስተዋወቅ ችሏል፡፡

በመሆኑም ከሚዲያ እጥረት፣ ልምድ፣ የሌሎች ፓርቲዎችና አካላት ትብብር ማነስ ተጨምሮበት ውጤታማ ነው ባይባልም ምልክቶቹ በጅምርነት ይታያሉ፡፡ ከአሁኑ እንዲህ ጅምር እንቅስቃሴዎችን ማስቀጠል ከቻለ፣ በአሁኑ ወቅት ያለ ምርጫ ሳይደርስ፣ ስለ እምነት ጣልቃ-ገብነት፣ ሙስና፣ ስለ ዜጎች በቀለም አብዮት ወቅት ተሳታፊዎች በስፋት የሚንቀሳቀሱበት ማህበራዊ ድረ-ገጽን ነው፡፡ በአሁኑ ወቅት ከየትኛው ፓርቲ በተሻለ ሁለቱ ፓርቲዎች የፌስ ቡክ ማህረሰቡን ቀልብ መግዛት ችለዋል፡፡ በቅረቡ የተጠራው ሰልፍም ቢሆን በዚሁ ፌስ ቡክ የተዘጋጀ ነው፡፡ ከሰላማዊ ትግል ስልቶች አንዱ አባላትና ደጋፊዎች በቀላሉ የሚተዋወቁበት፣ ገዥውን የሚያሳጡበት፣ የተበደሉትን የሚዘክሩበትን ቀለምን መጠቀም ነው፡፡ ይህም የ‹‹ቀለም አብዮትን›› የሰላማዊ ትግል ወሳኙ አካል ያደርገዋል፡፡ ከዩክሬን በኋላ የቀለም አብዮት እንዳካሄዱ ከሚነገርላቸው የሰሜን አፍሪካ አገራት መካከል ግብጻዊያን ይህን ተጠቅመውበታል፡፡ ግብጻውያን ወጣቶች በፌስ ቡክ ባደረጉት ጥሪ መሰረት መፈናቀል፣ ስለ መሬት ጉዳይ፣ ስለ ኑሮ ውድነትና የመሳሰሉትን ጥያቄዎች ማንሳት መጀመሩ በምርጫ ወቅት ይህን ሰልት ተጠቅሞ ተፎካካሪና ችግሮች ሲፈጠሩም የመደራደር አቅም ሊኖረው የሚችልበት አጋጣሚ ሰፊ ነው፡፡ በተለይ አጀንዳውን ለሌሎች ተቃዋሚዎች ማቅረብና ተባብረው መስራት ከቻሉ ኮሚኒስታዊ ካባውን ያላወለቀውንና ቻይናን ለስልጣን መከታ ያደረገውን ህወሓት/ኢህአዴግን አሉታዊ ስም በሚሰይመው ይህ ሰላማዊ የትግል ስልት ማሸነፍ የማይቻልበት ምክንያት አይኖርም፡፡ ይህ እንዳለ ሆኖ ግን ፓርቲዎች ከለውጥ በኋላ ለውጥን መሸከም የሚያስችል ትክሻ ለመገንባት ከአሁኑ መዘጋጀት ይኖርባቸዋል፡፡

## በዩክሬን ምርጫውን ተከትሎ አመጽ ሲቀጣጠል የእኛ 1997 ትልቅ ለውጥ የታየበት ወቅት ነው።1997 ላይ ዳግም ምርጫ አድርጋ 2002 ዓ.ም ላይ ዋናውን ምርጫ ያደረገችው ዩክሬን የተባረረው ፕሬዝዳንት እንደገና ስልጣን ያዘ በወቅቱ ከቀደሙ ጋር ሲነጻጸር ይህ ነው የሚባል የህዝብ እንቅስቃሴ አልነበረም። ይህ በኢትዮጵያም ተመሳሳይነት ነበረው። 1997 ላይ የተሸነፈው ኢህአዴግ ወደ ምርጫ የገባውን ብቻውን ነው ማለት ይቻላል። ይህን ያህል የህዝብ እንቅስቃሴ ባልነበረበት ኢህአዴግ 99.6 አሸንፌያለሁ ብሎ ያወጀበት ነበር።

# በአዲስ ጠብመንጃ በምንሽር፤ አገዳደሉ ሆድ የሚያሸር።

**ከፋክራ ሥነ ቃል የተወሰደ**



ታዴዎስ ታንቱ

የመ.ሣ.ቁጥር 43414

በምድር ላይ ከሱ በላይ ኃያል መኖሩን ዘንግቷል! አንገቱ ደንድኗል! ልቡ አብጧል! በዕብሪት ተወጥሯል! ናላው ተደፍኗል! በብዙ ካሚዮኖች ታጭቋል። በብረት ለበስ ታጅቧል! የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል በቀጥታ ወደ አዲስ አበባ ይጓዛል! መንገዱ አልጋ በአልጋ መስሎታል! ሳያውቅ ገብቶ አውቆ ያልቃል! ሞት ተደግሶለታል! የኢትዮጵያ አርበኞች በከፍተኛ የውጊያ ስነ ልቦና አድፍጠዋል! በጉዞ መስመሩ ላይ ተነጥፈዋል! ሰው ባገሩ ማንን ሊፈራ ይችላል? የኢትዮጵያ አርበኞች ጀግንነት ደግሞ ይለያል! የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል አሁን የኢትዮጵያ አርበኞች ካደፈጡበት በቅርብ ርቀት ይታያል! መጥቷል! መጥቷል! መጥቷል! ድም! ድም! ድም! ዱዋ! ዱዋ! ዱዋ! አልሰሜ ከጀግኖች አርበኞች ዒላማ ውስጥ ገብቷል! ወራሪው ኃይል ተደነባብሯል! ሳይዘገይ ግን አፀፋ ሰጥቷል! ጦርነቱ ተጋግሎ ቀጥሏል! እሳቱን ለማጥፋት እሳት ተለኩሷል! ተቀጣጥሏል! ጀግናው አርበኛ ጅማ ሰንበቴ እንደ ቀትር እባብ ይወረወራል! እያነጣጠረ ያደባያል! እንደ ገብስ ያጭዳል! የተቀሩት ጀግኖችም የሬሳ ነዶ አስረዋል! በወራሪው ኃይል ላይ ከፍተኛ ጉዳት ደርሷል! ጦርነቱ ቀጥሏል! ቀጥሏል! ቀጥሏል! ቀጥሏል! በጣም ብዙ የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ተዋጊዎች አልቀዋል! የእሳት እራት ሆነዋል! የአንበሳን ልጅ ዝንጀሮ እንዴት ይደፍረዋል? የጀግኖች መሬት በጣሊያን በምን ሒሳብ ይረገጣል? ጀግናው አርበኛ ጅማ ሰንበቴ በጋለ ወኔ ይስተዋላል! የኢትዮጵያ አርበኞች አጥቅተው የበላይነታቸውን አረጋግጠዋል! ወራሪው ኃይል ፈርጥጧል! ከስልሳ ያላነሱ ብረት ለበሶችና ካሚዮኖች ከጥቅም ውጭ ሆነዋል! በርካታ የነፍስ ወከፍ የጦር መሳሪያዎችና መሰል ጥይቶች ተማርከዋል! እንዲሁም አንድ ድንኳን ከአርበኞች እጅ ገብቷል! በዝርዝር ያልተጠቀሱ ሌሎች ዕቃዎችም ተማርከዋል! የዘገየ ዜና የደረሰው ይመስል የጦር አይሮፕላን መጥቷል! ቦምቦችን በገፍ ጥሏል! በጀግኖቹ በኢትዮጵያ አርበኞች ላይ አንዳችም ጉዳት ሳያደርስ ግን ተመልሷል! ይልቁንም የውሻ ሞት የሞቱ ባንዳዎችን ሬሳ በቦምብ ደብድቧል! ይህ በታሪካችን የጥንታዊ ኢትዮጵያ የጀግኖች አርበኞች የትግልና ድል ቀጥታ ድምፅ ነው! ከሸዋ ጠቅላይ ግዛት ምስር ምድር ከተባለ ጦር ሜዳ! ጥቅምት ወር 1929 ዓ.ም!

አንበሳው አርበኛ ጅማ ሰንበቴ አሁን ከመስክ ስምሪት ተከታታዮች መረጃ ደርሶታል! ወታደራዊ መረጃ መሆኑን አንዘንጋ! አንድ ግራዝማች አየለ የተባለ ባንዳ ህዝቡን ቁም ስቅሉን ያሳያል! ከፋሽስቶች በላይ ፋሽስት ሆኗል! ሽማግሌውን አሮጊቱን ወንዱንና ሴቱን ሁሉ እየጠቆመ ያስገድዳል! ምክንያት ደግሞ አያጣም! የሽፍታ አባት መሆኑን ይናገራል! ጣሊያኖች ቶሎ መጥተው አቅመ ደካማውን ሽማግሌ ወልዶና ከብዶ በክብር በኖረበት በገዛ ቤቱ በራፍ ላይ ይደፉታል!ምንም ምህረት የለም! የግራዝማች አየለ ጥቆማ መሬት አይወድቅም! ጣሊያን እንደ ወረደ ይቀበለዋል! ግራዝማች አየለ ሰብዓዊነት እንኳን አልነበረውም። ቤተክርስቲያን ከመሳለም በስተቀር አንዳችም ነገር ለመስራት አቅም የሌላትንም አሮጊት አስግድሏል! ዘወትር ሰበቡ አንድ አይነት ነው! አንድ ሰው ለማስገደል ሲፈልግ ከአርበኞች ጋር ግንኙነት እንዳለው ወይም እንዳላት ለጌታው ለጣሊያኑ ይናገራል! ጣሊያን ምን ቸገረው?ከመቅፅበት ሄዶ ይረሽነዋል÷ ወይም ይረሽናታል! ጀግናው አርበኛ ጅማ ሰንበቴ የደረሰውን የመስክ መረጃ በሚገባ መርምሮታል! በህዝቡ ላይ የተፈፀመውና በመፈጸም ላይ የነበረው ግፍ ዘግናኝ መሆኑን ተረድቶታል! በጣም ተናድዷል! ተናድዶ ግን ዝም አላለም! ግራዝማች አየለንና ተከታዮቹን ለመደምሰስ ሳልመኝ ማርያም ከነበረው ምሽጉ ተነሳ! አርበኞቹ ሃሳቡን ባንድ ቃል አፀደቁት! ወደ ግራዝማች አየለ መንደር ገሰገሱ! ቤቱን በጥቆማ አገኙት! ነገር ግን ወኔ ቢሱ ግራዝማች አየለ ገና አርበኞች ሳይደርሱ ሸሽቷል! ተከታዮቹ በእርግጥ ጥቂት ተታኩሰዋል! ጀግኖቹን የኢትዮጵያ አርበኞች ግን ሊቋቋሟቸው ሳይችሉ ቀርተዋል! ቆራጡ አርበኛ ጅማ ሰንበቴ የግራዝማች አየለን ቤት አቃጠለው! ጀግና በዋለበት ሁሉ ወገንን ያኮራል! አስር ጠብመንጃ ማርኮ ምንም ጉዳት ሳይደርስበት ወደ ምሽጉ ተመልሷል! ይህ የታሪክ ድምፅ ነው! ይህ የጥንታዊት ኢትዮጵያ የጀግኖች አርበኞች የጦር ሜዳ ድምፅ ነው! አሁን በፋሽስት ኢጣሊያ ወረራ ዘመን ላይ መሆናችንን አንዘንጋ! ድል አድራጊው ጅማ ሰንበቴ የማረከውን ጠብመንጃ አርበኞችን አስታጥቋል! ህዳር ወር 1929 ዓ.ም!

ጀግናው የኢትዮጵያ አርበኛ ጅማ ሰንበቴ ስሙ ገነነ። ስራው ታወቀ። በዚህ ምክንያት የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ሊገድለው ቆርጦ ተነሳ! በቀጥታ ሰንዳፋ ከነበረው ምሽጉ ተነስቶ ወደ ሳልመኝ ማርያም ይገሰግስ ገባ! ጀግናው ጅማ ሰንበቴ ሳልመኝ ማርያም ላይ መመሸጉን አውቋል! በቂ መረጃ ነበረውና! ጀግናው አርበኛ ጅማ ሰንበቴ በተጠንቀቅ ላይ ነው! በአፀፋ መረጃ የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ተግባራዊ እንቅስቃሴን መዝግቦታል! ቀጥሎ ምን ሊያደርግ አስቧል?ያሰበውን አስቧል! ለምሳ ያዘጋጁትን ለቁርስ አስቧል! ምሽጉን ትቶ ወጥቷል! የወራሪውን ኃይል መምጫ መንገድ አውቆታል! ጎሽ በር ከተባለ ቦታ ድረስ መጥቶ አድፍጧል! የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል መረጃ አልነበረውም! አሁንም ጀግናውን አርበኛ ጅማ ሰንበቴን በሳልመኝ ማርያም ምሽጉ ውስጥ ብዙ ባንዳ ሞቷል! በርካታ የጦር መሳሪያም ተማርኳል! ይህ በታሪካችን የጥንታዊት ኢትዮጵያ የጀግኖች አርበኞች የትግልና ድል ድምፅ ነው! ከሸዋ ጠቅላይ ግዛት ከጎሽ በር ጦር ሜዳ! ታህሳስ ወር 1929 ዓ.ም!

የወሳኙ ድል ጥያቄ በተግባር ቀጥሏል! ድል ወይም ሞት! ነጭ ጥቁርን አይገዛም! አንበሳው ጅማ ሰንበቴ ቀንና ለሊት በተጠንቀቅ ይስተዋላል! ተከታዮቹም በውጊያ ዝግጁነት ስነ ልቦና ቆመዋል! አሁን ከመስክ መረጃ መጥቷል! ወራሪው ኃይል ጀግናውን አርበኛ ጅማ ሰንበቴን ከነተከታዮቹ ለመግደል በተግባራዊ እንቅስቃሴ ላይ እንደ ነበር ተሰምቷል! የመስክ መረጃ ያረጋግጣል! መረጃው ተመርምሯል! እውነት ነው! አርበኞችን ለመግደል ወረራው ኃይል ተንቀሳቅሷል! ደም የለመደውን ቆራጥ አርበኛ በቀላሉ እንዴት መግደል ይቻላል? ሀሳብ የአዕምሮ ፈረስ ሆኖ ይቀራል! ድርጊትም አንዳንዴ ያለ ውጤት ይደመደማል! ሆነም ቀረ ወራሪው ኃይል ከአርበኞች መንደር ኃይል እንደልማዱ ፈርጥጧል! ይህ በታሪካችን የጥንታዊት ኢትዮጵያ የጀግኖች አርበኞች የጦርነትና የድል አድራጊነት ቀጥታ ድምፅ ነው! በሸዋ ጠቅላይ ግዛት የውጊያ ወረዳዎች ከተመዘገቡ ገድላት የተመዘዘ! ጀግናው አርበኛ ጅማ ሰንበቴ ድልን ተቀዳጅቷል! ጥር 29 ቀን 1929 ዓ.ም!

ቆራጡ የኢትዮጵያ ጀግና ጅማ ሰንበቴ ማንነቱን በተግባር አሳይቷል! ልበ ሙሉነቱን አስመስክሯል! የፋሽሽት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ግን ሞት አልጠገበም! ከውድቀቱ ለመማርም ዝግጁ አልነበረም! ባንዳ ደግሞ በሆዱ ያስባል! ለሆዱ ይኖራል! ለሆዱ ይሞታል!የእሣት እራት ይሆናል! አሁንም ይግተለተላል! ጀግናው የኢትዮጵያ አርበኛ ጅማ ሰንበቴ ሥጋውን ለምድር አራዊትና ለሰማይ አዕዋፍ ይሰጣል! በተጠንቀቅ ቆሟል! ምሽጉን በበለጠ አጠናክሯል! ጀግኖቹን ከጎኑ አሰልፏል! አማላጅ አይሰማም! ዕርቅ አይፈልግም! ጦርነት! ጦርነት! ጦርነት! ድል! ድል! ድል! ወራሪው ኃይል ሊያገኘው ቋምጧል! አንበሳው ተኝቶ የሚጠብቅ መስሎታል! የኢትዮጵያ አርበኞች ጎሽ በር ላይ አድፍጠዋል! አድፍጠዋል! አድፍጠዋል! አድፍጠዋል! ወራሪው ኃይል አሁን ከጎሽ በር ደርሷል! ድም! ድም! ድም! ዱዋ! ዱዋ! ዱዋ! የቅድሚያ ተነሳሽነትን የኢትዮጵያ አርበኞች ወስደዋል! ጦርነት ተከፍቷል! የወራሪው ኃይል አፀፋ ሳይዘገይ ተመልሷል! የጦርነት ነበልባል ይንቦገቦጋል! ትንታግ ይቅመዘመዛል! ጦርነቱ ቀጥሏል! ቀጥሏል! ቀጥሏል! የፋሽስቱ ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ለቅኝ ገዥነት ይፋለማል! የኢትዮጵያ አርበኞች ለሉዓላዊነታቸውና ለአንድነታቸው ቆርጠዋል! ጀግናው አርበኛ ጅማ ሰንበቴ በቁርጠኝነትና በዓላማ ፅናት ይዋጋል! የሬሳ ነዶ አስሯል! ባንዳ እንደ ቅጠል ረግፏል! በዚሁ ጦርነት ባንዳው ግራዝማች አየለ ከወራሪው ኃይል ጎን ቆሞ ታይቷል! ነገር ግን ቆስሎ አምልጧል! ድል የኢትዮጵያ አርበኞች ሆኗል! ወራሪው ኃይል ተመልሶ ወደ ሰንዳፋ ፈርጥጧል! በህይወት የተረፈው በሰላም ከምሽጉ ለመግባት ቋምጧል! ደርሷል! ተጠግቷል! ተጠግቷል! ተጠግቷል! ግፈኛው የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይል የቅድሚያ ተነሳሽነት ወስዷል! ተኩስ ከፍቷል! የኢትዮጵያ አርበኞች አፀፋ አሰምተዋል! ጦርነቱ በጥቂት ጊዜያት ተፋፍሟል! እሳት ይዘንባል! ጀግንነት ከጦር መሳሪያ ብዛትና ጥራት ይለያል! እርግጥ ነው! ለጀግና የጦር መሳሪያ ያስፈልገዋል! ግን የዓለም ምርጥ መሳሪያ የያዘ ተዋጊ ጀግንነት ከሌለው ድል ተነሺ ይሆናል! ይህ በታሪክ የተመዘገበ እውነት ነው! የፋሽስት ኢጣሊያ ወራሪ ኃይልና የኢትዮጵያ አርበኞች ጦርነትም በመሳሪያ ብዛትና ጥራት ልዩነት ሲመዘን በጣም ሰፊ እንደ ነበር ታውቋል! የታሪክ ሃቅ መሆኑን ይዘናል! ጦርነቱ ግን ተጋግሏል! ድል ወይም ሞት! ድም! ድም! ድም! ዱዋ! ዱዋ! ዱዋ! ይህ የነፍስ ወከፍ የጦር መሳሪያ ድምፅ ነው! የኢትዮጵያ አርበኞች በቆራጥነት ቀጥለዋል! ጀግናውን አርበኛ ጅማ ሰንበቴን በውጊያ መስከ ማሸነፍ ወራሪው ኃይል እንዳሰበው ቀላል ሳይሆን ቀርቷል! በአሁኑ ሰዓት የጥንታዊት ኢትዮጵያ አርበኞች ድልን ተቀዳጅተዋል! ወራሪው በጀግኖች መሬት ላይ ሆኖ ዕርቅ እንዴት ይታሰባል? ወራሪው ኃይል አሁን ወደ አርበኞች መንደር ሲጠጋ ይስተዋላል! ድፍረት ነው! ልብ ሳይኖረው እንዴት ልባም ይሆናል? አሁን በጣም ተጠግቷል! የኢትዮጵያ አርበኞች በከፍተኛ የውጊያ ሥነ ልቦና በተጠንቀቅ ቆመዋል! ወራሪው ኃይል በበለጠ ወደ ፊት ገፍቷል! ጀግኖቹ የኢትዮጵያ አርበኞች የቅድሚያ ተነሳሽነት ወስደዋል! ድም! ድም! ድም! ዱዋ! ዱዋ! ዱዋ! ይህ የጥንታዊት ኢትዮጵያ የጀግኖች አርበኞች የነፍስ ወከፍ የጦር መሣሪያ ተኩስ ድምፅ ነው! ሳይዘገይ አፀፋ ተሰምቷል! ጦርነቱ ወዲያው ተጋግሏል! ቀጥሏል! ቀጥሏል! ቀጥሏል! ወራሪው ኃይል የድል ተስፋ ሳይኖረው በተስፋ ይዋጋል! ጦርነቱ ለሰዓታት ተካሂዷል! ባንዳ እንደ ገብስ ታጭዷል! እርግጥ ነው! አርበኞችም ተሰውተዋል! ሆኖም አሁን ጀግኖቹ የኢትዮጵያ አርበኞች የበላይነትን ጨብጠዋል! በርካታ የነፍስ ወከፍ የጦር መሣሪያዎችንም ማርከዋል! ድልን ተጎናጽፈዋል! ይህ በታሪካችን የጥንታዊት ኢትዮጵያ የጀግኖች

**አንበሳው አርበኛ ጅማ ሰንበቴ አሁን ከመስክ ስምሪት ተከታታዮች መረጃ ደርሶታል ! ወታደራዊ መረጃ መሆኑን አንዘንጋ ! አንድ ግራዝማች አየለ የተባለ ባንዳ ህዝቡን ቁም ስቅሉን ያሳያል ! ከፋሽስቶች በላይ ፋሽስት ሆኗል ! ሽማግሌውን አሮጊቱን ወንዱንና ሴቱን ሁሉ እየጠቆመ ያስገድዳል !**

ወደ ገፅ 6 ይዞራል

# “የሚሊዮኖች ድምጽ ለመሬት ባለቤትነት ዘመቻ”



ግርማ ሞገስ

ይህን ጽሑፍ እንድጽፍ ያነሳሳኝ ዐርብ የካቲት 28 ቀን (March 7, 2014) አንድነቶች “የሚሊዮኖች ድምፅ ለመሬት ባለቤትነት” የሚል ህዝባዊ ንቅናቄ (ህዝባዊ ሰላማዊ ዘመቻ) በ14 ከተሞች (አዲስ አበባ፣ ደሴ፣ አዋሳ፣ አዳማ/ናዝሬት፣ መቀሌ፣ ደብረታቦር፣ ደብረ ማርቆስ፣ ድሬ ዳዋ፣ ጅንካ፣ ቁጫ፣ አሶሳ፣ ነቀምት፣ ለገጣፎ፣ እና በተጓዳኝ ከተሞች ወልዲያ፣ ጋምቤላ፣ ም/አርማጨሆ (አብርሃ ጅራ)) እንደሚያደርጉ ማሳወቃቸው ነው:: መግለጫቸውን እንዳነበብኩ ዘመቻው ለታሪካችን፣ ለተያያዝነው የነፃነት ትግል እና ዓይናችን ለተከልንበት የዴሞክራሲ ሽግግር የሚሰጣቸው ጠቀሚታዎች አሉን? የሚሉትን ጥያቄዎች አንስቼ ጥቂት ከራሴ ጋር ከተነጋገርኩ በኋላ ለዘመቻው ድጋፌን በመስጠት እና አንድነቶችን በማበረታት ተሳትፎዬን እንድገልጽ ህሊናዬ የግድ አለኝ::

ስለዚህ የዚህ ጽሑፍ ግብ ዘመቻው የህወሃት/ኢህአዴግን የመሬት ባላቤትነት ፖሊሲ ለማሻሻል ብሎም ዛሬ በኢትዮጵያ ምርጫ ፓርቲዎች የሚያካሂዱትን የነፃነት ትግል እና ኢትዮጵያ ወደ ዴሞክራሲ ለመሸጋገር የምታደርገውን ጥረት በማገዝ ረገድ ሊሰጥ የሚችለውን ጥቅም መመርመር ነው::

ታሪካችን እንደሚያመለክተው በዘውዳዊው ስርዓት የኢትዮጵያ መሬት ባለቤቶች ባላባቶችና ነገስታቱ ነበሩ:: የ1966 ዓ.ም. ህዝባዊ አብዮት ጉልታዊውን ስርዓት ቢገረስስም የኢትዮጵያን ህዝብ የመንግስት ስልጣን ባለቤት ማድረግ ስላልቻለ ሽብርተኛው አምባገነን መንግስቱ ኃይለማርያም (ደርግ) እራሱን አዲሱ የኢትዮጵያ መሬት ባለቤት (ባላባት) አድርጎ ሾመ:: በ1983 ዓ.ም. ደግሞ ህወሃት/ኢህአዴግ በወታደራዊ ኃይል (ሌላ ሽብር) ደርግን አስወግዶ የኢትዮጵያን የመንግስት ስልጣን እና የመሬት ባለቤትነት ጠቅልሎ በእጁ አስገባ::

የመሬት ባለቤትነት ለአምባገነኖች የፖለቲካ ኃይል ምንጭ ነው:: ሃቀኛው ባለቤት ህዝብ ነው:: ይሁን እንጂ አምባገነኖች በጉልበት የመሬት ባለቤት መሆናቸው የኢትዮጵያ የተፈጥሮ ሃብት ባለቤትም ያደርጋቸዋል:: ይህ የፖለቲካ ኃይል ምንጭ ከሌሎች የፖለቲካ ኃይል ምንጮች ጋር ተዳምሮ የህዝባቸውን የፖለቲካ ጸባይ ለመቆጣጠር (በፍራቻ መግዛት) ያስችላቸዋል:: ህወሃት/ኢህአዴግ ደግሞ የመሬት ባለቤትነቱን የጎሳ ፖለቲካ ስለቀባው ህዝብን ከፋፍሎ ለመግዛት የሚያስችል ተጨማሪ የፖለቲካ ኃይል (የፖለቲካ አቅም) መንጭቶለታል::

የህወሃት/ኢህአዴግ መንግስት መሬት ፖሊሲ በበርካታ ክልሎች መፈናቀል እና አለመረጋጋት ፈጥሯል:: ለዚህ ችግር ዋንኛ ምንጩ የህወሃት/ኢህአዴግ የጎሳ ፖለቲካ የተቀባው የመሬት ፖሊሲ ነው:: ሌላ ቋንቋ ተናጋሪ ወደ አገርህ ሂድ ተብሏል:: ተፈናቃዩ ሃብቱን ንብረቱን ተዘርፏል:: ይህን ወንጀል የፈጸሙት የክልል ሹማምንት ዛሬም ለፍርድ አልቀረቡም:: ንብረታቸውን ተዘርፈው የተፈናቀሉ ዜጎችም እስከዛሬ ካሳ አልተከፈላቸውም:: እስቲ ይሁን ብለው በነበሩበት መኖር የቀጠሉት ሌላ ቋንቋ ተናጋሪዎች የሚኖሩት በስጋት ነው:: በአገርህ በስጋት እንድትኖር የሚያደርግህ የመሬት ፖሊሲ እንዲሻሻል ህዝቡ እንዲጠይቅ ለማድረግ ሰላማዊ ትግል ዘመቻ ካላደረግህ ለምን ልትዘምት ነው? ስለዚህ የመሬት ፖሊሲ እንዲሻሻል ሰላማዊ ትግል ዘመቻ ማድረግ (መታገል) ለመብት መከበር የሚደረግ ሰላማዊ ትግል እንጂ ህወሃት/ኢህአዴግ እንደሚለው “ህገ-መንግስት ለመጣስ” ወይንም “ልማትን ለማሰናከል” የሚደረግ ሁከት አይደለም::

ህወሃት/ኢህአዴግ ስለ “ህገ-መንግስት መጣስ” እና ስለ “ልማት መሰናከል” የሚለፍፈው ህዝብን አሸማቆ በፍራቻ ለመግዛት ነው:: እንደ እኔ ከሆነ ደግሞ ከባቡር ሃዲዱ መዘርጋትም ሆነ ከስኳር ፋብሪካ መተከል በፊት ህዝብ በአገሩ በነፃነት ተንቀሳቅሶ በመረጠበት አካባቢ ኑሮውን መስርቶ ካለስጋት የመኖር መብቱን የማክበር እና የማስከበር ግዴታ የኢትዮጵያ ህዝብ ብቻ ሳይሆን የዓለም ህዝብም እምነት ነው:: ዓለም አቀፋዊ ህግ ነው::

የህወሃት/ኢህአዴግ መንግስት መሬት ፖሊሲ በቡድን እና በግለሰብ መብቶች መካከል ሊኖር የሚገባውን ቅደም ተከተል ፍትሃዊ በሆነ መንገድ አያስተናግድም:: በምድረ ኢትዮጵያ ግለሰባዊ መብት ሳይከበር የቀድሞውም ሆኑ የዛሬው ጠቅላይ ሚንስትር እየተካሄደ ነው የሚሉን የዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ ሙሉ በሙሉ ፌዝ ነው:: የግለሰብ መብት መከበር ለዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ ቅድመ ሁኔታ ነው::

ህወሃት/ኢህአዴግ የገጠር መሬትን የፖለቲካ መጠቀሚያ በማድረግ የስልጣን ዘመኑን አራዝሟል:: በየአምስት አመት በሚደረገው አገራዊ እና ክልላዊ ምርጫ በገጠር የሚኖረውን አርሶ እና አርብቶ አደር የምርጫ ፖለቲካ ጸባይ ሲቆጣጠርበት (በፍራቻ ተቃዋሚ እንዳይመርጥ ሲያደርግ) ቆይቷል:: ህወሃት/ኢህአዴግን ያልመረጠ ከመሬት ይፈናቀላል፣ የመሬት ማዳበሪያ አያገኝም፣ የተሰጠው መሬት ይቀነስበታል የሚሉትን እና ተመሳሳይ ማስፈራሪያዎች ናቸው የፖለቲካ ጸባይ መቆጣጠሪያ ሽብርተኛ ፕሮፖጋንዳዎቹ:: በምርጫ ዝግጅት ሰሞን እነዚህን የሽብር ፕሮፖጋንዳዎች በካድሬዎች አማካኝነት በማናፈስ የገጠሩ ነዋሪ በፍራቻ ለነፃነቱ ሳይሆን ለህወሃት/ኢህአዴግ ስልጣን ዘመን መራዘም እንዲመርጥ ሲያደርገው ቆይቷል:: ስለዚህ “የሚሊዮኖች ድምፅ ለመሬት ባለቤትነት” ዘመቻ የገጠሩን ዜጋ የራሱ ነፃ አውጭ እንዲሆን እና በምርጫ 2007 ከፍራቻ ነፃ ወጥቶ ለነፃነቱ ይበጀኛል ያላቸውን ተቃዋሚ ፓርቲዎች እንዲመርጥ ያበረታታዋል::

በቅርቡ ተግባራዊ የተደረገው የከተማ መሬት ፖሊሲም እንደዚሁ የከተማ ነዋሪውን የፖለቲካ ጸባይ ለመቆጣጠር (ከተሜውን ፈሪ በማድረግ) የተቀየሰ አዲስ የህወሃት/ኢህአዴግ የፖለቲካ ኃይል ምንጭ ነው:: እንግዲህ የከተማ መሬት የመንግስት ከሆነ ህወሃት/ኢህአዴግን የሚቃወም የቤት ባለቤት መሬቱ የመንግስት ስለሆነ እቤትህን አንስተህ የፈለክበት ሂድ ልትባል ትችላለህ:: ይኼን ፖሊሲ ሳስታውስ ሁልጊዜ በአእምሮዬ የሚመጡ እና መልስ ያላገኘሁላቸውን ጥያቄዎች ላንሳ፣ ሰው ሲሞትስ? እሬሳ ለመቅበር የሚች ቤተሰብ ከመንግስት በሊዝ (Lease) መሬት ማግኘት አለበት ማለት ነው? ወይንስ እያንዳንዱ ዜጋ ቀደም ብሎ መቀበሪያውን በሊዝ (Lease) ተከራይቶ ማስቀመጥ አለበት? ሊዙስ (Lease) ለስንት አመት ነው? “የሚሊዮኖች ድምፅ ለመሬት ባለቤትነት” ዘመቻ ህዝቡ እራሱን ከዚህ ሰብአዊ ክብር ነፋጊ የህወሃት/ኢህአዴግ አዲስ የፖለቲካ ኃይል ምንጭ በምርጫ 2007 ነፃ እንዲያወጣ ያዘጋጀዋል::

በአዲስ አበባ ከተማ በተሰሩት ኮንዶሚኒየሞች የሚኖሩትን እና በመሰራት ላይ ባሉት ውስጥ ለመኖር ተመዝግበው ተራቸውን የሚጠብቁትን ዜጎች ህወሃት/ኢህአዴግ አንድ ለአምስት የሚለውን መዋቅሩን ተጠቅሞ የዜጎችን የምርጫ ፖለቲካ ጸባይ በቆጣጠር በምርጫ 2002 ህወሃት/ኢህአዴግን እንዲመርጡ ለማድረግ ከፍተኛ ጥረት ማድረጉን እናስታውሳለን:: ተቃዋሚን ከመረጥህ የተሰጠህን ቤት ትነጠቃለህ፣ ተራህን የምትጠብቅ ከሆነም ቤት አይሰጥህም በሚሉ ሽብርተኛ ማስፈራሪያዎች በማሰራጨት ነበር የህወሃት/ኢህአዴግ ካድሬዎች የዜጎችን የፖለቲካ ጸባይ ተቆጣጥረው ተቃዋሚዎችን እንዳይመርጡ ለማድረግ የሞከሩት:: “የሚሊዮኖች ድምፅ ለመሬት ባለቤትነት” ዘመቻ ህዝብን ከዚህ አይነት የፖለቲካ ጸባይ ቁጥጥር ነፃ ለማውጣት ጠቃሚነቱ ግልጽ ነው::

በኢትዮጵያ እያንዳንዱ ዜጋ (አርሶ አደሩን ጨምሮ) የመሬት ባለቤት የመሆን መብቱ በህግ ሲደነገግ ብቻ ነው የመንግስት የመሬት ባላባትነት ገደብ ሊደረግለት የሚችለው:: የግለሰቦች መብት ማክበር የመሬት ባለቤትነትን መብት ያካትታል:: በቋንቋ በተከፋፈለ ክልል ውስጥ የሚገኘው መሬት ብቸኛ ባለቤት የክልሉ መንግስት ብቻ ነው ከተባለ በክልሉ የሚኖሩ ሌላ ቋንቋ ተናጋሪዎች ሂዱ ሊባሉ ይችላሉ ማለት ነው:: ይህ እርማት የሚያስፈልገው አደጋ ነው::

ሰላማዊ ትግል ዘመቻዎች ሚናቸው ህዝብን የራሱ ነፃ አውጪ ማድረግ ስለሆነ ይኼም ዘመቻ ለምርጫ 2007 የሚጠበቅበትን አስተዋጽኦ አድርጎ ይሄዳል የሚል እምነት አለኝ:: “የሚሊዮኖች ድምፅ ለመሬት ባለቤትነት” የሚለውን ዘመቻ ከምር ቁምነገር የሚያስገኝ ዘመቻ ለማድረግ ከተፈለገ እያንዳንዱ ዘመቻ በደንብ ፕላን መደረግ አለበት:: ፕላን ሲሰላ ብዙ ነገሮች መስተዋል አለባቸው:: ፕላን ማድረግ ማለት ከበርካታ ነገሮች በተጨማሪ የኢትዮጵያ አየር ጸባይ ትንበያ የሚሰጠውን መረጃ በመጠቀም ዘመቻዎች ዝናብ በማይዘንብባቸው ቀናት እንዲሆኑ ጥረት ማድረግን ሳይቀር ያካትታል:: የእያንዳንዱ ዘመቻ ዜና ከፌስ ቡክ ባሻገር ሽፋን ማግኘት አለበት:: በኢትዮጵያ ሰራተኛው፣ ነጋዴው፣ ተማሪው፣ የቢሮክራሲ ሰራተኛው፣ ወ.ዘ.ተ. ዜናው በህትመት ወይንም በአየር እንዲደርሰው ለማድረግ የተቻለው ጥረት ሁሉ መደረግ አለበት::

እያንዳንዱ ዘመቻ የአገር ውስጥ እና የውጭ ነፃ ፕሬስ እና ድረ-ገጾች፣ የኢቲቪ፣ የቪኦኤ፣ የጀርመን ሬዲዮ፣ የኢሳት ሽፋን እንዲያገኝ አስፈላጊው ጥረት በቅድሚያ መደረግ አለበት:: ዘመቻን ለመግለጽ ለህዝብ የሚቀርቡ ምስሎች፣ ዩ-ቲዩቦች ጥራት ሊኖራቸው ይገባል:: በዘመቻ ላይ ለግልጋሎት የሚውሉ የድምጽ ማጉያዎች ጥራት እንዲኖራቸው በቅድሚያ ጥረት መደረግ አለበት:: ዘመቻውን በፓልቶኮች ማሰራጨት ካስፈለገ የድምጽ እና የምስል ጥራት እንዲኖር በቅድሚያ ማስላት ያስፈልጋል:: ይኼ ሁሉ የፕላነሮች ስራ ነው::

በመጨረሻ “የሚሊዮኖች ድምፅ ለመሬት ባቤትነት” ዘመቻ ህገ-መንግስቱ ውስጥ የተደነገጉትን የመቃወም መብቶች በመጠቀም ዴሞክራሲ ግንባታን ለማገዝ የሚደረግ ሰላማዊ ህዝባዊ እንቅስቃሴ ነው:: ይኼን ማድረግ ወደ ዴሞክራሲ እና ስልጣኔ ለመሸጋገር የሚደረገውን ህጋዊ ጥረት የሚያግዝ እንጂ ህወሃት/ኢህአዴግ እንደሚለው ህገ-መንግስት ለመናድ የሚደረግ ግርግር አይደለም:: የህወሃት/ኢህአዴግ ፕሮፖጋንዳ ግብ ህዝብን አሸብሮ ፈርቶ እንዲገዛ ማድረግ ነው:: መብት ለማስከበር እና የዴሞክራሲ ስርዓት ለመገንባት መፍትሄው ደግሞ አለመፍራት ነው:: ስለዚህ በአገር ውስጥ እና ካገር ውጭ የሚኖሩ ዜጎች እና ባለሙያዎች “የሚሊዮኖች ድምፅ ለመሬት ባቤትነት” በሚለው ታሪካዊ ዘመቻ በብዛት በመሳተፍ ማህተማቸውን ማስቀመጥ ያለባቸው ይመስለኛል::


‹‹ስንቅ›› መጽሔት

በአብርሃም ግዛው ኢንተርቴይመንትና ፕሬስ ስራዎች ኃ/የተ/የግ/ማህበር የሚዘጋጅ የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ፖለቲካዊ ኪነጥበብ ፋሽንና ሞዴሊንግ ዙሪያ ትኩረት የምታደርግ ወቅታዊና አነጋጋሪ ጉዳዮችን የምትይዝ ተወዳጅ መፅሔት በቅርብ ቀን ይጠብቁ።

ምርትዎንና ድርጅትዎን ያስተዋውቁ
ለበለጠ መረጃ በስልክ ቁጥር
0912 37 40 14

# ኑሮ ሆነብን እሮሮ

ጋሻው መርሻ

እንዴት ሰነበቱ ወዳጆ! ሰላምና ጤና ይመኙላችኋል! ማን ካሉኝ መላው ህብረተሰቡ አልለዎትም፡፡ ህብረተሰቡማ ለራሱ የሌለውንና የማያውቀውን ሰላም እንዴት አድርጎ ለዕርስዎ ይመኛል ብለው ነው?

ሰላም ጤና ቢሉት ሰላም የት ተገኝቶ?

በዚያ ደግ ዘመን ተኑሮ ተፈጂቶ፡፡


አለች ያለችው ሴትዮ፡፡ ደግነቱን አብዝቶ የሚያውቅበት መንግስታችን ዋናው ሰላም ነው፤ ሌላው ሁሉ ትርፉ ገብስ ነው እያለንማ አይደል፡፡ ኧረ ገብስም ቢሆን ባተረፍን እንዳይሉ ወዳጆ፡፡ ገብስስ ቢሆን ሰላም ከሌለ እንዴት ተደርጎ በሶ ሆኖ ይጠጣል? ለነገሩ አፍሪካ ብሎ ሰላም የት የምናውቀውን ነው? የጥይት ድምጽ እንደ ክላሲካል ስናዳምጥ ያደግን አይደለምን? የክላሽ-እንኮብ ድምጽ እንደ ባቂላ ዱቤ በአናታችን ላይ ሲንጣጣብን ላደግን ልጆች ሰላም ማጣት ምናችን ነው? የአፍሪካ ቅል እራስ መሪዎች በዚያ ሰሞን ተሰብስበው 2020 አፍሪካን ከመሳሪያ ጩኸት ነጻ እናወጣታለን አሉ ሲባል የሰማ ጓደኛየ እንዲህ ሲል አላገጠ፡፡ ቻይናዎች በ2020 ሳይለንሰር የተገጠመለት (የድምጽ ማፈኛ ያለው) መድፍ ለመስራት እቅድ አላቸው እንዴ?

ለተወዳዳሪዎቻቸው የፈለጉትን ወንበር አሁን ማግኘት አይችሉም እባክዎን ከጥቂት አስርት አመታት በኋላ ይሞክሩ የሚሉት የአፍሪካ መሪዎች አህጉሪቱን ከመሳሪያ ጩኸት ነጻ እናደርጋታለን ማለታቸው በቁም ከማለም በምን ይለያል፡፡ ድንቁም ከመሳሪያ ጩኸት ነጻ! የት ሀገር ሂጄ ልፈንዳ አለች እንቁራሪት፡፡ እንቁራሪቷም ጂላጂል ነገር ናት ለመፈንዳት ደግሞ የምን መሰደድ አስፈለጋት እዛው ያለችበት ሆና አትፈነዳም እንዴ፡፡

እነዚያ ያላሉት ነገር የሌላቸው ሀዋሪያትስ ‹‹ከእራብ ጦር ይሻላል!›› ብለው አልነበር እንዴ? የራበው ህዝብ መሪውን ይበላል እንዲሉ የፖለቲካ ሳይንሱ ሀዋሪያ መረራ ጉዲና፡፡ የመረራ ትንቢት ግን ጉድለት አለው፡፡ ህዝቡ መሪዎቹን እንዴት እንደሚበላ ቢነግሩን መልካም ነበር፡፡ ለነገሩ ህዝቡ መሪዎቹን ልብላ ቢል ለብዙ አመታት ሊያኖረው የሚችል ስጋ ተሸክመዋል፡፡ ቀሳውስቱ የሚበላና የማይበላ ብለው የከፋፈሏቸው እንስሳት ያስጨነቀው አንድ ግለሰብ ቄሱን እንዲህ ብሎ ይጠይቃቸዋል፡፡ ቄሴ ጅብ የነከሰው እንስሳ ይበላል ወይስ አይበላም ሲል ይጠይቃቸዋል፡፡ ቄሱም ‹‹ሲርብ ነው ሳይርብ›› ይሉታል፡፡ ጠያቂው ሲርብ ብሎ ይመልስላቸዋል፡፡ አይ ልጄ ከራበማ ጂቡም ይበላል አሉት አሉ፡፡ ይኼኔ ነው የዶክተር መራራ ትንቢት ወደ እውነት የሚጠጋው አሉ፡፡ በትክክል!

የሆነው ሆኖ መንግስታችን ዋናው ነገር ሰላም ነው፤ ለዚህ ሰላማችሁ ደግሞ ወጣትነታችን ሰውተናልና ‹‹እልል በቅምጤ›› ብላችሁ ተቀበሉን እያለን ይገኛል፡፡ እውነታቸውን ነው አስራ ሰባት አመት ሙሉ ቆንጠር ለቆንጠር እንደ ዝንጀሮ እየዘለሉ የታገሉለት አላማ ይህ የዝምታ መታመም አይደለም እንዴ? ዝምታ ሁሉ ሰላም ነው ይላል መጽሃፈ አብዮታዊ ዴሞክራሲ የመጨረሻው ምዕራፍ፡፡ ወገኖቸ የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ነገር አይገርማችሁም? እንዲያ ስንቱን ጉምቱ ጉምቱ ባለስልጣን የእውቀት መለኪያ ሆኖ ሲያስጨንቀው እንዳልነበር ዛሬ ‹‹አብዮታዊ ዴሞክራሲ የሚባል ነገር የለም!›› ሲባል ደቀ መዛሙራቱ ምን ዋጣቸው ይሆን? የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ነገር አልሆንልሽ ያላቸው ወይዘሮ ገነት ዘውዴ አብዮታዊ ዶሞክራሲ ምንድን ነው ተብለው ሲጠየቁ እንዲህ ነበር ያብራሩት “አብዮታዊ ዴሞክራሲማ አብዮታዊ ዴሞክራሲ ነው” ድንቅ ማብራሪያ ነው፡፡ ፈጣሪዎቹ እነ ሌኒንም ቢሆን እንዲህ አድርገው ያብራሩት አይመስለኝ፡፡ ከሾሙ አይቀር እንዲህ አይነት እሳት የላሰ የፖለቲካ ተንታኝ ነው እንጂ፡፡

ለመሆኑ ኑሮ እንዴት ይዞታል! ስፍት አድርጎ ካሉ በትክክል መልሰውታል፡፡ ካለዚያ ግን ብር በጉድጓድ ይቀብሩ ነበር ማለት ነው፤ወይም ደግሞ የእነ ገብረዋህድ ወዳጅ ነበሩ ማለት ነው፡፡ እዚች ጋር አንድ ጥያቄ ጣል ብናደርግስ፤መልስ የለም እንጅ ጥያቄማ የት ጠፍቶ፡፡ ለመሆኑ ብር በጉድጓድ ሲቀብሩ የነበሩት ሰዎች ጉዳይ ምን ላይ ደረሰ? እንደው የአንድ ሰሞን ጫጫታ ሆኖ አለፈ እንዴ? እንግዲህ የዘንድሮ ኑሮ እኮ በአስራ አንድ ነጥብ ሁለት ቁጥር ሚስማር ነው ከችግር ጋር አጣብቆ የያዘን፡፡በዚያ ሰሞን አንድ ሰማያዊ የሚሉት እነ አቦይ ስብሀት ነጋ የማያውቁትና የሚፈሩት ፓርቲ በኑሮ ውድነት ዙሪያ ሰልፍ አዘጋጅቻለው ኑና የተኛውን መንግስት በጩኸት እናባንነው ሲለን ጊዜና ስራ ፈቶ የከረመውን አፌን በመፎክር ላፍታታው ብየ!



ኑሮ ሆነብን እሮሮሮሮሮ..... የምትል ጥቅስ ቢጤ ይዤ ከጧቱ 12 ሰዓት የሰልፉ ቦታ ደረስኩ፡፡ እንዴት በዚያ ሰዓት ደረስክ ብለው ጠየቁኝ ወዳጆ፤ ባይጠይቁኝም አብራራለው፤ ነገሩ እንዲህ ነው የአንድ ብር ከሃያውን የሸዋ ዳቦ ለምሳዬ ልገዛ አምስት ኪሎ ሄጄ የዳቦ ሰልፍ ይዤ ነበር፡፡ ይህ የዳቦ ሰልፍ እንደ ዘንዶ ወገብ እየተጠማዘዘ ግንፍሌ የሚገኘው የሰማያዊ ቢሮ ለመድረስ የቀረው አንድ እርምጃ ነበር፡፡ ይህን የዳቦ ሰልፍ ቀኝ ኋላ ዙር ብየ በቀጥታ ወደ ሰላማዊ ሰልፍ ቀየርኩት፡፡ እኔ ፊት ለፊት ሆኘ ‹‹ኑሮ!›› ሲል ተከታዮቼ ‹‹ሆነብን እሮሮሮ....›› እያሉ ሲቀበሉ ሁሉ ሰልፉችን ተቀላቀለው፡፡ ይችን ጥቅስ ከፍ አድርጌ በማያዝ ኑሮ የከበደውን ሁሉ በዙሪያዬ ሳሰልፈው ጋዳፊን የሆንኩ ያክል ነበር የተሰማኝ፡፡ ጋደፊ በመጨረሻ በበረሮና በቀበሮ ሊከበብ በፊት በፊት በቆነጃጅት ተደግፎ ነበር አሉ የሚጓዘው፡፡ ኧረ አንዳንዶችስ ስሙም ጋዳፊ የተባለው በቆነጃጅት ተደግፎ በመዋሉ ነው ይላሉ፡፡

ለማንኛውም ያን ቀን የከበበኝን ህዝብ ይዤ ወደ ቤተ መንግስት ባቀና ኖሮ እስካሁን እንዴት አይነት እሳት የላስኩ ነጋዴ እሆን ነበር፡፡ እሳት የላስኩ ሲባል ግን አይገርማችሁም! እሳት ግን ምኑ ይላሳል? መቸም ነጋዴ ቤተ መንግስት ውስጥ ምን አለው የሚል ልማታዊ ጠያቂ አይጠፋም፡፡ ከውጭ ሲያዩት መደዴ የመሰለው ሁሉ አይደል እንዴ ቤተ መንግስት ገብቶ እፍ ያለ ነጋዴ የሆነው፡፡ ካላመናችሁ ሂዳችሁ አጣሩ፡፡ አንዳንዶች የባሰባቸው አሽሟጣጮችማ አይደለም ቤተ መንግስት የገባ ይቅርና ገብተው የሚወጡትን ሰላም ያለ እንኳን በደቂቃ ነው ባለ ሀብት የሚሆነው ሲሉ ብሰማ አቤት ውሸት አላልኩም፡፡ ምክንያቱስ አለ ስብሀት ገብረ እግዚአብሔር ያላረጋገጥኩትን ነገር እንዴት ብየ ነው ውሸት ለማለት የምደፍረው? በዚህች እውነትና ውሸት በማይለይባት ሀገር እየኖርኩ እንዴት ብየ ማረጋገጥ ይቻለኛል?

ለነገሩ እኔ የመረጋገጥ እንጂ የማረጋገጥ አቅሙም የለኝም፡፡ ለምሳሌ ከሰሞኑ መብቴን አረጋግጣለው ብየ ሰልፍ ወጥቼ በፖሊስ እንዴት እንደተረጋገጥኩ ስነግራችሁ በኢቲቪ እውነት ነው፡፡ ደግሞ እዚህ ሀገር የማይሰራ ታምር አለ እንዴ ወዳጆ? ድንገት አይንዎትን ጭፍን አድርገው ሲገልጡት ፎቅ በቅሎ የሚገኝበት ሀገር አይደል እንዴ? ይሄው በዚያ ሰሞን ታክሲ ተሳፍሬ ከሀያ ሁለት ወደ መርካቶ ሳቀና ባዶ የነበረ ቦታ መርካቶ ደርሸ ስመለስ አንድ ባለ አስር ፎቅ ህንጻ ተገትሮ አልጠበቀኝም መሰላቹ!? የት ነው እንዳትሉኝ ሰው ነው ሲያወራ የሰማውት፡፡ የዛሬ ሰው እህ ብለው ከሰሙት እንደ ኢቲቪ የማያወራው የለውም፡፡ ለነገሩ ኢቲቪ እህ ብለው ሰሙትም አልሰሙትም ማውራቱን አያቆምም፡፡

ወዳጆ እንደው የኢቲቪ ነገር ግን አይገርመዎትም፡፡ እንደማንሰማው እያወቀ ለምንድን ነው የሚያወራው? አንድ ጓደኛዬ ጋር ስንደዋወል ኢቲቪ ማየት እንደሚያስደስተው ይነግረኛል፡፡ በጣም ገርሞኝ ከኢቲቭ የሚያገኘውን ቁም ነገር ስጠይቀው ባክህ የጭንና ሳሙና ማስታወቂያ ማየት ስለሚያስደስተኝ ነው ብሎኝ እርፍ፡፡ ባይሆን በውኑ ላገኘው የማልችለውን የምግብ አይነት ኢቲቪ ላይ አምሮቴን ልወጣ ብየ ነው አላለኝም መሰላቹ፡፡ እስኪ አስቡት ሽሮ ለጠረረበት ሰው ስለ ቴስቲ ሶያ ጣፋጭነት መደስኮር ምን የሚሉት ነገር ነው፡፡ ኢተቪ ሆይ የምንከታተልህ ወሶች እኮ አይደለም ቴስቲ ሶያ ዲሽ እንኳን መግዛት አቅቶን ነው እንዲህ የምትጫወትብን፡፡

አይ የኔ ነገር የተነሳውበትን ርዕስ እኮ ስቶ ልገለበጥ ስል ነው የባቡሩ ድልድይ ያስቀረኝ፡፡ ለመሆኑ ጤናዎ እንዴት ነው፡፡ እድሜ ለዚህ ከንዋታ መንግስት እንጂ ስንት ጤና ጣቢያ በየ ሰፈራችን ተገንብቶ የወሊድ መከላከያና ኮንዶም በማደል ጤናችንን እየተንከባከበ አይደለም እንዴ? ኮንዶም ማደል ነው እንዴ ትልቁ የጤና ጣቢያ ስራ እንዳይሉ ወዳጆ? ዋናው ነገር ኮንዶም ነው፡፡ እኛ ሀገር እኮ እርሀብን ሳይቀር በኮንዶም ነው የምንከከለው፡፡ እዚህ ጋር ቀልድ መሰል ቁም ነገር ጣል እናድርግባና እንለፍ፡፡

እንደ ዛሬው ቀኑ ሳይከፋ አንድ የሰፈራችን ጎረምሳ ሽሮ መብላት ስልችት ይለውና ለእናቱ ‹‹እማየ ሁሌም ሽሮ መብላት ኤድስ ያስይዛል ሲባል ሰምቻለውና ዛሬ በሽሮ እንዳትሰጭኝ!›› ይላቸዋል፡፡እናትየዋም የዋዛ አልነበሩምና ‹‹አይ ልጀ በኮንዶም ቢሆን ትበላታለህ እንጂ ማን ይለቅሃል!›› አሉት አሉ፡፡ከሆነ ጊዜ በኋላ ያን ልጂ አግኝቸው እንዲህ ብለሃል ሲባል ሰምቸ እውነት ነው ብየ ስጠይቀው ስልችት ባለ አነጋገር ‹‹አሁንስ እንኳን ኤድስ ያስይዛል ይቅርና እንደበላሽው ትሞታለህ እንኳን ቢሉኝ የምለቀው አይመስለኝም!›› ብሎ መልሶልኛል፡፡

# የኢትዮጵያ ፖለቲካና የሴቶች ተሳትፎ

ኤልሳቤት ወሰኔ

ሴቶች በኢትዮጵያ ታሪክ አንጸባራቂ ሚና መጫወታቸው በታሪክ ተዘግቦ ይገኛል። ከንግስት ኢሌኒ ተነስተን እስከ እትጌ ጣይቱ ብጡል ድረስ ያለውን ብንመለከት እነዚህ ሴቶች የአገር ሉዓላዊነትንና ነጻነት በማስጠበቅ የተወጡት ሚና ከአጼ ምኒልክ ያልተናነሰ እንደነበር ጥቂቶችም ቢሆኑ የታሪክ ጸሃፊዎች ይናገራሉ። የአገርን ነጻነት ለማስጠበቅ ከቁስለኛው ጋር፣ ከጦረኛው ጋርም ብዙዎቹ ሴቶች አብረው ይዘምቱ ነበር። በጦርነቱም አብረው ተጎድተዋል። ተፋልመዋል። ይህን መሰል ታሪክ የሰሩት የኢትዮጵያ ሴቶች በርካቶች ናቸው። ይሁንና በኢትዮጵያ ታሪክ የወንዶቹ ሚና ጎልቶ ሲወጣ የሴቶች ሚና ጎልቶ አይታይም።

አንድ አገር በዴሞክራሲ፣ በፍትህ፣ በልማትና በሌሎች መስኮች በስልጣኔ እንድትጓዝ ሴቶች የሚኖራቸው ሚና ቀላል አይደለም። ሴቶች ከወንዶች እኩል የሆኑባቸው እንደ ስዊድን፣ ኖርዌይ ያሉ አገራት በአብዛኛው መስኮቻቸው በዓለም ቀዳሚ የሆኑት ሴቶች ተሳትፎ ምክንያት ነው። በአንጻሩ እንደ ኢትዮጵያ ያሉ አገራት ወደ ኋላ የቀሩት የሴቶች ተሳትፎ ባለመኖሩ ነው። ሴቶች ለፖለቲካው ተቀባይነት አላቸው። በ1997 መጀመሪያ ቅድሚያ የተሰለፉት ሴቶች ናቸው። በኢህአፓ ዘመን ትልቁን ሚና የነበረቻው ሴቶች ናቸው። እነዚህ ሴቶች ግን አልተጻፈላቸውም። በአሁኑ ወቅት ብናይ እንኳ ርዕዮት ታጋይ ነች። ርዕዮት ሰርቃ ሳይሆን የታሰረችው ለዴሞክራሲ ባደረገችው አስተዋጽኦ ነው። ትናንት ብርቱካን ነበረች። ዛሬ ሴቶች አሉ። ዛሬም ጠንካራና ታጋይ ሴቶች አሉ። ሴቶች በፖለቲካው ተሳትፎም ሆነ በሌላ መስክ ተቀባይት ቢኖራቸውም የሚተረከው ግን ለወንዶች ብቻ ናቸው።

አልተጠቀምንበትም እንጂ ሴቶች ትልቅ ኃይል አላቸው። አንዲት ሴት ከአንድ ወንድ የተሻለ ፖለቲካውን የመለወጥ፣ የመሳብና አስተዋጽኦ የማደርግ አቅም ይኖራታል። 100 ወንዶች ሰላማዊ ሰልፍ ከሚወጡ መቶ ሴቶች ሰላማዊ ሰልፍ ወጥተው የተሻለ ተጽዕኖ ማምጣት ይችላሉ። በተለያዩ ምክንያቶች ወንዶችም ይሁኑ ሴቶች ተከትለዋቸው ይወጣሉ። የኢትዮጵያን ፖለቲካ ከወንዶች በላይ ሴቶች መቀየር ይችላሉ። ይቅር ባይ ናቸው። ጨካኞች አይደሉም። እናት እንደመሆናቸው ለሌሎች ያስባሉ። ብልህ፣ አስተዋይና አስታራቂዎችም ናቸው።

ኢትዮጵያ ውስጥ ህዝቡ ደስታ የራቀውና ሰብአዊ መብቱ የማይከበር ለመሆኑም የሴቶች ተሳፍቶ አለመኖር እንደሆነ በምክንያትነት መጥቀስ ይቻላል። ከአርበኝነት፣ ከጀግንነትና ከፖለቲካ ተሳትፎ ውጭ የምናውቃቸው እናቶቻችንም አሉ። ልጅ ማሳደግ፣ ቤትን ማስተዳደር፣ ልብስ ማጠብ፣ ምግብ ማዘጋጀትንና የመሳሰሉት ሚናዎች ቀላል ስራዎች አይደሉም። አንዲት እናት ልጅ ወልዳ ልጇን ለቁም ነገር እስክታበቃ ድረስ በርካታ ፈተናዎች ይገጥሟታል። ይህን ሁሉ መከራ አልፈው አሳድገው በደርግም ሆነ በአሁኑ ወቅት በስደትም ሆነ በሌሎች መከራዎች ልጆቻቸው በርሃ ላይ ይቀሩባቸዋል። እነዚህ ሴቶች መከራው ምንም ያህል ቢከብድምና የድካማቸውን ዋጋ በሚገባ ባያገኙም ጀግናዎች ናቸው።

ኢትዮጵያውያን ሴቶች በፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህራበራዊ መስኮች በርካታ ታሪኮችን ሰርተዋል። ለምሳሌ ያህል ንግስተ ሳባ በመንግስት አስተዳደርና በአመራር ጥበብ ለኢትዮጵያውያን ብቻ ሳይሆን ለዓለም ሴቶችም ምሳሌ የሆነች ሴት ነች። ንግስት ኢሌኒና እትጌ ጣይቱን የመሳሰሉት የአገራችን ሴቶች በአመራር ጥበባቸው፣ በጀግንነታቸው የተመሰከረላቸው ናቸው። ወይዘሮ የሸዋ ረገድ ገድሌ በጣሊያን ወረራ ወቅት ለጀግኖቻችን ምግብና ውሃ በማቀበል፣ የጦርነት አካባቢውን ቦታ በማሰስና መረጃ በማቀበል ትልቅ ጀብዶችን ሰርተዋል። ስለ ሸዋረገድ ገድሌ ተግባርና ተጋድሎ በርካታ ሰዎችን ብጠይቅም ይችን ጀግና የሚያውቃቸው ግን ጥቂቶች ብቻ ናቸው። በጣሊያን ወረራ ወቅት ግን እኒህን ሴት የማያውቅ ሰው አልነበረም ማለት ይቻላል። በትምህርት መስክ ከወንዶች ጋር እኩል እድል እንዲያገኙ ትልቅ ጥረት (ትግል) ያደረጉት ወይዘሮ ስንዱ ገብሬም ሌላኛዋ ጀግና ሴት ናቸው። ዮዲት እምሩም ሌላኛዋ ጠንካራ ሴት ነበሩ። በደርግና ኢህአዴግ ዘመንም በፖለቲካው በሌላው መስክ ጠንካራ ተሳትፎ ያደረጉ ሴቶችን እናገኛለን።



## ሴቶች ለምን የፖለቲካ ተሳትፏቸው ቀነሰ?

የኢትዮጵያ ሴቶች የፖለቲካ ተሳትፎ ለምን ዝቅ አለ? ለምን በፖለቲካ ተሳትፎው የለንም? ብዙዎቹ ወንዶች እህት፣ እናት፣ ወይም ሚስት አላቸው። እነሱ ወደ ፖለቲካው መድረክ ሲመጡ ግን ሴት የለችም።

የሴቶች ችግር አጠቃላይ የሀገራዊ ችግር ነው። ይህ ችግር ኢኮኖሚያዊ፣ የባህል፣ የሴቶችና የወንዶች ማህበራዊ ክፍፍል ደረጃም ችግር አለበት። ከአስተዳደጋችን ጀምሮ ቤተሰብ ለወንድ ዶክተርና ሌሎች የስራ መስኮችን ሲመኙለት ለሴት ልጅ ግን የሚመኙላት የቤት አስተዳዳሪ፣ ልጅ አሳዳጊነት፣ ወጥ ሰሪና እንጀራ ጋጋሪነትን ነው። ሴቶች የወንድ ረዳት እንዲሆኑ እንጂ ራሳቸውን ችለው ትልቅ ቁም ነገር እንደሚያደርጉ አይደለም። ባህላችን ሴቶች ረዳት፣ አጋዥና ታዛዥ እንጅ በራሳቸው ለራሳቸው፣ ለቤተሰባቸው፣ ለዓለም ትልቅ ቁም ነገር ያበረክታሉ ብሎ አላስተማሩንም። ይህም የአገራችን ማህበራዊ ክፍፍል ደረጃ ሆኖ ተለምዷል። አስተዳደጋችን ትልቅ ችግር ፈጥሮብናል። ሴት አገልጋይ እንጂ ወንድን ወክላ ወይንም በራሷ ሚና የምትጫወትበት ባህላዊ መሰረት የለንም። ከአገራችን የተለያዩ አካባቢዎች ከአካባቢ አካባቢም፣ ከስርዓት ስርዓት ለሴቶች የሚሰጥ ክብርና ባህል አለን።

በአሁኑ ወቅት ሴቶች ከወንዶች ያላቸው ምጥጥን (ሬሾ) 51 በመቶ እንደሆኑ ይነገራል። ይህ ከግማሽ በላይ የሆነው ህዝብ ካልታገለ ዴሞክራሲና ሰብአዊ መብትን ማስከበር አይቻልም። ከምንም በላይ ሴቶች ልጆቻቸውን፣ ጓደኞቻቸውንና ባላቸውን ያሳምናሉና ይህም ለትግሉ ትልቅ አስተዋጽኦ ማድረግ ይችል ነበር።

ከእኛው አገር በላይ የባህልም ጭቆና አለበት በሚባለው የአረብ አገራት ሴቶች ከፍተኛ ተቃውሞ እንደሚያደርጉ በዓረብ አገራት የተደረጉ አብዮቶች ላይ አይተናል። ይህን የእኛውን አገር ችግር ከባህልም በተጨማሪ ሌሎች ስልታዊ ጭቆናዎች እንዳሉበት አመላካች ነው። ይህ ጭቆና እያለ ግን የሴቶች ተሳፍሮ መቀነስ ከራሳቸው ከሴቶች የመነጨ ችግር ተደርጎ ሲወሰድ ማየት የተለመደ ነው። ሴቶች ሲጨቆኑም ሆነ ችግር ሲደርስባቸው የራሳቸው ችግር ተደርጎ ይወሰዳል። በተለያዩ ምክንያቶች የአሁኑ ሴቶች ተሳትፎ ባነሰ ቁጥር የድሮዎቹም እየደበዘዙ ይመጣሉ። ኢትዮጵያ ውስጥ ቀዳሚው ሚና ያላቸው ወንዶች በመሆናቸው የምንሰማው፣ የምናነበው፣ የሚዘከረው የወንዶችን ታሪክ ነው። ለወንድ የሚስበውና ይበልጡን ውስጡ የሚኖረው የወንዱ ነው። የጣይቱን ታሪክ ከወንዶች በላይ ሴቶች ሊጽፉት ሊዘክሩት ይችሉ ነበር። ሆኖም የሴቶች ተሳትፎ በመቀነሱ ምክንያት መዘከራቸውም ቀንሷል።

የቀደሙት አባቶቻችን ሴቶቻችንን ‹‹ትችያለሽ›› ብለው እስከማማከር ደርሰዋል። ለአብነት ያህል አጼ ምኒልክ እትጌ ጣይቱን ‹‹አውሉምን ምን ላድርገው ብለው አማክረዋታል።›› እቴጌ ጣይቱ እንደምትችል ተማምነውባታል። ይህ በመሪዎቻችን መካከልም ያለ ችግር ነው። እትጌ ጣይቱ አውሎምንና ሌሎች ባንዳዎች ለኢትዮጵያ አገራቸው ታሪክ ሰርተው እንዲያልፉ የማይተካ ዲፕሎማሲያዊ ስራ ሰርተዋል። በዚህ ዘመን ግን የሴቶችን ታሪክ የመዘከረና የማስታወስ ባህላችን እጅግ ዝቅተኛ ነው። በአገራችን ቴዎድሮስ በሚባል ስም የሚጠሩት በርካቶች ናቸው። ሆኖም ለእትጌ ጣይቱ ማስታወሻነት ሴት ልጆቻቸውን ጣይቱ ብለው የሚጠሩ እናትና አባቶች በጣም ጥቂቶች ናቸው። አንዳንዴ የሉም ማለትም ይቀላል። ጣይቱ የሰራችው ትልቅ አኩሪ ገድል ቢሆንም እናቶች እንኳ ልጆቻቸውን በዚች ጀግና ስም ሲጠሩ አይታይም። ታሪካቸውን በመጻፍና በሌሎች ጉዳዮች በማስታወስና በመዘከርም ተመሳሳይ ችግር ይታይብናል። ቴዎድሮስ ታላቅ ስራ እንደመስራቱ በታሪክ ይዘከራል። ራሱን አጼ ቴዎድሮስ ገናና እንዲሆን ግን ተዋበች ትልቅ አስተዋጽኦ አድርጋለች። የእናቱ ታሪክም ቢሆን ቀላል የሚባል አይደለም። ቴዎድሮስ ሲታወስ ከእሱ ጋር የተሳተፉ ወንዶች ካልሆኑ በስተቀር እነዚህ ሴቶች ግን በስፋት ሲታወሱ አይታይም።

ይህ ሴቶቻችንን በየ መስኩ የቀዘቀዘ ተሳትፎ እንዲያደርጉ አድርጓቸዋል። ሴቶቻችንን ማደፋፈር ያልቻልንበት አንዱ ምክንያት ቀደምት ሴቶች የሚገባቸውን ክብር ባለማግኘታቸው ነው። በአገራችን በርካታ ታሪኮችን የሰሩት እነ ጣይቱና ሸዋረገድ ገድሌ የመሳሰሉ ሴቶቻችን አንድ ገጽ በማይሞላ የመማሪያ መጽሃፍ ከመጠቀሳቸው ውጭ ይህን ያህል የሚዘከሩበት ነገር አልተቀመጠላቸውም፤ አልተሰራላቸውም። ይህም የአሁኑን ዘመን ሴቶች ደፍረው ወደ ትግሉ እንዳይገቡ አድርገዋቸዋል።

## ኢህአዴግና የሴቶች ጭቆና

በእርግጥ የኢትዮጵያ የሴቶች ችግር አጠቃላይ የህዝብ ችግር አንድ አካል ነው። ዴሞክራሲ፣ ፍትህ፣ እኩልነት፣ ነጻነት የሴቶችም ሆነ የቀሪው ኢትዮጵያዊ ችግር ነው። ያም ሆኖ ግን ሴቶቻችን ከእነሱ ያነሰ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ማህበራዊ አስተዋጽኦ ባላቸው ወንዶች ጭቆና ይደርስባቸዋል። እኔ በበኩሌ ጥሩ የሴቶች ጨቋኝ አድርጌ የምወስደው ኢህአዴግን ነው። ኢህአዴግ ስልጣን ሲያዝ ለስልጣን ያበቁት በርካታ ሴቶች አብረው መጥተው ነበር። ኢህአዴግ ስልጣን ከያዘ በኋላ ግን እነዚህ ስልጣን እንዲይዝ ቀላል የማይባል አስተዋጽኦ ያደረጉት ሴቶች ስልጣን ላይ የሉም። ሴቶቹ ምንም አይነት የእውቀትም ሆነ ሌላ ችግር ሳይኖርባቸው ወንዶች ሴቶቹን ገፍትረው ነው ያባረሯቸው። ከወንዶቹ እኩል መሳሪያ ተሸክመው፣ ወጥተው ወርደው፣ ደክመው፣ ቆስለው፣ ሞተዋል።

አዲስ አበባ ከገቡ በኋላ ወንዶቹ ስልጣን ሲይዙ ሴቶቹ የሚገባቸውን ስልጣን አላገኙም። ይህ ለምን ሆነ ብዬ የህወሓት ታጋይ የነበሩትን ሴቶች ጠይቄያለሁ። ጋዜጣና መጽሄት ላይም የሰጧቸውን ቃለ ምልልሶች አንብቢያለሁ። ብዙዎቹ ሂዱ ብለው ከስልጣን ሲያገልሉን ‹‹ለዚች አገር እኩል ነው የደማነው፣ የቆሰልነው አንሄድም ማለት ነበረብን›› ነው የሚሉት። ይህን የሚሉት ግን ከ20 አመት በኋላ ነው። እንደ ሴት እኩል ነን ብለን ካላሰብን ችግሩ የሚጀምረው ያኔ ነው። ሰው በመሆናችን እኩል መሆናችንን ካሰብን በሁሉም መንገድ አጥጋቢ ውጤት እናስመዘግባለን።

ወይዘሮ የውብ ማር አሰፋ የአቶ ገብሩ አስራት ባለቤት ናቸው። በህወሓት ክፍፍል ወቅት ገና ገብሩ አስራት ከእነ መለስ ቡድን በሃሳብ ተነጥለው ሲወጡ ከባለቤታቸው ጎን ይቆማሉ ብለው አንገላትተዋቸዋል። ይህን የውብ ማር እውነታ በርዕዮት አለሙ

ወደ ገፅ 15 ይዞራል

# ሰላማዊ ትግሉ መሪዎቹን ይሻል



ታምራት ታረቀኝ

ባለፈው ሳምንት በፖለቲካውም ማለባበስ ይቁም በማለት በርግጥ ለውጥ የምናልም ድል የምንናፍቅ ከሆነ ከመጣንበት መንገድ ወጣ ብለን በእውነትና በድፍረት እንነጋገር፣ ማለባበሱ ይቅርና ገልጠን ገላልጠን እንይ እንተያይ በማለት የወቅቱ አብይ ጉዳይ በሆነው የፓርቲዎች የመተባበር/የመዋሀድ ጥያቄ ላይ ትኩረቴን አድርጌ አስተያየቴን ሰንዝሬ ሌሎችም የምትሉትን በሉና እንነጋገር ብዬ ነበር፡፡

እንግሊዛዊው ፈላስፋ ጆን ስቴዋርት በ1859 የጻፉት ተብሎ የሚጠቀሰው «በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ዜጎች በሚናገሩት ግልጽ በሆነ የሀሳብ ልውውጥ አማካኝነት ሀሰት እየኮሰመነች እውነት ደግሞ እያበበች ጎልታ የምትታይበት መድረክ ይፈጠራል፡፡ የሌሎች አስተሳሰብ ግልጽ እየሆነ ይሄዳል፡፡ መቻቻል የሚፈልጉት ጉዳዮች ቁልጭ ብለው ይታያሉ፡፡ ሰለዚህም የእድገት ጎዳና ይከፈታል፡፡» የሚለው ዘመን የማይሽረው ግዜ የማያስረጀው አባባል በፖለቲካውም ማለባበስ ይቁም በማለት ያነሳሁትን ርዕሰ ጉዳይ በበቂ የሚያጠናክርልኝ ነው፡፡ ለዛሬም በርእሱ በጠቀስኩት ጉዳይ ላይ በግልጽ እንነጋገር ዘንድ የሚከተለውን ብያለሁ፡፡

ለእውነት ሳይሆን ለቅርበት ማድላት፣ በእምነት ሳይሆን ጥቅም በመሻት መስራት፣ ለዓላማ ሳይሆን ለግለሰቦች መገዛት በዚህም ምክንያት እውነትን እየረገጡ ሀሰትን እያገነኑ መጓዝ ትግላችንን ከማክበድና መስዋዕትነቱን ከማብዛት ውጪ የፈየደው ነገር የለም፡፡ ስለሆነም ትግሉ ለድል እንዲበቃ አሊያም አላስፈላጊ መስዋዕትነቱ እንዲያበቃ «አለባብሰው ቢያርሱ በአረም ይመለሱ» ነውና መጋረጃውን እየገለጥንና ክንብንቡን እየገፈፍን በእውነትና በድፍረት እንነጋገር፡፡

እያንዳንዱ ተግባር የራሱ የሆኑ በከፊል ወይንም በሁለንተናዊ መልኩ ከሌሎች የሚለይባቸው ባሕርያት ይኖሩታል፡፡ መሪዎችም እንደ ተግባሩ ባህርይ የተለያየ ችሎታና እውቀት ያላቸው ይሆናሉ፡፡ ሁሉም ሰው ለሁሉም ሥራ በመሪነት ሊሰለፍ አይችልም፡፡ በመሆኑም ሠላማዊ ትግልም የራሱ ባህርያት አሉትና የራሱ የሆኑ ወይንም በሂደት ሊሆኑ የሚችሉ መሪዎች ያስፈልጉታል፡፡

ሠላማዊ ትግል ሳይገሉ እየሞቱ (ለሞት ራስን አዘጋጅቶ) የሚከናወን የአስተሳሰብ ትግል ነው፡፡ በመሆኑም ለድል ይበቃ ዘንድ የጠለቀ እውቀት ግልፅ አቋም አንድነትና የመንፈስ ፅናት ያላቸው መሪዎች ይፈልጋል፡፡

የአጭር ግዜ የሥልጣን ህልምን ለማሳካት የታለመ ወይንም ቁሳዊ ጥቅም ማግኛ ተደርጎ የሚከናወን ሳይሆን ትውልድ ተሻጋሪ ድል ሊያቀዳጅ የሚችል ራዕይ አንግበው ለዓላማቸው ስኬት ከምቾት ባሻገር ለመታገል ወስነው ሳንገል እየሞትን ብለው በቁርጠኝነት የተሰለፉ መሪዎችን ሲያገኝ ነው ድል ለማብሰር የሚበቃው፡፡

ሠላማዊ ትግል በራስ ላይ እንዲሆን የማይፈልጉትን በሌላ ላይ የማይፈጽሙበት ሊያደርጉ የማይችሉትን ከሌላ የማይጠብቁበት በፍቅር የሚያሸንፉበት እንጅ ጥላቻ የማይዘሩበት፣ የአስተሳሰብ ልዩነትን በስሉጡን ፖለቲካዊ መንገድ በውይይት በክርክርና በማቻቻል የሚያስተናግዱበት ነውና ስብእናቸው ለዚህ የሚመጥንና ተቀዋሚነትንና ጠላትነትን በግልጽ የለዩና ይህንንም በተግባር የሚያሳዩ መሪዎች ያስፈልጉታል፡፡

በሰላማዊ ትግል ሥልጣን ለመያዝ የሚቻለው የሚገባውም ግልጽ ዓላማ ይዞና ሕዝብን አሳምኖ ለተፈጻሚነቱ በጽናት እየታገሉ በተግባር ልቆ ወይንም ተሽሎ በመገኘት በምርጫ ኮሮጆ ውጤት ለአሸናፊነት በመብቃት ነው፡፡ የትም ፍጪው ዱቄቱን አምጪው በሚለው ሀገራዊ ብሂል ወይንም በምንም ይሁን በየት ዋናው አሸናፊ መሆን ነው በሚለው ማኪያቬሌያዊ ስልት በሚደረግ ትግል ሥልጣን ለመያዝ ማለም ከመነሻው ለውጤት አያበቃም፡፡ ምድራችን በተለይ ደግሞ ሀገራችን ይሆናል ተብሎ ተስፋ ከተደረገበትና ከሚጠበቀው ይልቅ አይሆንም የሚባለው የመሆን አጋጣሚ የሚታይባት ናትና በዚህ መልኩ ለሥልጣን መብቃት ቢቻል የሰዎች እንጂ የሥርዓት ለውጥ ለማምጣት አያበቃም፣ ዴሞክራሲንም አያሰፍንም፡፡ ስለሆነም ሰላማዊ ትግሉ ሁለተኛው አስተሳሰብ ካላቸው ጸድቶ የሕዝብን የሥልጣን ባለቤትነት የሚያረጋግጥ ዴሞክራሲዊ ሥርዓት ለመገንባት በሕዝብ ይሁንታ በምርጫ ለሥልጣን መብቃት የሚል እምነት ይዘው በጽናት የሚታገሉ መሪዎች ግድ ይሉታል፡፡

እነርሱ መሰረቱን ጥለው ትውልድ እየተቀባበለ የሚገነባው በማንም መቼም የማይናጥና የማይናወጥ ሥርዓት ለመፍጠር እንጂ ራስን ለሥልጣን ማብቃትን መነሻም መድረሻም ግባቸው ያደረጉና መስዋዕትነት ከሚጠይቀው ጋሬጣና እሾህ ከበዛበት መስመር እየሸሹ ሆነው ሳይሆን አስመስለው የሚኖሩ ሰዎች ሰላማዊ ትግልን መርተው ለውጤት አያበቁም፣ የተቀዋሚ መሪ እየተባሉ ከመኖር አልፈውም የሚያልሙትን የመንግሥት ሥልጣን ለማግኘት አይችሉም፡፡ የማይሆነው ሆኖ በተአምር ለሥልጣን ቢበቁ ደግሞ ያለፈውን የሚያስመሰግኑ አምባገነኖች ይሆናሉ፡፡

የሰላማዊ ትግል ዋንኛው ኃይል ሕዝብ ነው፡፡ ሕዝብ ኃያል የሚሆነውና ለድል የሚበቃው በእድሜ፣ በጾታ፣ በዘርና በኃይማኖት መለያየት ሳይፈጥር በአንድ ሀገር ልጅነት መንፈስ መሰለፍ ሲችል ነው፡፡ በመሆኑም የሰላማዊ ትግል መሪዎች በተግባራቸውም በንግግራቸውም ከከፋፋይ ተግባር የራቁ የአንድነት ተምሳሌት ሆነው በተግባር የሚታዩ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡ ሕዝብን ለሰላማዊ ትግሉ ለማሰለፍ የሚያደርጉት እንቅስቃሴም ይሁን ፕሮፓጋንዳና ቅስቀሳ ጥላቻ የሚሰበኩበት፣ ያለፈ ቁስልን እያከኩ የሚያደሙበት ሊሆን አይገባም፡፡ ይህን መሰሉ ተግባር የእለት ጭብጨባ የአንድ ሰሞን የጥቂት ሰዎች ማበረታቻ ያስገኝ ካልሆነ በስተቀር ለሰላማዊ ትግሉ ውጤታማነት አይፈይደም፣ እንዲያውም ተቃራኒውን ውጤት ነው የሚያመጣው፡፡

በራሳቸው እግር መቆም የተሳናቸው፣ ዓላማችን ብለው በወረቀት ያሰፈሩትን በተግባር ሊያውሉት ጽናቱም እምነቱም የሌላቸው ዋና ስራ የሚያደርጉት ስለ ዓላማቸው ዴሞክራሲያዊነት፣ ስለ ትግላቸው አዋጪነት፣ ሀገር ለመምራት ስለሚኖራቸው ብቃት ወዘተ ተናግሮ ማሳመንና በየቤታቸውም ትንሽ ትንሽ እየሰሩ ማሳየት ሳይሆን የተቀናቃኞቻቸውን ድክመት እያሰፉ፣ ጥፋቱን እያገዘፉ ከርሱ የተጎዳኘን ሁሉ በአንድ እየፈረጁ ማጥላላትን፣ መዘለፍን፣ መኮነንን ነው፡፡ ሰላማዊ ትግል በዚህ መንፈስ ተመርቶ ለውጤት እንደማይበቃ መለስ ብለን ማየት ብንችል የራሳችን ጉዞ ከበቂ በላይ ያስተምረናል፡፡

በድፍረት ሳይሆን በእውቀት፣በዘልማድ ሳይሆን በእቅድና በስልት፣ በ ‹‹ከማንአንሼ!›› ሳይሆን በእምነትና በጽናት ሲመራ ነው ሰላማዊ ትግል ዋነኛ ባለቤቱን ሕዝብን አሰልፎ ለድል ሊበቃ የሚችለው፡፡

ከዚህ አንጻር የ21 ዓመት የሰላማዊ ትግል ጉዞአችንን ስንፈትሽ የምናገኘው እውነት በመነሻችን ያነሳነውንና ሰላማዊ ትግሉ እስካሁን መሪዎቹን አላገኘም የሚለውን የሚያጠናክር ይሆናል፡፡ ይህም በመሆኑ ነው ሕዝቡ ለከፈለው መስዕትነት የሚመጥን ቀርቶ ትንሽ ተስፋ የሚፈነጥቅ ውጤት ለማየት ያልቻልነው፡፡ በርግጥ በጣት የሚቆጠሩ እምነቱም ጽናቱም ቁርጠኝነቱም የታየባቸው መሪዎች ከፕ/ር ዓሥራት እስከ ብርቱካን ሚደቅሳ በፖለቲካው መድረክ ላይ ብቅ ብለው ነበር፡፡ አያያዛቸውን አይቶ አካሄዳቸውን ገምቶ «ይህች ባቄላ ካደረች አትቆረጠምም» ያለው ሥልጣን ወይም ሞት የሚለው ወገን ጉልበት ከሥርዓት ተጠቅሞ ሁሉንም ስንዝር ሳይራመዱ ከመድረኩ ለማስወገድ በቅቷል፡፡ የሚያሳፍረው መሪዎቹን ከመድረኩ ለማስወገድ ለተከናወነው ድራማ መሪ ተዋናይ አልያም ተባባሪ በመሆን የተሰለፉት ከጎናቸው የነበሩ ሆነው ሳይሆን መስለው በሰላማዊ ትግሉ ባቡር ላይ የተሳፈሩ ሰዎች መሆናቸው ነው፡፡

ትግሉ ባለበት እየረገጠ እንዲያውም ወደ ኋላ እየተንሸራተተ ለውጤት ላለመብቃቱ ዘወትር በምክንያትነት የሚቀርበው የገዢው ጸረ ዴሞክራሲ አፈናና ሕገ ወጥ ተግባር ነው፡፡ ይህ የማይካድ ቢሆንም አንድና ብቸኛ ምክንያት ተደርጎ መቅረቡ ግን ትክክል አይደለም፡፡ እንዲያውም በአንድ በኩል ሰለማዊ ትግሉ መሪዎቹን አለማግኘቱና ሆነው ሳይሆን መስለው የተሰለፉት መበርከታቸው፣ በሌላ በኩል በጥሎ ማለፉ የፖለቲካ ጨዋታ የተካኑ ሲችሉ ራሳቸው፣ ሳይችሉ ለባለጡንቻው ተባባሪ በመሆን ለሰላማዊ ትግሉ የሚመጥኑ ወይንም በሂደት ራሳቸውን ለትግሉ ለማብቃት የሚታትሩ ሰዎችን ከመድረኩ ማስወገዳቸው ለሰላማዊ ትግሉ ውጤታማ አለመሆን ሚዛን የሚደፋ ምክንያት ነው፡፡

ነጻው ፕሬስም በዚህ ረገድ የድርሻ አበርክቶ አለው፡፡ ሀቁን እያለባበሰ እውነትን እየተራመደ ፖለቲከኞቹን ያልሆኑትን እያንቆለጳጰሰ ትክክለኛ ማንነታቸውን ተረድተው ወይ እንዲታረሙ ወይ ለሰላማዊ ትግሉ ‹‹አንመጥንም!›› ብለው ገለል እንዳይሉ፣ አለያም ገለል እንዳይደረጉ መከታ እየሆነ፣ ፓርቲዎቹንም ያልሰሩትን እየጋነነ በማቅረብ ቆም ብለው ራሳቸውን እንዳይፈትሹ እየጋረደ ለሰላማዊ ትግሉ ውጤታማ አለመሆን አሉታዊ ድርሻ ማበርከቱ ተለባብሶ መታለፍ የሌለበት ነው፡፡ ጋዜጠኛ የሚጽፈውም ሆነ የህትመት ውጤቶች ጽሁፎችን የሚያስተናግዱት ፓርቲውን በመውደድ በመጥላት እንዲሁም ለፓርቲዎቹ መሪዎች ባላቸው ፍቅርና መቀራረብ ወይንም በሚያገኙት ቁሳዊ ጥቅም ላይ በመመስረት ሊሆን አይገባም፡፡ መነሻም መድረሻቸውም እውነትና እውነት ብቻ መሆን ነው ያለበት፡፡ ቅዱስ መጽሀፍ እውነት ነጻ ያወጣችኋል አይደል የሚለው፡፡

በ1988 ዓ.ም መአህድ ውስጥ የነበርን ወጣቶች ስለፓርቲዎችና መሪዎቻቸው በየጋዜጣውና መጽሄቱ የምናነበውና እኛ ከውስጥ ሆነን የምናውቀው አልዛመድ ቢለን፤ ይበልጡንም የህትመት ውጤቶቹ አጋነውና አክብደው የሚያቀርቡት ያልተገባ አገላለጽ መሪዎቹን ለእብጠት ፓርቲዎቹንም ለስህተት እየዳረገ መሆኑ ቢያሳስበን በነጻው የህትመት ውጤት አካባቢ ተጽእኖ ፈጣሪ ወደ ሆኑ አንጋፋ ጋዜጠኛ ቢሮ አመራንና ጉዳዩን አስረዳናቸው፡፡ ርሳቸውም የምትሉት ትክክል ነው፣ ነገር ግን አሁን የተቃውሞውን ጎራ አመራሮች ስህተት እየነቀሱ፣ የፓርቲዎቹንም ድክመት እያመላከቱ መጻፍ ኢህአዴግን የሚጠቀምና የተቃውሞውን ጎራ ይበልጥ የሚያዳክም ይሆናል አሉን፡፡

በዚህ አባባላቸው ባለመስማማት ይልቁንም አሁን የሚሉንና እየተፈጸመ ያለው ነገር ነው ፖለቲከኞቹ ስህተታቸውን በጊዜ ተገንዝበው እንዳያርሙ፣ ድክመታቸውን አውቀው መፍትሄ እንዳይፈልጉ በማድረግ ፓርቲዎቹን የሚጎዳቸውና በአንጻሩ ኢህአዴግን የሚጠቅመው በማለት ለመከራከር ሞክረን ሳይሳካልን ተለያየን፡፡ እኚህ ሰው በጣም ዘግይተው ፓለቲከኞቹ የሚታረሙበት አሊያም ለትግሉ በሚመጥኑ ሰዎች ሊተኩ የሚችሉበት ብዙ ግዜ ከባከነና እድሎችም ካመለጡ በኋላ በ1997 ዓ.ም ልሳነ ሕዝብ ይባል በነበረው መጽሔት ላይ ባሰፈሩት ጽሁፍ «እዚህ ከደረስን በኂላ ለትግሉ ጥላ የሆኑ ካሉ (አምልኮ አይመሰልብኝና) መድረኩን ለብቻና በብቸኝነትም ለመያዝ ዘላለም የሚደክሙ ካሉ፣ የትግሉ ስትራቴጂና የመንገዱ ካርታ የጠፋባቸው ካሉ፣ ‹እኛ ሞክረን አልሆነልንም፣ ሌሎች ደግሞ ይግቡበት› በሚል ትህትና ዘወር ማለት አለባቸው፡፡ ገዢውንም ‹ቦታ ልቀቅ› ተቀዋሚውንም ‹በቃህ ቦታውን ልቀቅ!› ወደ ማለቱ ማዘንበላችን ደግሞ ወደ ፊት ያለመራመድ ችግር ስላለ ነው፣» በማለት በምሬት ጻፉ፡፡ ከእኛ ጋር ከተነጋገሩ በአስረኛው ዓመት መሆኑ ነው፣ ርሳቸው ይህን ከጻፉ ደግሞ አሁን የምንገኝበት ምርጫ 2007 ዋዜማ አስር ዓመት ሞልቶታል፡፡ ነገሮች ግን ያው ናቸው፡፡

ሰላማዊ ትግሉ ለድል በቅቶ አስተማማኝ የዴሞክራሲ መሰረት በዚህች ሀገር እንዲጣል ካስፈለገ በትናንት አስተሳሰብ የዛሬ ትግል አይመራምና፣ ሰላማዊ ትግሉም የራሱን መሪዎች ይሻልና፣ በያዙት መንገድና አስተሳሰብ ለለውጥ ሊበቁ አልቻሉምና፣ ትግላቸውን ሰላማዊ፣ ዓላማቸውን በምርጫ ሥልጣን መያዝ ያደረጉ ፓርቲዎች ምርጫ 2007 ላይ ከመድረሳችን በፊት አሁንና ዛሬውኑ ጀምሮ ከወቅቱ ጋር በሚራመድና ለሰላማዊ ትግሉ በሚመጥን ደረጃ ራሳቸውን ማስተካከል ይጠበቅባቸዋል፡፡

ነገር ግን፤ ሆነው ሳይሆን መስለው በጽናት እየታገሉ ሳይሆን የተቀዋሚ አመራር እየተባሉ ለመኖር በትግሉ ሰገነት ላይ በሚገኙ ሰዎች ሰላማዊ ትግሉ እየተመራ ዛሬም እንደ ትናንቱ መስዋዕት እንጂ ለውጥ የማያስገኝ ከሆነና በዚህም ሕዝብ የቀረችውን እንጥፍጣፊ ተስፋ ካሚጠጠ፣ «ሰላማዊ ትግሉ የገዢዎችን እድሜ ከማራዘም ውጪ ፋይዳ የለውም የሚያዋጣው ኢህአዴግን በሚያውቀው ቋንቋ ማነጋገር ነው» የሚለው አስተሳሰብ ክብደትም ተቀባይነትም እንዲያገኝ ማገዝ ይሆናል፡፡

በሌላ በኩል ከእንግዲህ የኃይል አማራጭ የሚያስቡ ቢኖሩ፤ ልክ እናስገባቸዋለን ብሎ በሀይል መመካት እንደማያዋጣ ከታሪክም፣ ከራስ ተሞክሮም፣ በጎረቤት ሀገራት እየሆነ ካለውም መማር ትልቅነት ይሆናል፡፡ ብሶት የወለደን የሚሉትና ዛሬም ከሁለት አስርት ዓመታት በኋላ በስራቸው ከመከበር ይልቅ በጡንቻቸው መፈራትን፣ ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶችን አክብረውና የህግ የበላይነትን አረጋግጠው ተቀባይነትን ከማግኘት ይልቅ ስለ ደርግ አረመኔነት፣ ስለ ቀደምት የኢትዮጵያ ነገስታት ተስፋፊነትና ጨቋኝነት እየተረኩ እኔ እሻላችኋለሁ በሚል ማስፈራሪያ የሥልጣን ዕድሜአቸውን ለማራዘም የሚጥሩ ወገኖች ሌላው ወገን ብሶት አይብሰውም፣ እምቢ ለመብቴ ብሎ ለመነሳትም የሚያበቃ ወኔም አመቺ ሁኔታም የለውም ብለው የሚያስቡ ከሆነ ከስህተት ሁሉ የከፋው ስህተት ይሆናል፡፡

በፖለቲካው ምህዋር ላይ የሚሽከረከሩ ከየትኛውም ጎራ የተሰለፉ ከግል ጥቅም በፊት የህዝብን ጥቅም ቢያስቀድሙ፣ ከሥልጣን በላይ ለሀገር ቢያስቡ ይመረጣል፡፡ ይህ

ወደ ገፅ 6 ይዞራል

# ኢ/ር ይልቃል ጌትነት በአሜሪካ....

ኢንጅነር ይልቃል፡- አሜሪካ ስቴት ዲፓርትመንት ባደረገልኝ ግብዣ ላይ ለሶስት ሳምንት እቆያለሁ። የትኬትና ተመሳሳይ ጉዳዮችን ከሚሰሩት የአሜሪካ ሰዎች ጋር ስንነጋገር ከዚህ ውጭ አንድ ወር ያህል አሜሪካን አገር እንደምቆይ ገልጨላቸዋለሁ። በዚህም አጋጣሚ ባለፈው በአየር ንብረትና በድካም ምክንያት ያላዳረስኳቸው ቦታዎች ላይ ስብሰባ የማካሄድ ሀሳብ አለኝ። ምን አልባትም ወደ ለንደንና ካናዳ ልሄድ የምችልበት አጋጣሚ ይኖራል። ይህ እንግዲህ ከዚህ ካለው ስራ፣ ከጉዞ ሰነዶችና ከጊዜም ጋር ተደማምሮ በሂደት የምናየው ይሆናል። በድርጅታዊ ጉዳይ ላይ ለመስራት እቅዱም ሀሳቡም አለን። እዚያው ያሉት ደጋፊዎቻችንም በጉዳዩ ላይ እየሰሩበት ይገኛሉ።

ነገረ-ኢትዮጵያ፡- ወደ ሌላ ርዕሰ-ጉዳይ ልውሰድዎትና፣ ባለፈው እሁድ ሴቶች በተሳተፉበት የታላቁ የጎዳና ላይ ሩጫ የሰማያዊ ፓርቲ አባላት የተለያዩ ጥያቄዎችን አንስታችኋል በሚል ከተያዙ በኋላ ለሁለተኛ ጊዜ ‹‹መረጃን ለማሰባሰብ›› በሚል ቀጠሮ ተሰጥቷቸዋል። ይህን እንዴት ያዩታል?

ኢንጅነር ይልቃል፡- በዚህ ጉዳይ ከማዘንና ከማፈር ውጭ የምለው ነገር አይኖርም። ኢህአዴግ በዴሞክራሲ እየማለ፤ ለዜጎች እኩልነት፣ ለኃሳና ሀይማኖት እኩልነት፣ ለሴቶች እኩልነት ጠብመንጃ አንስተን በመዋጋት የልጅነት እድሜያችንን በበርሃ አጥፍተናል እያሉ፤ 23 አመት ቆይተው ግን ሴቶች ለነጻነት በተሰለፉበት ቀን ስለ አገራቸው አንድነትና ስለ መሰረታዊ መብቶች የጠየቁ ሰዎችን እስር ቤት ሲያጉሩ ምን ያህል የማይማርና ወደ ኋላ እየተንደረደረ የሚገኝ፣ የራሱን ሞት እየጠበቀ ያለ መንግስት እንደሆነ ለመረዳት ችያለሁ። ከዚህ ውጭ ምንም አዲስ ነገር ባላይበትም ትግሉ ውስጥ መግባታችን ምን ያህል ትክክል እንደሆነ ግን አረጋግጦልኛል። እሱ የማይፈልገው ሀሳብ ከሆነ ለምንም ነገር የማይመለስና ሴት፣ ህጻን፣ ህጋዊም ሆነ አልሆነ ለእሱ ምኑ እንዳልሆነ፣ በስልጣኑ ላይ ለመጣ ወደኋላ የማይመለስ መንግስት መሆኑን ተረድተንበታል። ይህም ዘላለም ለመጨቆን የተዘጋጀ መንግስት በመሆኑ ወደ ትግል መግባታችን ትክክል መሆኑ እንድንረዳ አድርጎናል። ይህም ለትግሌ መሰረት ስንቅ ከመሆኑ በተጨማሪ በኢህአዴግ ላይ አዝኛለሁ፣ አፍሬያለሁ።

ነገረ-ኢትዮጵያ፡- ባለፉት ሁለት አመታት አረቦቹ አብዮት አካሂደዋል። ዩክሬን ውስጥ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ለውጥ ነበር። ለባለፈው አንድ አመት ተኩል ደግሞ ኢትዮጵያ ውስጥም የተቃዋሚዎች እንቅስቃሴ በአንጻራዊነት እየተጠናከረ ነው። አመጽ እየተለመደ ከመምጣቱ፣ የኑሮ ውድነትና ጭቆናው ከመባባሱ ጋር ተዳምሮ ኢትዮጵያ ውስጥ በቀጣይነት የሚመጣውን ለውጥ እንዴት ነው የሚያዩት?

ኢንጅነር ይልቃል፡- መቼም እኔ የምናገረው ምኞቴንና የምሰራበትን ነገርም ነው። ከዛ ውጭ ያለውን ነገር ብንወደውም ባንወደውም ራሱ መምጣቱ ስለማይቀር፣ ስለ እሱ መናገር ለእኛ አወንታዊ አስተሳሰብ ስለማይበጅም ሆነ እርግማት ተናጋሪ ስለሚያሰኝ ማድረግ የሚቻለውን በጎ ነገር እያደረግን ብንሄድ የተሻለ ነው የሚሆነው። እንደ ኢትዮጵያ አይነት በዓለም የመጨረሻ ድሃ ለሆነ፣ ብዙ የኃሳና የእምነት መቃቃር በተፈጠረበት አገር፣ በሩቅም በቅርብም የኢትዮጵያን መረጋጋት የማይወዱ አካላት ባሉት ቀጠና ላይ ሆነን፣ እርስ በራሳችንም በተለያዩ የታሪክ ግጭቶች ውስጥ እያለን እንዲህ አይነቱ ለውጥ ባይኖር ደስ ይለናል። ነገር ግን አልፈለግነውም ማለት አይከሰትም ማለት አይደለም። ሰማያዊ ፓርቲ እንዲህ አይነት ጉዳይ እንዳይከሰት የተጠና፣ አስቀድሞ በድርጅቱ የተመራ፣ ኃላፊነት በተሞላበት መልኩ የሚካሄድ የስልጣን ሽግግር እንዲኖር ሌት ተቀን ይሰራል። ሆኖም ገዥው ፓርቲ በጠቅላይነትና ባታላይነት እቀጥላለሁ ካለ ህዝቡ ውስጥ መሰላቸት በግልጽ ይስተዋላል፣ ችግሮች ከዕለት ዕለት እየተደራረቡ ነው፣ ህዝብ አገሩ ውስጥም ሆነ በአካባቢው የለውጥ ምሳሌዎችን እያየ ነው፣ ችግሩ መሸከም ከሚችለው በላይ ሆኖበታል።

በመሆኑም እነዚህ ለለውጥ መሰረት የሆኑ ነባራዊ ሁኔታዎች እየመጡ ስለመሆኑ የፖለቲካ ተንታኝ መሆን አያስፈልግም። በዚህ ሁኔታ አገዛዙ ውስጥ ያሉት ሰዎች የሚፈተኑት ከመግዛትና ከመጨቆን አስተሳሰባቸው ወጥተው ወደ እውነታው ቀርበው ለለውጥ ይዘጋጃሉ ወይንስ በተለመደው ግትርነት ይቀጥላሉ? በሚለው ነው። በሌላ በኩል እኛም ደግሞ አማራጭ ሆነን፣ እነሱን ሳናስደነብር፣ ሰላማዊ የስልጣን ሽግግር እንዲፈጠር መቻቻልና ይቅር ባይነቱ ኖሮን አገራችንን ማዳን የምንችልበት ሆደ ሰፊነትና አስተዋይነት ፖለቲካ በሁለታችንም በኩል ይጠበቃል። ግን ይህን ታሪካዊ ጉዳይ ከሁለታችን አንዳችን ከሳትነው ሂደት በተፈጥሮ የሚያመጣው ጉዳይ አለ። ሁሌም



ታሪክም፣ ስልጣኔም፣ የሰው ልጅም ይወለዳል፣ ያድጋል፣ ይለወጣል። ልቡን የደፈነ ሰው ካልሆነ በስተቀር ለውጥ አይቀሬ ስለመሆኑ የሚጠራጠር ያለ አይመስለኝም። በዚህ ሂደት ውስጥ ምን ያህል ንብረት ይወድማል፣ ምን ያህል የሰው ነፍስ ይጠፋል፣ በሂደቱ ምን ያህል የተጠና እና ለአገራችን የሚጠቅም ለውጥስ ይመጣል የሚለው ነው እንጂ የሚያስጨንቀኝ ለውጡ እንደቀረበ ጥርጥር የለኝም።

ነገረ-ኢትዮጵያ፡- ይህ ለውጥ ቢከሰት ለውጡን በሚገባው መልኩ ለማስተናገድና ለመምራት ትክሻ ያለው አካልስ አለ ብለው ያስባሉ?

ኢንጅነር ይልቃል፡- እኛ ሰማያዊ ይህን ለውጥ መሸከም የሚችል ትክሻ አለው ብለን ነው የምናምነው። በእኛ አገር ይህንን አይነት ነገር ደፍረን ስንናገር በሁሉም ወገኖች ዘንድ አይወደድልንም። ለምን እንደማይወደድም ይገባናል። ባይወዱትም መናገር አለብን። ከማይወደድበት ምክንያት የመጀመሪያው በጭቆና መንፈሳችን መላሸቁ ነው። ስለዚህ ‹‹ይቻላል!›› ማለት እንደ ቅዠትና እብደት ይቆጠራል። ይህም ‹‹ይቻላል›› የሚለውን ከመጥላት፣ ከጭቆናው መብዛት፣ በተደጋጋሚ ከመክሸፍ የመጣ የአቅመ ቢስነት ችግር እንጅ የእኛ ችግር አይደለም። እነዚህ በጭቆና አስተሳሰብ ስር የወደቁት የእኛን አመለካከት እንዲይዙ ጥረት በማድረግ በተደጋጋሚ ስለ ጉዳዩ እንናገራለን። ከዚህ በተጨማሪም ድርጅት ሆነን ስንቋቋም እኛ የተሻለ አማራጭ አለን፣ አገርና ህዝብን ወደተሻለ ደረጃ እናደርሳለን ብለን ነው። ስለሆነም ስለ ራሳችን ስለ ድርጅታችን በሙሉ ልብ ‹‹እንችላለን!›› ስንል፣ ሌሎች ድርጅቶች ቅር ይላቸዋል። ይህ ከፖለቲካ እውቀት ማነስ የመጣ ነው። እኛ እንደ ድርጅት ተቋቁመን ‹‹እንችላለን!›› ካላልንና ህዝብና አገርን ወደ ተሻለ ደረጃ እንደምናደርስ መናገር ካልቻልን ህዝቡ እንዴት ሊከተለን ይችላል? ለምንስ ጊዜያችንን እናጠፋለን?

ሰማያዊ ፓርቲ ባለፈው አንድ አመት ተኩል የፖለቲካ ነገር በቀላሉ የማይመዘን ሆኖ እንጅ መብት መጠየቅን፣ መነቃቃትን፣ ከአይቻልም ባይነት ይቻላል ባይነትን፣ አዲሱ ትውልድ የራሱን እጣ ፈንታ ለመወሰን በድርጅት የመታቀፍንና የመታገልን በአዲስ መልክ ይዞ ብቅ ብሏል። ይህም ለረዥም ጊዜ በወደቀና በከሸፈ የፖለቲካ አመለካከት ውስጥ በጣም ረዥም ጊዜን የሚጠይቅ ስራ ነው። ይህም በቀላሉ የተገኘ ሳይሆን በርካታ የሰማያዊ ወጣቶች የራሳቸውን የህይወት አማራጭ ትተው በዚህ ጉዳይ ላይ ጥርሳቸውን ነክሰው፣ በግልጽ የፖለቲካ አመለካከት ሌት ተቀን ከአገዛዙ ጋር እየተጋፈጡ፣ እየታሰሩ፣ ዋጋ እየከፈሉ የመጣ ነገር ነው። በዚህ ሂደታችን ውስጥ ወጣቶች ወደ ፖለቲካው እንዲመጡ ማነቃቃት ችለናል። ከትልልቅ የአደባባይ ምሁራን፣ ከዩኒቨርሲቲ ፕሮፌሰሮች፣ ከውጭም ከአገር ውስጥም ክብርና

ከ ገፅ 4 የዞረ

ይሁንታን አግኝተናል።

ከክርስትናም ሆነ እስልምና ሀይማኖት መሪዎችና አማኞች አካባቢም መከበር ችለናል። ከዓለም አቀፍ ማህበረሰቡም ቢሆን እንደሚታየው ወጣትና ወደፊት አገራቸውን መምራት የሚችሉ ተብለን መወደስና መሸለም ችለናል። የዓለም አቀፉም ሆነ የአገር ውስጥ ሚዲያው እንደ አንድ የፖለቲካ ኃይል አይቶናል። በኢትዮጵያ የፖለቲካ ታሪክ ውስጥ ለስልጣን መሰረት የሆኑት ነገሮች እነዚህ ናቸው። ዩኒቨርሲቲዎች፣ ወጣቶች፣ የአደባባይ ምሁራን፣ ዓለም አቀፍ ማህበረሰቡና ሚዲያው ሰማያዊን እንደ አንድ የፖለቲካ ኃይል ማየት ችሏል። በእነዚህ ኃይሎች ተቀባይነት ካገኘ አገሪቱን ለመምራት የሚያቅተው ምንም ነገር አይኖርም ማለት ነው። የራሱ አላማ፣ የራሱ ፕሮግራም አለው። ይህን ለማስፈጸም የሚችል ቆራጥ አመራር አለው። በእርግጥ ኢትዮጵያ ትልቅ አገር ብትሆንም ሰማያዊ ለውጥን በአግባቡ ለመረከብና ለመምራት የሚያስችል አቅም እንዳለው መግለጽ እፈልጋለሁ።

ነገረ-ኢትዮጵያ፡- ዲያስፖራው የገንዘብም፣ የመረጃና የእውቀትም አቅም እንዳለው ቢታመንም ከ1997 በኋላ ግን ለአገሪቱ ፖለቲካ አሉታዊ ጎን እንደነበረው በስፋት እየተጠቀሰ ነበር። በአሁኑ ወቅት እናንተ ከዲያስፖራው ተቀባይነት እያገኛችሁ ነውና መልካም ጎኑንና ፖለቲካውን ላይ አለው የሚባለውን አሉታዊ ተጽዕኖ እንዴት ነው የምታስታርቁት?

ኢንጅነር ይልቃል፡- ሰማያዊ ፓርቲ ውስጥ አንድን አካል በቅራኔ መድቦ መታገል የተለመደ ባህል አይደለም። ለምሳሌ ሰማያዊ ፓርቲ ወጣቱ ላይ ያተኩራል ሲባል፤ በየትኛውም ታሪክ ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ ግን የሽማግሌዎችን፣ የአደባባይ ምሁራንንና የትልልቅ ሰዎችን ድጋፍ አግኝቷል። በተመሳሳይ ሁኔታ የሰማያዊ አመራር አገር ውስጥ ቢሆንም የራሳቸው የፖለቲካ ፋይዳ፣ ካፒታል፣ አንጻራዊ ነጻነት ያላቸው፣ የአገራቸውን ነጻነት በቀናነት የሚመኙ፣ በመረጃው በኩል ቅርብ በመሆናቸው በዲፕሎማሲው መስክ ትልቅ እገዛ ከሚያደርጉት በውጭ የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ትልቅ ተቀባይነት አለው። ይህን ጉዳይ ሚዛናዊ በመሆነ መልኩ የመምራት ችግር ካልሆነ በስተቀር በውጭ የሚገኙት ኢትዮጵያውያን አገር ውስጥ ከሚገኙት የተለዩ አይደሉም። አገር ውስጥ እንዳለው ሁሉ ውጭ ያለውም የአገሩ ሁኔታ ያሳስበዋል። የአገር ውስጡ የራሱ ሚና ይኖረዋል። በውጭ የሚኖረው ደግሞ የራሱ የሆነ ሚና ይኖረዋል።

እነዚህን ሁለት ጉዳዮች አገር ውስጥ ያለው በተገቢው መንገድ ማስተባበር ይኖርበታል። አገር ውስጥም ውጭም ያለውን አጣጥሞ የማስኬድ ስራ ነው የምንሰራው። መሪነት ሲባል እኮ የሰዎችን አቅም ለግብ መጠቀም ነው። የትኛውም የማህበረሰብ ክፍል፤ አርሶ አደር፣ ነጋዴ፣ ውጭ ያለ፣ አገር ውስጥ የሚገኝ፣ የተማረም ይሁን ያልተማረ፣ ሁሉ ጥቅምና ፍላጎት አጣጥሞ ወደፊት መምራት ነው ዋናው ስራችን። ዲያስፖራውንም እንደ አፈንጋጭ፣ እንደ አጥፊና ለኢትዮጵያ ችግር ተጠያቂ አድርጎ ማየት በሰማያዊ ፓርቲ የተለመደ አይደለም።

ባለፈው ጉብኝት ባደረኩበት ወቅት የዲያስፖራውን ድክመትና ስህተቶች ያልኳቸውን በአደባባይ ተናግሬያለሁ። እነሱም ከጊዜ ብዛትና ከመውደቅ መነሳት ብዙ የተማሩት ነገር እንዳለ ተረድቻለሁ። ይህን ጉዳይ አጣጥሞ የሚመራ አስተዋይ፣ ብልህና ሆደ ሰፊ መሪ ያስፈልጋል። ይህ እኛ እንደ ድርጅት አዲስ ብንሆንም በፖለቲካው መውደቅ መነሳት ከ1997 ዓ.ም ጀምረን የነበርን ሰዎች በመሆናችን የተፈጠሩትን ነገሮች በቅርበት እናውቃቸዋለን። ባገኘነው በቂ ልምድም ጉዳዩን በጥበብ መያዝ ችለናል። ወደፊትም በጥሩ ሁኔታ እንሄዳለን የሚል እምነት አለኝ።

ነገረ-ኢትዮጵያ፡- የዲያስፖራውን ጉዳይ ካነሳን አይቀር፤ ከ1997 በኋላ በነበረው ፖለቲካ ተስፋ ከመቁረጡም ባሻገር በቅንጅት አባል ፓርቲዎች መካከል ተከፋፍሎ እንደነበር ይነገራል። ባለፈው ጉብኝት ባደረጉበት ወቅት ዲያስፖራውን እንዴት አገኙት? አሁንስ ምን አዲስ ነገር ይጠብቃሉ?

ኢንጅነር ይልቃል፡- እኔ ስሄድ የምጠብቀው አነስ ያለ ነገር ነው። ትግል ውስጥ ስትገባ ያለውን አስቸጋሪ ነገር ቀይሬ ከዚህኛው ወደዚህኛው አሻሽለዋለሁ ነው እንጂ፣ ይህኛው አለኝ ብለህ አትኩራራም። የዓለም የመጨረሻ ድሃ አገር ነን። የፖለቲካ ባህላችን አስቸጋሪ ነው። የእምነት አገር ነው። የ1966 አብዮት የፈጠረው ችግር አለ፣ 1997 የፈጠረው ችግር አለ። እንደ ፖለቲከኛ ይህን ችግር እለውጣለሁ የሚል እምነት ይዤ ነው የተነሳሁት። ከላይ የተጠቃቀሱት ችግሮች በአንድም ሆነ በሌላ ምክንያት መኖራቸውን ብገነዘብም አንድ መልካም ነገር መኖሩ ሌሎቹን ችግሮች ያቃልላቸዋል።

ለምሳሌ ያህል የኢሳት መኖር በአገሩ ጉዳይ ተስፋ ቆርጦ የነበረውን የዲያስፖራ ማህበረሰብ መረጃ እንዲኖረውና ተነቃቅቶ እንዲጠብቅ በማድረግ መልካም ስራ አከናውኗል። በተለይ የሰማያዊ ወጣቶች ‹‹አይቻልም!›› በተባለበት አገር ትንሽም ነገር ሲሰሩ ሲታይና ይህም የማህበረሰባዊ ድህረ-ገጾችን ጨምሮ ለበርካታ ሰዎች መድረሱ አድናቆት አስገኝቶልናል።

እንዲያውም እኛን ከልክ በላይ የማወደስና ነጻ አውጭ አድርጎ የማየት እንጂ በእኛ ላይ ቅሬታ ያለው ሰው የለም። ለዚህም እድሜያችን እንደመልካም አጋጣሚ ሊታይ የሚችል ነው። እድሜያችን፣ በኢህአፓ፣ በደርግ፣ በመኢሶን የተቋሰለው ትውልድ አለመሆናችን ለፍረጃ ክፍተት አልሰጠም፣ ሰውም እንዲጠላን ምክንያት አልሆነም። ይህ በእኛ ስራ ሳይሆን በትውልድ ያገኘነው መልካም አጋጣሚ ነው። እንዲያውም በሰማያዊ በኩል እንደ ችግር ይቆጠራል ከተባለ ሁሉም ኃይል የራሱ ለማድረግ ስለሚሞክር ሚዛን የማስጠበቅና ማዕከል ላይ ሆኖ የማሰባሰብን ሚና ነው እየተወጣ የሚገኘው።

ከዚህ ውጭ ከርቀት ሆነው ወጣትነታችን ሲያዩ የቆዩና ትውልዱ ጫታም፣ ስደተኛና ይህ ነው የሚባል ቁም ነገር የማይሰራ የሚመስላቸው የነበሩ ሰዎች ስንቀራረብ ትልቅ አድናቆት ችረውናል። መጀመሪያ ላይ በሆይ ሆይታና በጮኸት የተሰባሰብን ቢመስላቸውም ስለ እኛ ካወቁ በኋላ ‹‹እንዲህ አይነት ወጣትም አለ?›› በሚል ተገርመውብናል። በመልካም ሁኔታም ነው የተቀበሉን። እስካሁን ያለው ተስፋ ሰጭ ቢሆንም አሁንም ትልቅ ስራ ይጠይቃል።

ነገረ-ኢትዮጵያ፡- ያለፉት የፖለቲካ ውድቀቶች በመፍራት ወጣቱም ሆነ ዲያስፖራው ፓርቲዎችን ለመቅረብ ይፈራል። ‹‹ምንድን ነው ማረጋገጫችን?›› የሚል ጥያቄም በስፋት ሲነሳ ይስተዋላል። ለዚህ ጥያቄ እናንተስ መልሳችሁ ምንድን ነው?

ኢንጅነር ይልቃል፡- እኛ የምንሰራው ለአገራችን ብለን እንጂ ማንም እንዲያወድሰንና እንዲያምነን ብለን አይደለም። የሰራነው ነገር ሲያሳምነው ይከተለናል፤ ያምነናልም። ባለፈው 10 አመት ውስጥ ፖለቲካው ውስጥ ስለነበርን በመውደቅ በመነሳቱ ላይም አልፈናል። የራሳችንን ታሪክ ያለን እንጂ ከምንም ዱብ ያልን ፖለቲከኞች አይደለንም። የሚያከብሩን ሰዎች አሉ፣ በቅርብ የተማርንባቸው ሰዎችም አሉ፣ በተግባር ውጣ ውረድ ውስጥም አልፈናል። ይህ ለመታመን በቂ ይመስለኛል። ከዚህ በተጨማሪ ሰማያዊን የመሰረትን ሰዎች ስብሰባ ላይ በአጋጣሚ የተገናኘን ሳይሆን ከእነ ድክመትና ጥንካሬያችን ለረዥም ጊዜ የምንተዋወቅ ሰዎች ነን። በጎሳ፣ በወንዝ ልጅነት ሳይሆን ነጻ በሆነ የፖለቲካ አስተሳሰብ ተገናኝተን በደንብ የተዋወቅን ሰዎች በመሆናችን በቀላሉ እንዳንፈርስ መልካም እድል ይሰጠናል።

በተጨማሪም ይህ አስተሳሰብ ከመውደቅ የመጣ እንጂ ከእኛ ጥፋት የመጣ አይደለም። ስጋቱ ቢኖርም እኛ በመታመን እንሰራለን እንጂ አያስጨንቀንም። ምክንያቱም ችግሩ ከእኔ አሊያም ከአንዱ ጓደኛዬ ድክመት የመነጨ ስላልሆነ ነው። አገራችን ውስጥ አለመተማመን በመኖሩ፣ ሰዎች ደጋግመው በመውደቃቸው፣ አጠቃላይ ክሽፈት በመብዛቱ የተፈጠረ የወል ስነ ልቦና ነው። ይህ እንደ አገር የጋራ ችግራችን በመሆኑ ይህን ባህል ለመቀየር እንሰራለን እንጂ አንድ ሰው ለምን አላመነኝም ብዬ አልጨነቅም። ይህን የወል ስነ ልቦና በድፍረት፣ ከራስ ወዳድነትና ከዝርክርክነት ወጥተን፣ አርዕያና ታማኝ በመሆን፣ የውሳኔ አሰጣጥም ሆነ የገንዘብ አወጣጥን ተጠያቂነት በተሞላበት መንገድ በመፈጸም፣ ከአባላት ጋር የቅርብ ግንኙነት በመመስረት፣ የስልጣን ልዩነትን በማጥፋት ሰው ከአሉባልታ ይልቅ በሳይንስና በምክንያታዊ ነገር እንዲመዘን ማድረግ ይቻላል።

እኛ ልናደርግ የምንችለው ሰውን ተስፋ ያስቆረጡትንና ለመለያየት ምክንያት የነበሩትን ነገሮች መቀነስ ነው። አለመተማመኑ ግን ደጋግሞ የመክሸፉ ችግር እንጂ የሰማያዊ ልጆች ችግር አይደለም። የሰማያዊ ልጆች ከአሁን በኋላ ምንም ይምጣ እስካሁን ባደረጉት ነገር ብቻ ሊደነቁ ይገባቸዋል። ባለፈው አስር አመት ውስጥ የግል ህይወታቸውን መኖር እየቻሉ ለአገርና ለወገን ሲሉ ብዙ ስቃይን የሚቀበሉ ልጆችን ማፍራት ችለናል። ለነጻነታቸው የሚዘምሩ ወጣት ሴቶችን ማፍራት ችለናል። የወደቀውንና አይቻልም የሚለውን መንፈስ ማነቃቃት ተችሏል። የወደፊቱ እንዳለ ሆኖ በእስካሁንም ቢሆን ሊመሰገኑ ይገባቸዋል። አለመተማመኑ በውድቀት የመጣ እንደመሆኑ እሱን መቀየር የሚቻለው በስራ ነው።

ነገረ-ኢትዮጵያ፡- ለነበረን ቆይታ አመሰግናለሁ።

ኢንጅነር ይልቃል፡- እኔም አመሰግናለሁ።

# ይህ ገጽ በሰማያዊ ፓርቲ አዘጋጅነት የሚቀርብ ሲሆን፣ ፓርቲው ፕሮግራሙንና አላማውን ለአባላትና ደጋፊዎቹ የሚያደርስበት ነው።

## የሰማያዊ ፓርቲ ፕሮግራም

መግቢያ፡-

*ሀገራችን ኢትዮጵያ የረጅም ጊዜ አኩሪ ታሪክ፣ ቀደምት የሥልጣኔ ባለቤትና ከ3000 ዘመን በላይ የመንግስትነት ታሪክ ያላት ታላቅ ሀገር ናት። የሰው ልጅ ዛሬ ለደረሰበት የዕድገትና የስልጣኔ ደረጃ መሰረት የሆኑ ቁሳዊና መንፈሳዊ ትውፊቶችን በማበርከት ለዓለም ስልጣኔ ታላቅ አስተዋፅዖ አበርክታለች። በየዘመናቱ ነፃነቷን ለማጥፋት የወረሯትን የውጭ ተስፋፊዎችና ቅኝ ገዥዎች በተደጋጋሚ ጊዜ ድል በማድረግ ነፃነቷንና ሉዓላዊነቷንም አስከብራ ኖራለች። ሀገራችንን በእብሪት ለመውረር የመጣውን የኢጣሊያን ወራሪ በመደምሰስ በዓለም ለመጀመሪ ጊዜ ጥቁር የሰው ልጅ ዘር ነጭ ወራሪዎችን ማሸነፍ እንደሚችል በአድዋ ታሪካዊ ድል ያስመሰከረች ብቸኛ የጥቁር ሰው ዘር መኩሪያና መመኪያ ሃገር ነች። ቅኝ ገዥዎችና ኢምፔሪያሊስቶች አፍሪካን ለመቀራመትና የተፈጥሮ ሃብቷን ለመዝረፍ ያደረጉትን ስምምነት ተከትሎ አፍሪካን በቅኝ ግዛት ስር ለማዋል በተደረገው ወረራ ተስፋፊዎችን በመመከት በቅኝ ገዥዎች ሥር ያልወደቀችና ለመላዉ ጥቁር ሕዝብ የነፃነት ተምሳሌት ሐገር ነች። አብዛኛዎቹ አፍሪካዊ ሀገሮች ድንበሮቻቸውና ማንነታቸው በቅኝ ገዥዎች ፍላጎት እንዲወሰን ሲደረግ ሀገራችን ወራሪዎችን በመቋቋም የራሷን የድንበር ወሰንና ማንነት በራሷ መወሰን የቻለች ብቸኛዋ አፍሪካዊ ሀገር ናት።*

በሃገር ውስጥም የንግድ መስመሮችንና የኢኮኖሚ ተጠቃሚነትን ለመቆጣጠር እንዲሁም አንዱ አካባቢ በሌላው ላይ የሥልጣን የበላይነትን ለመያዝ በርካታ የእርስ በእርስ ጦርነቶች ተካሄደዋል። በየዘመናቱ በተካሄዱ በእነዚህ የእርስ በእርስ ጦርነቶች ብዙ ህይወትና ንብረት ጠፍቷል፤ ብዙ ሰቆቃዎችም ተፈፅመዋል። በየጦርነቱ አሸናፊ የሆኑ ኃይሎችም ተሸናፊውን በማስገበር ከአንደኛው የሃገሪቱ ጫፍ እስከ ሌላኛው የሀገሪቱ ጫፍ ድረስ የግዛት መነሻቸውንና ስልጣናቸውን በማስፋፋት ሃገሪቱን ሲያስተዳድሯት ኖረዋል። በዚሁም ምክንያት የባህል የሃይማኖት የቋንቋና የልማድ ውርርሶች ከአንደኛው ወገን ወደሌላኛው ወገን በስፋት ተሸጋግረዋል። በጋብቻና በማህበራዊ ትስስሮችም የበርካታ ጎሳዎች ዉህደትና የስነ ልቦና ጥምረት እንዲዳብር ምክንያት ሆኗል። ሀገራችን የበርካታ ገፀ ምድርና ከርሰ ምድር ኃብት፣ አስደናቂ የተፈጥሮ ውበትና የሰው ልጅ ቀደምት ስልጣኔ መገለጫ የሆኑ ቅርሶች ባለቤት፣ ሰፊ መሬትና የሰው ኃይል ያሏት ታላቅ ሐገር ናት። ሀገራችን የተለያዩ የአየር ፀባያትባለቤት ስትሆን ለሰው ልጅ መኖሪያና ለአዝርዕት መብቀያ ተስማሚ ተፈጥሮ በሰፊው የተለገሳት ሀገር ናት። በርካታ በጥቅም ላይ የዋሉና ገና ያልተነኩ የተፈጥሮ ስጦታ የፈሰሰባትም ምድር ናት። ሆኖም የዚህ አኩሪ ታሪክ፤ ባህልና የተፈጥሮ ሃብት ባለቤት የሆነች ሃገራችን ዛሬ በቀሪው የዓለም ሕዝብ ፊት የምትታወቀው በርሃብተኝነት፣ በተመፅዋችነት፣ በስደትና በእርስ በእርስ ጦርነት ባለቤትነቷ ነው። የሰው ልጅ ዛሬ ከረደሰበት የአስተዳደርና የኢኮኖሚ እድገት ደረጃ እንዳንደርስ ያደረገን በሃገራችን ተንሰራፈተው በቆዩና አሁንም ባሉ የአስተዳደርና የፖለቲካ ሥርዓት ብልሹነቶች ምክንያት ነው ብለን እናምናለን።

ዛሬ ኢትዮጵያ በፖለቲካ እድገት ብቻ ሳይሆን በኢኮኖሚና በማህበራዊ እድገትም የዓለም ሃገራት የመጨረሻዎቹ ደረጃ ላይ ትገኛለች። ሕዝቧ የዘር፣ የሃይማኖት፣ የቋንቋና የባህል ልዩነቶችን ተቀብሎ ለበርካታ ዘምናት ተቻችሎ የኖረ ቢሆንም ዛሬ እርስ በእርስ በጥርጣሬ እንዲተያይና አንድነቱ እንዲላላ እየተደረገ ነው። ሃገራችን በተቀበለቻቸውና ባፀደቀቻቸው ዓለም አቀፍ ህጎች እንዲሁም በኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት እውቅና ያገኙ ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች የሚያከብራቸውና የሚጠብቃቸው ባለቤት አጥተዋል። የኢኮኖሚ መርሃችንም በጥናትና በአስተማማኝ መሠረት ላይ ያልተጣለ በመሆኑ ካለንበት የድሕነት አዘቅት ሊያወጣን አልቻለም። ፍትኃዊ የንብረት ስርጭትና የሥራ እድል ባለመኖሩ በኢትዮጵያውያን መካከል ያለው የኑሮ ደረጃ እጅግ እየተራራቀ መጥቷል። ዜጎችም የዜግነት እኩልነት ክብራችን ተነፍገን አብዛኛዎቻችን በሃገራችን ጉዳይ ባይተዋር ሆነናል። ዛሬ የዚህ ትውልድ አካል የሆንን ዜጎች ይህንን የተዛባ አካሄድ የመቀየርና ሃገራችንን የተሻለች ሃገር የማድረግ ኃላፊነት አለብን ብለን እናምናለን። በመሆኑም የሰማያዊ ፓርቲያችን ራዕይ፣ ተልዕኮና ዓላማ ለሃገራችን ካለን ጥልቅ ፍቅር፣ ለፍትሃዊ አስተዳደር መስፈን ካለን ፅኑዕ እምነትና ከሰው ልጅ ምክንታዊ አስተሳሰብ ይመነጫሉ። ፍትሕ እንዲሰፍን የምንፈልግ ሃገራችንንም በእውነት የምንወድ ከሆነና በሰው ልጅ ምክንያታዊ አስተሳሰብ የምንገዛ ከሆነ ችግሮቻችን በሰላማዊ መንገድ፣ በመነጋገር፣ በመደማመጥና በመግባባት ብሔራዊ እርቅና መከባበርን በመፍጠር የሚፈቱ ናቸው ብለን እናምናለን።

*ፓርቲያችን በሃገሪቱ ህገ-መንግስት መሠረት በሰላማዊ መንገድ የፖለቲካ ትግል በማድረግ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከውስብስብና ፈርጀ ብዙ ችግሮች ተላቆ እያንዳንዱ ዜጋ በነፃነት ሃሳቡን የመግለፅ፣ የመደራጀት፣ የፈለገውን የመደገፍና የመቃወም፣ በፈለገው ሙያና የሥራ መስክ የመሰማራት፣ ሃብት የማፍራትና የሃብቱ ባለቤት የመሆን እንዲሁም የግል ስብዕናውን የማሳደግ መብቱ የተረጋገጠ እንዲሆን እንታገላለን። ሐገራችን ከድህነትና ከጦርነት የተላቀቀች፣ ፍትሕና ሰላም የሰፈነባት እንድትሆን የፖለቲካ ሥልጣን በመያዝ የዜግነት ድርሻችንን ለመወጣትና ራዕያችንን እውን ለማድረግ ሰማያዊ ፓርቲያችንን መስርተናል። ሰማያዊ ፓርቲ ራዕዩን እውን ለማድረግ፤*

*ሀ. ፓርቲያችን የዲሞክራሲያዊ ሥርዓት መርሆችን ይከተላል።*

ለ. በሰማያዊ ፓርቲ ፕሮግራም ውስጥ ለተካተቱ አንዳንድ ጉዳዮች ተፈፃሚነት የሕገ-መንግሥቱ አንዳንድ ድንጋጌዎችን ህገ-መንግስቱ ባስቀመጠው የህገ-መንግስት ማሻሻያ መርሆች መሰረት ማሻሻል አስፈላጊ መሆኑን ታሳቢ ተደርጓል።

መ. ዓላም ዛሬ ከደረሰችበት የሥልጣኔ ደረጃና ከሰው ልጅ ምክንያታዊ አስተሳሰብ በመነሳት ከሰላማዊ ትግል ውጭ በሃገራችን የተረጋጋ የፖለቲካ ሥርዓትን መገንባት አይቻልም ብለን እናምናለን። ስለዚህ ፓርቲያችን በሰላማዊ የትግል ስልት የፖለቲካ ሥልጣን ለመያዝ ይታገላል።

በአጠቃላይ መልኩ ይህ የሰማያዊ ፓርቲያችን ፕሮግራም የፓርቲያችንን ራዕይ፣ ተልዕኮና ዓላማ እንደሚከተለው በዝርዝር አስፍሯል። ራዕይ የዜጎች ሰብዓዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች ሙሉ በሙሉ የተከበሩባት፤ ለሕዝብ ፍላጎት መሟላት በኃላፊነትና በተጠያቂነት መንፈስ የሚሰራ መልካም አስተዳደርና የህግ የበላይነት የተረጋገጠባት፤ የኢኮኖሚና ማሕበራዊ ብልፅግና የሰፈነባት፤ ለዜጎቿ ሁሉ አለኝታና መኩሪያ የሆነች፤ ለዓለም ሕዝብ መልካም ግንኙነት የበኩሏን አስተዋፅዖ የምታደርግ ኢትዮጵያን ማየት ነው።

ዓላማ፡-

ሀ. የዜጎች ዲሞክራሲያዊና ሰብዓዊ መብቶች እንዲከበሩና ተፈፃሚም ኢንዲሆኑ በጽናት መቆም።

ለ. ለዜጎች አስተማማኝ የማሕበራዊ ደህንነት ዋስትና አገልግሎት ማቅረብ።

ሐ. በኢትዮጵያ ፈጣንና ዘላቂ የኢኮኖሚ እድገት ማረጋገጥ።

መ. የፖለቲካ ፓርቲዎችና ግለሰቦች ነፃ፣ ፍትሃዊና ትክክለኛ በሆነ መንገድ ተወዳድረው የፖለቲካ ሥልጣን የሚይዙበት የምርጫ ሥርዓት መመስረት።

ሠ. ራዕዩን ተግባራዊ ለማድረግ በነፃና ፍትኃዊ ምርጫ በህዝብ ድምፅ የፖለቲካ ሥልጣን መያዝ

ረ. ሀቀኛ፣ ብቃትና ተጠያቂነት ባለው አመራር አማካኝነት ታታሪና የፈጠራ ችሎታ ያላቸው ዜጎች መፍጠር።

ሰ. የሕብረተሰቡን የፖለቲካ ግንዛቤ በማሳደግ ዜጎች በሃገራቸው ጉዳይ በንቃት እንዲሳተፉ፣ ግዴታቸውንና ኃላፊነታቸውንም እንዲወጡ ማድረግ።

ሸ. የእያንዳንዱን ዜጋ ችሎታ በማሳደግ በሃገርና በዓለም ደረጃ ብቁ ተወዳዳሪ ለመሆን ያለውን ምኞት ማሳካት።

ቀ. ከሀገራቸው ውጭ ያሉ ኢትዮጵያውያን ሰብዓዊና ቁሳዊ አቅማቸውን ለሃገራቸው ልማት እንዲያውሉና ለሕዝብም ቁሳዊና መንፈሳዊ ሕይወት መሻሻል የበኩላቸውን አስተዋፅዖ ማበርከት የሚችሉበት የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና የማሕበራዊ ሥርዓት መመስረት።

በ. ዓለምን ለመረዳትም ሆነ የዓለም ሕብረተሰብ በአግባቡ እንዲረዳው ማድረግ የሚችልና በነፃነት የሚያስብ ሕብረተሰብ መመስረት።

ተ. የኢትዮጵያ ወጣት ትውልድ በራሱና በወረሰው መልካም ነገር እንዲኮራና በሕይወቱ ውስጥ ተስፋ እንዲኖረውና ለከፍተኛ ግብ እንዲሰራ ማደፋፈር።

ተልዕኮ፡-

ተልዕኮአችን ዓላማችንን ማሳካት ሆኖ በተለይ በሀገራችን ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት እንዲሰፍንና የሕግ የበላይነት እንዲረጋገጥ ዋስትና የሚሰጥ ከሕዝብ፣ በሕዝብ፣ ለሕዝብ የቆመ መንግስት በሰላማዊ መንገድ መመስረት ነው።

*ሀገራዊ ዕይታ፡-*

ሀ. ኢትዮጵያ ሀገራችን በኢትዮጵያ ህዝብ ሙሉ ገዥነት ስር የሚገኘውን መሬት፣ ውሃ፣ የአየር ክልል፣ በከርሰ ምድርና በከርሰ ውኃ የሚገኘው ሃብት፣ በአየር ክልሉ ያለው የድምፅና የምስል ሞገድ ባለቤት ሉዓላዊ ሀገር ናት።

ለ. የኢትዮጵያ ያልተመለሱ የድንበርና የይገባኛል ጥያቄዎች መኖራቸው እንደተጠበቀ ሆኖ የኢትዮጵያ ሉዓላዊ የአስተዳደር ወሰን አሁን በኢትዮጵያ መንግስት ሥር የሚገኘውና በተባበሩት መንግስታት ድርጅት የተመዘገበዉ ክልል ነው።

ሐ. በኢትዮጵያ ውስጥና በውጭ ሃገራት የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን በአንድነት የኢትዮጵያ ሕዝብ ናቸው።

መ. የኢትዮጵያ ሕዝብም በኢትዮጵያ ጉዳይ ባለሙሉ የሥልጣን ባለቤት ነው። ሃገሪቱን የማስተዳደር ሥልጣን ከሕዝብ ይመነጫል።

ሠ. የኢትዮጵያ አንድነትም ሆነ ሉዓላዊነት አይነጣጠሉም፤ ለሌላም አይለቀቁም።

ረ. ኢትዮጵያውያን በግል ያላቸው የዜግነት መብትም ሆነ በወል የሚጋሩት የህግ፣ የፖለቲካ የማህበራዊና የባህል መብት የአንድነታቸው ዓይነተኛ መሰረት ነው።

ሰ. ኢትዮጵያ ሀገራችን የረጅም ጊዜ አኩሪ ታሪክ፣ የበርካታ ገፀ-ምድርና ከርሰ-ምድር ሃብት ባለቤት፣ አስደናቂ የተፈጥሮ ውበትና የሰው ልጅ ቀደምት ሥልጣኔ መገለጫ የሆኑ ቅርሶች ያሏት ታላቅ ሃገር ናት።

ሸ. ሃገራችን ኢትዮጵያ በተለያዩ ባህል፣ ሃይማኖት፣ ቋንቋ፣ ወግና ሥርዓት አሸብርቃ የኖረች፣ በብዙ ዓይነት ሃረጎች ተሳስረውና በታሪክ ተቆራኝተው የጋራ አመለካከትና ኢትዮጵያዊ ማንነትን በማዳበር ለዘመናት ተቻችለውና ተከባብረው በአንድነት የኖሩ ዜጎች ሃገር ናት።

እነዚህ ዜጎች በየዘመናቱ የተለያዩ አስተዳደራዊ በደልና ጭቆና ደርሶባቸዋል። ዛሬም ቢሆን የዜጎች የአስተዳደርና የፍትህ ጥያቄ በአግባቡ አልተፈታም ወይም መብታቸው አልተከበረም። በመሆኑም ሁሉም ዜጎች የዜግነት መብታቸው እንዲከበርና በሃገር ጉዳይ ላይ ተገቢው ድርሻና ተሳትፎ እንዲኖራቸው አሁንም ፅኑዕ ትግል የሚያስፈልጋት ሃገር ናት። ርዕዮተ ዓለም እጅግ ውድ የሆነው የሰው ልጅ ሃብት ነፃነቱ በመሆኑ ሰማያዊ ፓርቲ ለግለሰብ ነፃነት ቅድሚያ ይሰጣል። ዜጎች በቡድን ሊያከናዉኗቸው የሚፈልጓቸው እንደ ሃይማኖት፣ ልማዶች፣ ቋንቋ፣ ማህበራት እና የመሳሰሉት የጋራ መብቶች የግለሰብን በነፃነት የመወሰን መብት ሳይሸረሽሩ እንዲከበሩ የህግ ጥበቃ እንደሚያስፈልጋቸው ያምናል። በመሆኑም ሰማያዊ ፓርቲ በለዘብተኛ ሊብራል ዲሞክራሲ መሰረታዊ መርሆች ይመራል። ..... ይቀጥላል....

# ነጻነት የዋጋ ተመን የለውም !

በላይ ማናዬ

ዋጋ ስንል ተመን ወይም የአንድን ነገር የተመጠነ ልክ ማሳያ ማለታችን ነው፡፡ ዋጋ ስንል አንድን ነገር ወይም ዕቃ አሊያም አገልግሎት መግዣ፣ መሸጫ እንዲሁም መለዋወጫ ተመን ማለታችን ነው፡፡ ለምሳሌ በአሁኑ ወቅት በሀገራችን ያለው የጤፍ ዋጋ ይህን ያህል ነው ብለን ተመጣጣኝ ሊሆን በቻለው የብር ወይም ሌላ ምጥጥን ተመን ባለው ዕቃ ልንናገር እንችላለን፤ በተመሳሳይ አንድ ኪሎ ስኳር ከ15 ብር ጋር ተመጣጣኝ ወይም እኩል ነው ልንል እንችላለን፡፡ ስለሆነም ዋጋ ስንል ሊለካ ስለሚችል ነገር እያወራን ነው ማለት ነው፡፡

አንዳንድ ጉዳዮች ግን ከዚህ መሰረታዊ የዋጋ ጽንሰ-ሃሳብ የወጡ ናቸው፡፡ ለአብነትም የሰው ልጅ በዋጋ አይተመንም፤ እንደ ባሪያ ንግድ ዘመን ሰውን እንደ እቃ ቆጥረው ለመሸጥ በሚከጅሉት ‹የሰው አውሬዎች› ዘንድ ካልሆነ በቀር፡፡ ሆኖም ግን በአጠቃላይም ባይሆን በአመዛኙ ሰዎች ዋጋችን ስንት ነው ብለው ሲጠይቁ ይደመጣሉ፡፡

እነዚህ ሰዎች በሰውነታቸው ያላቸውን ክብርና መብት እየተነጠቁ ቢቸገሩ ለገዥዎቻቸው ማስተላለፍ የፈለጉት ነገር ቢኖር እንጂ ራሳቸውን በዕቃ ተራ ማውረዳቸው አይመስለኝም፡፡ ምክንያቱም ሰዎች ናቸውና፤ ሰዎች ደግሞ በዋጋ ሊተመኑ አይችሉም፤ አይገባምም፡፡ ሰው የፈጣሪ አምሳል ነው፤ ፈጣሪ ደግሞ አይለወጥም፤ አንድ ነው፡፡ የሰው ልጅም ቁስ ሊለካው የማይችል ክቡር ፍጡር ነው፤ ሰውን ዋጋ (Price) አስቀምጠንለት የምንለካው አይደለም፡፡

በተመሳሳይ አንዳንድ ጽንሰ-ሃሳቦችና መርሆዎች ከዋጋ ተመን በላይ ሆነው እናገኛቸዋለን፡፡ ከነዚህም ውስጥ ነጻነት የሚለውን በራሱ ነጻ የሆነ ጽንሰ-ሃሳብ ማየት ይቻላል፡፡ ከዚህ ጋር በተገናኘ በተለያየ ጊዜ በርካታ ሰዎች የነጻነትን ዋጋ ለማወቅ ሲጠይቁ አስተውያለሁ፤ ሰምቻለሁ፡፡ ‹‹ነጻነት ዋጋው ስንት ነው?››፣ ነጻነት ምን ያህል ዋጋ ያስከፍላል?››… እና በተለያየ አገላለጽ የሚቀርቡ ተመሳሳይ ጥያቄዎች ሲስተናገዱ ልብ ብያለሁ፡፡ የነጻነት ዋጋ ይህን ያህል ነው ብሎ መልስ የሰጠ ሰው ወይም ተቋም ግን አላውቅም፤ ወይም የለም፡፡

በእርግጥም ነጻነት የዋጋ ልክ ሊኖረው አይችልም፤ ዋጋ ሊተምነው ከሚችለው በላይ ነውና፤ አዎ፣ ነጻነት (Immeasurable or beyond calculable value) ነው፡፡ ነጻነትን ሀብት ያለው አይገዛውም፤ ሀብት የሌለው ደግሞ አይሸጠውም፤ ሊሸጠውም አይቻለውም፡፡ ነጻነትን ባለ ጠብመንጃ የግሉ አያደርገውም፤ ነጋዴ ሸጦ አያተርፍበትም፡፡ ምክንያቱም ነጻነት ቁስ ወይም የዕለት ከዕለት መገልገያ ዕቃ አይደለም፡፡

አሁን ላይ ብዙዎቻችን በገዛ ሀገራችን ነጻነት እንደሌለን እንናገራለን፡፡ በእውነትም ነጻነት የለንም፡፡ ይህ ግን ስንወለድ ጀምሮ ያጣነው ፀጋ ሆኖ አይደለም፡፡ ሸጠነውም አይደለም፤ ለጊዜው ተነጥቀነው እንጂ! አንድን ነገር ለመሸጥ ፍቃዳችን ሊኖርበት ይገባ ነበር፡፡ ለሸጥንበትም ተመጣጣኝ ክፍያ ልናገኝ ይገባ ነበር፡፡ ነገር ግን እንሸጠው እንኳ ብንል ነፃነት ከተመን በላይ ነው፤ ሊገዛው የሚችል ዋጋ የለም፤ አቅሙ የሚኖረው ገዥም አይገኝም፡፡ ስለዚህም ነጻነታችንን አልሸጥነውም፤ መሸጥ ብንችል ኖሮና ሸጠነው ቢሆን ኖሮ መልሰን አንጠይቅም ነበር፡፡

እናም ነጻነታችን ለጊዜው በጉልበታሞች እጅ ገብታለች፡፡ ለዚህም ነው ስለ ነጻነት አብዝተን የምንጮኸው፤ የማድረግ ነጻነትን በነጻነት ፈቅደን ያልሰጠነው አካል ነጻነታችንን እየመነተፈን ነው፡፡ አሁንም ግን ሙሉ በሙሉ አልተወሰደብንም፡፡ የተወሰደብንን ለማስመለስ በእኛ በኩል የማድረግ ጭላንጭል ነጻነት አለን፡፡ ለዚህም ነው ጭቁኖች ሁሉ (መጨቆናቸው የገባቸውና ለአርነታቸው ዘብ ለመቆም የወሰኑ) ቆርጠው እየታገሉ የሚገኙት፡፡

> አሁን ላይ ብዙዎቻችን በገዛ ሀገራችን ነጻነት እንደሌለን እንናገራለን፡፡ በእውነትም ነጻነት የለንም፡፡ ይህ ግን ስንወለድ ጀምሮ ያጣነው ፀጋ ሆኖ አይደለም፡፡ ሸጠነውም አይደለም፤ ለጊዜው ተነጥቀነው እንጂ ! አንድን ነገር ለመሸጥ ፍቃዳችን ሊኖርበት ይገባ ነበር፡፡ ለሸጥንበትም ተመጣጣኝ ክፍያ ልናገኝ ይገባ ነበር፡፡ ነገር ግን እንሸጠው እንኳ ብንል ነፃነት ከተመን በላይ ነው፤ ሊገዛው የሚችል ዋጋ የለም፤ አቅሙ የሚኖረው ገዥም አይገኝም፡፡ ስለዚህም ነጻነታችንን አልሸጥነውም፤ መሸጥ ብንችል ኖሮና ሸጠነው ቢሆን ኖሮ መልሰን አንጠይቅም ነበር፡፡

ነጻነት ነጻ አይደለም (Freedom is not free.)፡፡ በመሰረቱ ነጻነት ነጻ ቢሆን ኖሮ ሰዎች ለነጻነት አይታገሉም ነበር፡፡ ነጻነት በሰፈነበት ቦታ ሁሉ የነጻነት ትግል ብሎ ነገር ሊኖር አይችልም፡፡ ዛሬ ላይ እልፍ አዕላፋት ትግል ላይ ናቸው፤ ይህ የሚያሳዬን ነጻነት አለመኖሩን ነው፡፡ ሰዎች በተፈጥሯቸው ግፍና ጭቆናን እንዲሁ አሜን ብለው አይቀበሉም፡፡ ስለሆነም ጭቆና ባለበት ቦታና ሁኔታ ሁሉ ስለ ነጻነታቸው ይታገላሉ፤ እስከ ሞት ድረስ አፈናን ተቃውመው፣ ነጻነትን ወግነው ይዋደቃሉ፡፡

በሀገራችን ኢትዮጵያ ያለውን ሁኔታ ብናይ እንኳ ሁሌም ትግል መኖሩን እንታዘባለን፡፡ ትናንት ወረራን ለመከላከል ስለ ነጻነታችን ታግለናል፤ ከራሳችን አብራክ በወጡ ጨቋኞች ላይ አብረን ተነስተናል፡፡ ትግላችን ቆሞ አያውቅም፡፡ ምክንያቱ ደግሞ እስከ ዛሬም ድረስ ነጻነታችንን መጎናጸፍ ስላልቻልን ነው፡፡ አንዱ ጨቋኝ ሄዶ ሌላው ጨቋኝ እየተተካ በመሄዱ ምክንያት ትግላችንም መቀጠሉ አልቀረም፡፡ ደግሞም ገና እንታገላለን፤ የተሻለ ነጻነት ሲመጣ ትግላችን ይቀንሳል፤ እንዳሁኑ ያለ ሁኔታ እስካለ ድርስ ግን ትግላችን መፋፋሙ እሙን ነው፡፡

ትግሉ ዋጋ ያስከፍላችኋል የሚልን አካል ሰሚ ጆሮ አንሰጠውም፤ ከዚያ ይልቅ ትግሉን እንዲቀላቀል እንመክረዋለን፡፡ ስለነጻነት እየታገልን የምንከፍለው ዋጋ በአፈና ውስጥ ሆነን ከምንከፍለው ዋጋ የበለጠ የከፋ ነው፡፡ ላለመታገል ምንም ምክንያት ሊኖረን አይችልም፤ ስለራሳችን መብት መከበር ለመታገል ግን አያሌ ምክንያቶች አሉን፡፡ እናም በዋጋ ለማይተመነው ነጻነታችን ስንል መታገላችን ትክክል ነው! ትግሉም የማይቆም ሰደድ ይሆናል፡፡ ትግላችን ደግሞ ሰላማዊ ነው፤ ሲጀመርም ነጻነት ማለት ጦርነት ማለት አይደለምና፡፡ በጨለማው ውስጥ ጭላንጭል ብርሃን አለ፤ ይህ ጭላንጭል ብርሃን በትግላችን የበለጠ ፈክቶ ጨለማውን ያሸንፋል፡፡ ያኔ ከዋጋ ተመን በላይ የሆነውን ነጻነታችንን በሀገራችን እንጎናጸፋለን፡፡

ዴሞክራሲያዊና የዘመነ አስተዳደር ለኢትዮጵያ ይገባታል!

## የኢትዮጵያ ፖለቲካና . . .

ከ ገፅ 12 የዞረ

መጽሃፍ ላይ ‹‹ከገብሩ ሀሳብ አትለይም ብለው የነበረኝ የትግል ልምድ፣ እምነትና አስተሳሰብ ግምት ውስጥ ሳያስገቡ ሚስት ከባሏ ሀሳብ ውጭ የራሷ የሆነ ሀሳብ አይኖራትም በሚል ኋላ ቀር አመለካከት በመነሳት የነበረኝን የስራ ሃላፊነት እንዳልወጣ እንቅፋት ሆነውብኛል፡፡›› በሚል ቃል በቃል አንብቤያለሁ፡፡ እውነት ሴት ከባሏ የተለየ ሀሳብ አይኖራትም? ይህ በኢህአዴግ ዘመን በሴቶች ላይ የተጫነ ጭቆና አንድ አካል ነው፡፡

ኢህአዴግ ሴቶችን ከመሳሪያነት፣ ለስልጣን ከመወጣጫነት ያለፈ ስለማይፈልጋቸውና ስለሚጨቁናቸው ከወንዶቹ ጋር የታገሉት እነዚያ ታጋይ ሴቶች አሁን ስልጣን ላይ የሉም፡፡ በአሁኑ ወቅት ተቃዋሚ ውስጥ ያለው ተሳትፎም ተመሳሳይ ነው፡፡ አንድ በመቶ ሴቶች አይኖራቸውም፡፡ ይህ አንዱ የተቃዋሚዎች የቤት ስራ ነው፡፡ ተቃዋሚ ፓርቲ ውስጥ ያሉ ወንዶች እህት፣ እናት፣ የፍቅር ጓደኛ፣ ሚስትና ሌሎች ሴቶች በአካባቢያቸው ይኖራሉ፡፡ ታዲያ እነዚህን ሴቶች እነሱ ወደሚሳተፉበት ፖለቲካ ለመሳብ እንዴት አልቻሉም? በየ ቤቱ የሰብዓዊም ሆነ ሌላ ጭቆና የበዛባቸው፣ እምባቸውን የሚያፈሱ ሴቶች ሞልተዋል፡፡ በየ ቤቱ ስትሄዱ እናቶች፣ እህቶች፣ ሚስቶች ሌሎችም ሴቶች በኢኮኖሚው፣ በፖለቲካዊ በማህበራዊ ጉዳዮች ያማርራሉ፡፡ እነዚህን ሴቶች ፓርቲ ፖለቲካ ውስጥ ገብተው የሚመስላቸውን አመለካከት እንዲያራምዱ የሚገፋፉትና የሚያግዙት ወንዶች ይህን ያህል ናቸው፡፡ ሴቶች ወንዶች ታግለው ነጻነታችንን ያረጋግጡልናል ብለው ነው ወይንስ ኢህአዴግ ውስጥ እንደተደረገው አብረን ሄደን መጨረሻ ላይ ልንገፈተር ነው? እኔ እንደሚመስለኝ የቀድሞ አባቶቻችን (ለአብነት ያህል ምኒልክን የመሳሰሉት) ለሴቶች ከነበራቸው እምነት በመማር የዘመኑ ወንዶች በሴቶች ላይ እምነት ጥለው ወደ ፖለቲካው እንዲመጡ ማድረግ አለባቸው፡፡ በግላቸው ወንዶች የሚያደርጉባቸውን ጫናም ሆነ የባህል ተጽዕኖውን በመቀነስ ይህን ተሳትፎ ከፍ ማድረግ ይቻላል፡፡ በሌላ በኩል ሴቶችም ቢሆን የራሳችንን ነጻነት ማስከበር ይኖርብናል፡፡ ይህ ሲሆንም ነው ወንዶች በእኛ ላይ ክብርና እምነት ሊኖራቸው የሚችለው፡፡ ሁለቱ ተዳምረው ሴቶች በፖለቲካው ላይ የሚኖራቸውን አስተዋጽኦ ከፍ ያደርገዋል፡፡ ሴቶች እናቶች፣ እህቶች፣ ሚስቶች እንደመሆናቸው በፖለቲካው ሲሳተፉ ወንዶችንም ወደ ፖለቲካው ይስባሉ፡፡ ከእናትነት፣ ከሚስትነትና እህትነትም በላይ ሩህሩህ፣ አዛኝ፣ አስተዋይና ብልህ መሆናቸው ደግሞ በወንዶች የበላይነት የተበላሸውን የአገራችንን ፖለቲካ ማነቃቃት ብሎም ማስተካከል ይቻላል፡፡

# ኢትዮጵያዊነት ለእኔ!



አፈወርቅ በደዊ

አትዮጵያዊነት ለእኔ በቀለበት ይመሰላል፡፡ ቀለበት ፈርጥ ካለው ያምራል፡ ፡ ያለ ፈርጥ ግን ቀለበት አለ፡፡ ግን አያምርም፡፡ ስለዚህ በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ ጎሳዎች የቀለበት ፈርጥ እንጂ ቀለበት አይደሉም፡፡ ህልውናቸው ከቀለበቱ ጋር በጥብቅ የተሳሰረ ነው፡፡ ቀለበት ከሌለ ፈርጥ የለም፡፡ ኦሮሞ፣ አማራ፣ ትግሬ፣ ወላይታ፣ ጋምቤላ፣ ጉሙዝ እና ሌሎችም እያልን በሃገሪቷ ውስጥ ያሉትን ጎሳዎች በጠቅላላው ብንዘረዝር የሃገሪቷ ውበቶች ወይም ፈርጦች ናቸው፡፡

---

እያንዳንዱ ጎሳ እና የጎሳ አባል ማወቅ የሚገባው ዋና ነገር ጎሳው ኢትዮጵያዊ በመሆኑ ያገኘው ገፀ-በረከት እንጂ መርጦ እና ፈቅዶ ያገኘው አለመሆኑን ነው፡፡ እኔ ኦሮሞነቴን ወይም አማራነቴን ያገኘሁት ኢትዮጵያዊ በመሆኔ ነው ብሎ ማሰብም ሆነ ማመን ያስፈልጋል፡፡ ይህ ባልሆነበት ሁኔታ እኔ ኢትዮጵያዊ ባልሆንም ኦሮሞ፣ አማራ ወይም ትግሬ ወይም ሌላ ጎሳ መሆን እችላለሁ የሚል ግንዛቤ እውነትነት የሌለው የትም የማያደርስ መንገድ ነው፡ ፡ አንዳንድ ያወቅን የነቃን የጎሳ አባላት ነን የሚሉ ‹‹አላዋቂ አዋቂዎች ወይም አለማወቃቸውን የማያውቁ አዋቂዎች›› ማንነታቸውን እና መሰረታቸውን ረስተው የሚያራምዱት መርዘኛ አስተሳሰብ የትም አያደርስም፡፡

እንዴት እና በየትኛው መመዘኛ አሮሞ ኢትዮጵያዊ ከመሆኑ በፊት አሮሞ ሊሆን እንደሚችል ‹‹የኦሮሞ ፈርስት›› አስተሳሰብ ጠንሳሾች እና አራማጆች ማስረዳት የሚያስችል የእውቀትም ሆነ የሞራል ብቃት ሊኖራቸው አይችልም፡፡ ኢትዮጵያዊነት እራሳቸው በየጓዳው የሚያበስሉትን መርዝ እንደማስረጃነት ለማቅረብ ሊያስገቡበት የሚችሉበት ምንም ክፍተት የለውም፡፡ ሊጠቀሙበት የሚችሉት ብቸኛው ክፍተት የወያኔ መንግስት ያዘጋጀላቸውን የጎሳ ፖለቲካ ብቻ ነው፡፡

እኔ አሮሞነቴ በኢትዮጵያዊነቴ ያገኘሁት ሽልማት እንጂ አውሮፓ ወይም አሜሪካ ወይም ኤሲያ ወይም የተቀረው አፍሪካ ውስጥ ብወለድ አሮሞነትን የሚያክል ትልቅ ገፀ-በረከት አገኛለሁ ብሎ ማሰብ የቁም ቅዠት ብቻ ሳይሆን እብደትም ነው፡ ፡ ምናልባት ‹‹የኦሮሞ ፈርስት›› አስተሳሰብ ጠንሳሾች እና አራማጆች በዚህ ሰዓት እኔን ለመሞገት የሚጠቀሙበት ክፍተት ቢኖር በኬንያ፣ በሩዋንዳ፣ በዩጋንዳ፣ … ያለው ኦሮሞ ኦሮሞነቱን እንዴት አገኘው ብለው ሊሆን ይችላል፡፡ ለዚህ ቀለም እና ወረቀት ከማባከናቸው በፊት መልሼ ማለፍ ይኖርብኛል፡፡

በተጠቀሱት አገሮች የሚገኘው ኦሮሞ ‹‹የኦሮሞ ፈርስት›› አስተሳሰብ ጠንሳሾች እና አራማጆች በስደት በአውሮፓ እና አሜሪካ እንደሚኖሩት ሁላ በኢትዮጵያዊነቱ የኦሮሞነት ገፀ-በረከቱን ከተረከበ በኋላ በተለያዩ ገፊ ምክኒያቶች (pushing factors) ሃገሩን ጥሎ በመሰደድ አሁን ባለበት አጎራባች አገሮች ለመኖር የተገደደ ነው፡፡ እዚህ ጋር መርሳት ያልነበረባቸው ጉዳይ እነርሱ ዛሬ አሜሪካ ወይም አውሮፓ ሆነው የሚያቀነቅኑት የጎሳ ተኮር ፖለቲካ መነሻቸው እዚሁ ኢትዮጵያ መሆኑን ነው፡፡ ለምን አውሮፓዊ፣ አሜሪካዊ፣… የሆነ ኦሮሞ፣ አማራ፣ ትግሬ፣ ወላይታ፣ ከምባታ፣ …ሊኖር አልቻለም፡፡ የእነዚህ ሃገሮች ማሕፀን እነዚህን ጎሳዎች ለመፍጠር ስላልተመረጠ ወይም የሚያስችል አቅም እና ብቃት ስለሌለው ነው፡፡

እነዚህ ‹‹የኦሮሞ ፈርስት›› አስተሳሰብ ጠንሳሾች እና አራማጆች የሚያራግቡት የአባቶቻቸውን ታሪክ ሳይሆን የአባቶቻቸውን ጠላቶች ታሪክ ነው፡፡ እንደ ኢህአዴግ የኦሮሞን፣ የአማራን፣ ወይም የትግሬን ህዝብ የበደለ ከየትም ሊመጣ አይችልም፡ ፡ እውነት እነዚህ ሰዎች እንደሚሉት አባቶቻቸው በኢትዮጵያዊነታቸው ላይ እምነት የላቸውም? የኦሮሞ ህዝብ አድዋ ዘምቶ በኢትዮጵያዊነቱ የመጣበትን ጠላት መግቢያ መውጫ አላሳጣም?

ለነገሩ እነዚህ ሰዎች ጎበናን የሚያክል ጀግና እንዲሁም ባልቻን የሚያክል የጦር ገበሬ ኦሮሞነት ሲክዱ ማንነታቸውን ወይም አሮሞነታቸውን ክደዋል፡፡ እነዚህ ከላይ የጠቀስናቸው ሃገራችን በታሪኳ ዳግም ልታፈራቸው ያልቻለች ጀግኖች ለኢትዮጵያዊነት ክብር ደማቸውን አፍሰው፣ አጥንታቸውን ከስክሰው እንዲሁም ውድ ህይወታቸውን ያለማወላወል ገብረዋል፡ ፡ የኢትዮጵያዊነት ክብር ሳይኖር የኦሮሞነት ክብር ሊኖር እንደማችል ቀድሞውኑ ተረድተው ነበር፡፡ አሮሞነት ያለ ኢትዮጵያዊነት ምንም አቋራጭ መንገድ እንደሌለ አበክረው አምነው ነበር፡ ፡ ‹‹ጅራቷ ያደርሳል ካናቷ›› እንደሚባለው ታዲያ እነዚህ ሰዎች የሚያወሩት እና የሚያቀነቅኑት ኦሮሞነት የአባት የቅድመ-አያታቸውን ወይስ የኢትዮጵያ እና የኢትዮጵያዊነት ጠላት በሆነው የወያኔ መንግስት ለአገዛዝ እንዲያመቸው ያቀበላቸውን አሮሞነት?

እኔ ይህንን ፅሁፍ ስፅፍ ባልቻ እና ጎበና የሞቱለትን በኢትዮጵያዊነቴ ያገኘሁትን ኦሮሞነት መሰረት አድርጌ ነው፡፡ ለእኔ ባልቻ ኦሮሞ ነው፡፡ ለእኔ ጎበና ኦሮሞ ነው፡፡ ለእኔ የእነዚህን ጀግኖች ኦሮሞነት ክዶ አሮሞነት ሊኖር አይችልም፡፡ አንዳንዶች መለስ እና ግብራበሮቹ (አጫፋሪዎቹ) ካደረሱብን በደል ተነስተው ኢትዮጵያዊነታቸውን ጥያቄ ውስጥ ሲያስገቡ የባሰባቸውም ኢትዮጵያዊነታቸውን ሲገፉ መመልከት የተለመደ ነው፡፡ የወያኔዎች ኢትዮጵያዊነት መካድ የራስን ኢትዮጵያዊነት መካድ ነው፡፡ የእነዚህን ሰዎች ኢትዮጵያዊነት ይቅረብም ይራቅ ከእኛ ኢትዮጵያዊነት ጋር የተጋመደ ነው፡፡ የአንዱን ኢትዮጵያዊነት ለመግፈፍ ስንሞክር የራሳችንን እንዳንገፍ መጠንቀቅ ይኖርብናል፡፡

ኢትዮጵያዊነትን ማንም ሰው ሲያሰኘው የሚሾመው የሚሽልመው ሲያሰኘው ደግሞ የሚገፈው ማዕረግ አይደለም፡ ፡ እነዚህ ሰዎች ከሰው ተፈጥረው ሰው ለማጥፋት ታትረው የሚሰሩ እንዳሉ ሁሉ ከኢትዮጵያ ማሕፀን ተፈጥረው አትዮጵያ፣ ኢትዮጵያዊያን እና ኢትዮጵያዊነት ለማጥፋት ቀን ከሌት ተግተው የሚሰሩ የአስተሳሰብ እና አመለካከት ስህተት ያላቸው ኢትዮጵያዊያን ናቸው፡፡ ይህ ስህተት ማረም የሚቻለው ኢትዮያዊነትን በመግፈፍ ሳይሆን አመለካከት እና አስተሳሰባቸውን በተሻለ አመለካከት እና አስተሳሰብ ለመተካት ታትሮ በመስራት ነው፡፡

የጎበናንም ሆነ የባልቻን ኦሮሞነት የመግፈፍ ወይም ጥያቄ ውስጥ የማስገባት የሞራል ብቃት ሆነ መብት ያለው አንድም ግለሰብ የለም፡፡ ምናልባት እነዚህ ሰዎች ኢትዮጵያዊነታቸው ከኦሮሞነታቸው በልጦባቸው ጥቂቶችን በማወቅም ሆነ ባለማወቅ ‹‹ያስቀየመ›› ተግባር ፈጽመው እንኳ ቢሆን ኦሮሞነትን ሊያስገፍፍ የሚችል አንዳችም ተግባር የለም፡፡

የኦሮሞ ህዝብ እንደተቀሩት ህዝቦች እና ጎሳዎች በኢትዮጵያዊነቱ ያገኘው እንጂ ያጣው አንዳችም ነገር የለም፡፡ ነገር ግን በተለያዩ ወቅቶች በሃገሪቷ ስልጣን ላይ በወጡ ገዢዎች የኦሮሞን ህዝብ እንደተቀረው የኢትዮጵያ ህዝብ ሁሉ ሲጨቆን መኖሩ የማይካድ ሃቅ ነው፡፡ ይህንን የኦሮሞ ህዝብ በኦሮሞነቱ የተቃጣበት ችግር ብቻ ሳይሆን በኢትዮጵያዊነቱ የተቃጣበት ችግር ነው፡፡ የኦሮሞን ህዝብ ከተቃጣበት ችግር ለማላቀቅ ብቸኛ መፍትሔው የኢትዮጵያን ህዝብ ከባርነት እና ጭቆና ነፃ ማውጣት ብቻ እና ብቻ ነው፡፡ የኢትዮጵያ ህዝብ ነፃ ወጥቶ የኦሮሞ ህዝብ በባርነት የሚኖርበት ሁኔታ እና ምክኒያት የለም፡፡ መላው የኢትዮጵያ ጎሳዎች ከኢትዮጵያዊነታቸው በሚያገኙት ትሩፋት ልክ የኦሮሞ ህዝብም ተጠቃሚ ይሆናል፡፡

ማንኛውም ጎሳ አማራም ሆነ ትግሬ በኢትዮጵያዊነት ውስጥ ያላቸው ድርሻ ከየትኛውም ጎሳ አይበልጥም፤ አያንስምም፡ ፡ ሁሉም ጎሳዎች በኢትዮጵያ ውስጥ ያላቸው የባለቤትነት ድርሻ እኩል ነው፡ ፡ ማንኛውም ጎሳ ይህንን አምኖ ከተቀበለ በኢትዮጵያዊነት ላይ ምንም ጥያቄ ሊያነሳ አይችልም፡፡

የኦሮምን ህዝብ ኢትዮጵያዊነት የሚጠራጠሩ ግለሰቦች እና ስብስቦች ለኦሮሞ ህዝብ ጥፋትን እንጂ ልማትን የሰነቁ አይደሉም፡፡ የኦሮሞን ህዝብ አትዮጵያዊነትን መካድ ለኢትዮጵያዊነት የተዋደቁ የኦሮሞ ጀግኖችን መካድ ማለት ነው፡፡ የኦሮሞ ህዝብ ኢትዮጵያዊ ባይሆን ኖሮ አድዋ ድረስ ዘምቶ ባልደማ ወይም ባልሞተ ነበር፡፡ የኦሮሞ ህዝብ አድዋ ድረስ የዘመተው ተገዶ ወይስ አድዋ የኦሮሞ ግዛት ነው ብሎ? በእኔ አመለካከት ለሁለቱም መልሱ አሉታዊ ነው፡፡ ማለትም የኦሮሞ ህዝብ አድዋ ድረስ ሂዶ የደማውም ሆነ የሞተው ተገዶ ወይም ግዛቱ ስለሆነ ሳይሆን በኢትዮጵያ ላይ የተቃጣውን አደጋ የመጋፈጥ እና የመቀልበስ ኃላፊነት እና ግዴታ እንዳለበት አምኖ ስለተቀበለ ነው፡፡

በመጨረሻም እኔ ኦሮሞነቴን በኢትዮጵያዊነቴ ያገኘሁት ነው፡ ፡ ከኢትዮጵያዊነት የተለየ ኦሮሞነትም የለኝም፡፡ ሊኖረኝም አይችልም፡፡ ስለዚህ መጀመሪያ ኢትዮጵያዊ ነበርኩ፡፡ ኩሩ ኢትዮጵዊ በመሆኔ ኢትዮጵያ ሃገሬ አሮሞ የሚባል ጎሳ በገፀ-በረከትነት አበረከተችልኝ፡ ፡ እኔም ይገባኛል ብዬ ተቀበልኳት፡፡ ለሌላው ወንድሜ አማራ፣ ለሌላዋ እህቴ ትግሬ፣ ሌላዋ ወላይታ፣ ለሌሎቹ ደግሞ ሌላ ተበረከተላቸው፡፡ ወደው አክብረው ተቀበሉት፡፡ እኔ ኦሮሞነቴን በማከብረው እና በምወደው ልክ ሌሎች ጎሳዎችን እወዳለሁ፤ አከብራለሁ፡፡ ከእነርሱም የተለየ ማንነት የለኝም፤ ሊኖረኝም አይችልም፡፡

እዚህ ጋር ኢትዮጵያን እና ኢትዮጵያዊነትን በጆውራራ አይን ለሚያዩት ለጃዋር እና ለጃዋራዊያን መልክቴን ሳስተላልፍ… ኦሮሞ ለመሆን ብቸኛው መንገድ ኢትዮጵያዊ መሆን ነው፡ ፡ ኢትዮጵያዊነትን አዋርዶ ኦሮሞነትን ማስከበር አይቻልም፡፡ ኢትዮጵያዊ ለመሆን ብቸኛው መንገድ አፍሪካዊ መሆን ነው፡ ፡ አፍሪካዊ ሳይሆኑ ኢትዮጵያዊ መሆን አይታሰብም፡፡ ኢትዮጵያዊ ሳይሆኑ ኦሮሞነት የለም!!!

ስለዚህ ‹‹ቦይ-ኮት›› ብለህ በነካው እጅህ የአባትህን ታሪክ ባቆሸሸው ወያኔ ላይ ‹‹ቦይ-ኮት ወያኔ›› አውጁበት፡፡ ያለ እዚህ መንግስት አትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊ ክቡር ነው፡፡ ይህም ማለት የኦሮሞ፣ የአማራ፣ የትግሬ፣…ህዝብ ክቡር ነው፡፡

*ክብር ለኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊያን ይሁን!!*

*የነገ ሰው በለን!!*